ያልተሰበረ
ልብ



ገጽ 16

የሕዝብ ጥያቄን የሚመልሰው የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ በሆሳዕና



ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 203 መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ፦ ዳኘ አበራ

## "ሀገራዊ እሳቤዎቻችንን እና ሀብቶቻችንን በአግባቡ በመጠቀም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ትልቅ አቅም አለን"

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት
እና የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ

**መማር ደበልጣል**

አዲስ አበባ፡- "ሀገራዊ እሳቤዎቻችንን እና ሀብቶቻችንን በአግባቡ በመጠቀም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ትልቅ አቅም አለን" ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አደም ፋራህ ገለጹ።

አቶ አደም ፋራህ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ ያላት ሀገር ነች። ሀገራችን የልማት ጉዞዋን በጀመረችው አግባብ ከቀጠለች የብልጽግና ግባችንን ዕውን እንደምናደርግ የሚያሳዩ ሶስት መሰረታዊ አቅሞች አሉ።


የመጀመሪያው ጉዳይ እሳቤዎቻችን ላይ ያተኩራል ያሉት አቶ አደም፤ እንደሀገርም ሆነ እንደ ፓርቲ ሀገር በቀል የሆኑ የኢትዮጵያን


ሀገራዊ ... ወደ ገጽ 17 ዞሯል






የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

## "ግድቡ የደረሰበት ደረጃ ኢትዮጵያ ፍላጎቷን ማሳካቷን የሚያሳይ ትልቅ ድል ነው"

- አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ
የዓባይ ግድብ ተደራዳሪና ዓለም አቀፍ የሕግ ምሁር


ገጽ 4


## በማደያዎች የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ መካሄድ ጀመረ

### -ከሐምሌ አንድ ጀምሮ ግብይቱ ሙሉ በሙሉ ዲጅታላይዝ ይደረጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በማደያዎች የነዳጅ ግብይትን በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ለማከናወን የሚያስችል የሙከራ ትግበራ ሥራ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ኢትዮ ቴሌኮም በትብብር በትናንትናው ዕለት ተጀምሯል።

በመርሃግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትሩ ዶክተር አለሙ ስሜ እንዳሉት፤ የነዳጅ ግብይት በዲጂታል ማከናወን ብክነትንና ሌብነትን ለመከላከል ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።


በማደያዎች የነዳጅ ... ወደ ገጽ 17 ዞሯል


ፎቶ፦ ዳኘ አበራ



## "የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተሻለ እድገት እንዲያስመዘግብ ዓለም አቀፍ ተቋማት የብድር እፎይታ ጊዜን ሊያራዝሙ ይገባል"

- ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ
የምጣኔ ሀብት ባለሙያ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋማት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተረጋግቶ እንደገና የተሻለ ደረጃ እስኪደርስ ከሚሰጡን ገንዘብ ይልቅ ያለብንን ዕዳ ሊያራዝሙ እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ ገለጹ፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት


የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ክልሉ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የህብረተሰቡን ሕይወት ለማሻሻል እየሰራ ነው

**- በ2015 ደረጃቸውን የጠበቁ 100 ሺህ ቤቶችን ይገነባሉ**

**ገመቹ ከድር**

አሰላ፡- ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅና በመቅዳት የህብረተሰቡን ሕይወት ለማሻሻል የሚያስችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶችን በመስራት ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ እንደሚገኝ የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ። በክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት የተመራ ቡድን የአትሌት ቀነኒሳ በቀለ ፖሊቴክኒክ ማሰልጠኛ ኮሌጅን ጎብኝቷል።

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ ክልሉ የህብረተሰቡን ሕይወት ለማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅና በመቅዳት ላይ ትኩረት በማድረግ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ይህንን ለማሳካትም የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጉልህ ሚና እንዳላቸው የጠቆሙት አቶ አወሉ፤ የክልሉ መንግሥት በገጠርና በከተማ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አወሉ ገለጻ ፣ በክልሉ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ቴክኖሎጂን በማፍለቅ ለልማት ማዋል፣ ጠንካራ ኢንተርፕረነርሽፕ በመፍጠር በከተማና በገጠር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ጥረት እየተደረገ ነው። በገጠር አርሶአደሩ ሁለት ጊዜ እንዲያመርት በማድረግ ገቢያቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው።

እነዚህን ፕሮግራሞች ከግብ ለማድረስ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ቴክኖሎጂን በማፍለቅና በመቅዳት ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶችን ለመስራት ጉልህ ሚና አላቸው ያሉት አቶ አወሉ፤ በዚህም መሠረት በ2015 ዓ.ም የህብረተሰቡን ሕይወት መቀየር የሚያስችሉ 100 ሺህ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች ለመገንባት መታቀዱን ገልጸዋል።

በቀነኒሳ ፖሊ. ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የተመረተውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችሉ ብሎኬቶችን ለማምረት የሚያስችለውን ማሽን እንደጎበኙ አቶ አወሉ ገልጸው በማሽኑ ፈጠራና ብሎኬት ማምረት ሂደት ውስጥ የስራ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

የኦሮሚያ ስራ ዕድል ፈጠራና ሙያ ቢሮ ሃላፊ አቶ ማቲያስ ሶቦቃ በበኩላቸው ፣ ቢሮው ስራ ዕድል መፍጠር፣ ሙያን የተላበሰ ህብረተሰብ መገንባት፣ ኢንተርፕረነርሽፕን ማሳደግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማዕከል ያደረገ ፈጠራ ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ ቴክኖሎጂን በመቅዳት ከአካባቢው ጋር የሚስማሙ ሞዴል ቤቶችን ለመገንባት የሚያስችሉ ማሽኖችን በመፍጠር እንደማሳያ መወሰዱን ገልጸዋል።

አትሌት ቀነኒሳ ፖሊ. ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኮሌጅ ዲን አቶ ነስረድን ቃዲ ኮሌጁ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት ቴክኖሎጂን ማፍለቅ፣ መቅዳትና ማባዛት ላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ እስከ አሁን በተሰራው ስራ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶችን ለመስራት የሚያስችሉ ብሎኬቶችን ማምረት የሚችል ማሽን መፍጠር ችሏል ብለዋል። ኮሌጁ በ25 ዓመት ውስጥ በመደበኛና በአጫጭር ስልጠናዎች ከ40ሺህ በላይ ዜጎችን ማሠልጠኑንም ጠቁመዋል።

ኮሌጁ ጠቅላላ መካኒካል ዎርክሾፕ (general mechanics) ፣ አውቶሞቲቪ ፣ መንጃ ፈቃድ ማሰልጠኛ ማዕከልና በህላዊና ዘመናዊ የልብስ ማምረቻ (testile) ክፍሎች እንዳሉት መረዳት ተችሏል።



# የካቲት 12 ሆስፒታል የተመሰረተበትን 100ኛ ዓመት በቅርቡ ያከብራል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ ፡- የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አንድ መቶኛ ዓመት የአገልግሎት ዘመን ክብረበዓሉን የነበሩ መልካም ጎኑቹን በማሳደግ በቅርቡ እንደሚያከብር ተገለጸ፡፡

የየካቲት 12 ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሮቮስት አቶ አለሙ ክብረት እንደገለጹት ሆስፒታሉ 100ኛ ዓመቱን የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በማከናወን ያከብራል፡፡

በዚህም የነጻ ህክምና በመስጠት፣ ሕዝብ በሚበዛባቸው ቦታዎች ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች የነጻ ምርመራ በማድረግ፣ ወረፋና ረጅም ቀጠሮ ያላቸው የከፍተኛ ቀዶ ጥገና ህክምናዎችንና የሥነ ልሳን ህክምናዎችን በዘመቻ መልክ በማከናወንና ለአቅመ ደካሞች የቤት እድሳት በማድረግ እንደሚያከብር ገልጸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የስፖርት መርሀግብሮች ፣ የጥናትና ምርምር አውደ ጥናት፣ ሆስፒታሉ ሲመሰረት ጀምሮ በሕይወት ያሉ ሰራተኞችን እውቅና በማድረግና የአብረን እንስራ ግብዣ በማቅረብ ይከበራል፡፡

የየካቲት 12 ሆስፒታል ዋና ፕሮቮስት ዶክተር ኤልያስ ተዋበ ሆስፒታሉ በአሁኑ ሰአት በአስተኝቶ ህክምና ፣ በተመላላሽ ህክምና ፣ በድንገተኛ ህክምና በርካታ ዘርፎች አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሆስፒታሉ አገልግሎቱን በማዘመን ከወረቀት ነጻ የሆነ አገልግሎት እየሰጠ ነው ያሉት ዶ/ር ኤልያስ የመድሃኒት ግልጋሎት በተመለከተ ባለፉት አምስት ዓመታት በተሰራው ስራ የመድሃኒት ምጣኔን 86 በመቶ ማድረስ ተችሏል ብለዋል፡፡

ተቋሙ ቀዳሚ በሆነበትና በሀገር ደረጃ በሚታወቅበት የቃጠሎ ህክምና ፣ በከንፈርና ላንቃ ክፍተት ላለባቸው የቀዶ ጥገና ህክምናና በንግግር ህክምና በርካታ አገልግሎት መስጠቱን ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በሀገሪቱ ህሙማን ቁጥር እየጨመረ ላለው የካንሰር ህክምና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በዘንድሮው ዓመት ስራ እንዲጀምር የተደረገ ሲሆን በዚህም ከሶስት ሺ በላይ ለሚሆኑ ህሙማን አገልግሎት መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

የሆስፒታሉ የአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕሮቮስት ዶ/ር መረርቱ ተመስገን ሆስፒታሉ በ2003 ዓ.ም ሜዲካል ኮሌጅ ሆኖ ከተቋቋመ በኋላ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኘውን ከፍተኛ የሆነ የጤና ባለሙያ እጥረት ለመቅረፍ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በመሆን ላለፉት ዓመታት ከ 400 በላይ የጠቅላላ ሀኪሞችንና ከ 200 በላይ የህብረተሰብ ጤና ባለሙዎችን አስመርቋል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል የተቋሙ ተልዕኮ የሆነው የጥናትና ምርምር ስራ ሲሆን በሜዲካል ኮሌጁ በመምህራንና ጤና ባለሙያዎች ከ150 በላይ የሚሆኑ የምርምርና ጥናት ስራዎች ለህትመት መብቃታቸውን ገልጸዋል፡፡

በ1915 የተቋቋመው የካቲት 12 ሆስፒታል ኤክስሬይ ህክምና ፣ የነርሲንግ የህክምና ትምህርት፣ እንዲሁም የደም ልገሳን በቀደምትነት ያስተዋወቀ ሆስፒታል ነው፡፡

# የመስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ ከ213 ሺህ በላይ ለሆኑ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሰጥቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ከሐምሌ 2013 እስከ መጋቢት 2015 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ በመስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ ከ213 ሺህ በላይ መኪናዎች አገልግሎት ማግኘታቸውን የኤግዚቢሽን ማዕከል አስታወቀ።

በኤግዚቢሽን ማዕከል የመስቀል አደባባይ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አያሌው መንገሻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የመስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ በአካባቢው የሚስተዋለውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ጥበት ችግርን ለመፍታት ታስቦ የተሰራ እና አንድ ሺህ 400 የሚደርሱ ተሽከርካሪዎችን የሚያስቆም ባለሁለት የመሬት ውስጥ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያ ነው።

በዚህም ከሐምሌ 2013 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2015 ዓ.ም ድረስ 213 ሺህ 183 በላይ መኪናዎች አገልግሎት አግኝተዋል ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ በ2015 ዓመተ ምህረት ብቻ 100 ሺህ 189 ተሽከርካሪዎች የመኪና ማቆም አገልግሎት አግኝተዋል ብለዋል።

በመኪና ማቆሚያው ኢትዮ ቴሌኮም፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ሲኖር አብዛኛዎቹ መኪናዎች እዚህ ይቆማሉ ነው ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ።



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

እንደ አቶ አያሌው ገለፃ፤ የመስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ 35 ሱቆች፣ 140 መፀዳጃና 20 መታጠቢያ ቤቶች እንዲሁም ሌሎች የቢሮ መገልገያ ክፍሎች፣ ስድስት ዘመናዊ ሊፍቶች፣ ለ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የደህንነት ካሜራዎች፣ ዘመናዊ ዲጂታል ስክሪኖች እና የእሳት መከላከያ ጭምር አለው፡፡

ሱቆቹ የኢትዮጵያን ባህል እና ቅርሶች የሚያሳዩ እና ጎብኚዎችን እንዲስቡ በሚያመች ሁኔታ የተገነቡ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ወደሠላሳ የሚጠጉ ሱቆች አገልግሎት እየሰጡ ነው ብለዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ በአደባባዩ ሃያ ሱቆች የፈጣን የምግብ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ ሲሉም ጠቅሰዋል።

የመስቀል አደባባይ ከመኪና ማቆሚያ አገልግሎት ባለፈ የዲጂታል ማስታወቂያ አገልግሎት፣ ለባዛር ዝግጅት እንዲሁም ለመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መርሃ ግብር የሚያካሂዱበት ቦታ ነው። የመስቀል አደባባይ በአሁኑ ወቅት ከ200 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር ችሏል ብለዋል።



# የበዓል ገበያ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የተለያዩ ምርቶች ወደ አዲስ አበባ እየገቡ ነው

## - ለመንግሥት ሰራተኞች በሦስት ወራት የሚከፈል ብድር አዘጋጅቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የበዓል ገበያ እና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የተለያዩ ምርቶችን በማስገባት ላይ መሆኑን የጨፌ ህብረት ሥራ ማህበር አስታወቀ:: ለመንግሥት ተቋማት ሰራተኞች በሦስት ወራት የሚከፈል ብድር ለመስጠት መዘጋጀቱንም ተቋሙ አስታውቋል::

ጨፌ ወጣቶች ሁለገብ ኃላፊነቱ የተወሰነ መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት ፕሬዚዳንት አቶ ሰኘ ኢዳሹ የጤፍ ርክክቡን ባደረጉበት ወቅት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ ማህበሩ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመሆን በመስራት ላይ ነው:: በዚህም በማህበራቱ በኩል 10 ሺህ ኩንታል የጤፍ ምርት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ገብቷል::

እንደ አቶ ሰኘ ገለጻ፤ ማህበሩ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከአምራች ገበሬው ላይ በቀጥታ በመቀበል በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በማድረስ ላይ ነው:: የገበያውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት በሚደረገው ጥረት ላይ ድርሻውን በመወጣት ላይ ይገኛል::

በማህበሩ በኩል ገበያን የማረጋጋት እና የዋጋ ግሽበትን የማስታገስ ሥራ በመሰራት ላይ መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ በከተማ አስተዳደሩ ከሚገኙ ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመሆን የዋጋ ግሽበትን የማረጋጋት ሥራ በመስራት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል::

ማህበሩ መጪውን የፋሲካ በዓል ገበያን ለማረጋጋት ከጤፍ ምርት በተጨማሪ ከ50 ሺህ በላይ የሀበሻ እንቁላል ለማቅረብ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከ35 ሺህ በላይ የፈረንጅ እንቁላል፣ ሰባት ሺህ ፍየሎች፣ በጎች፣ የእርድ ሰንጋ እንዲሁም አይብ፣ ቅቤ እና ዶሮን በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ መዘጋጀታቸውን አስረድተዋል::

በዋጋ ግሽበቱ በዜጎች እና በመንግሥት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና ለመፍጠር የሚሰሩ አካላት መኖራቸውን የገለጹት አቶ ሰኘ፤ በ15 ቀናት ውስጥ ስምንት ሺህ ኩንታል የጤፍ ምርት ወደ ከተማዋ ለማስገባት የታቀደ መሆኑን ገልጸው በአሁኑ ጊዜ ከ10 ሺህ ኩንታል በላይ ለማስገባት መቻሉን አብራርተዋል::

በተለይ የጤፍ ምርትን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ ለከተማው ህብረተሰብ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች በ121 ወረዳዎች ላይ በሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በኩል እንደሚሰራጭ ገልጸዋል::

በተጨማሪም ማህበሩ በተለየ መልኩ ለመንግሥት ተቋማት ሰራተኞች በሦስት ወራት የሚከፈል ብድር ለመስጠት የተመቻቸላቸው መሆኑን ገልጸው፤ የትኛውም መንግሥት ሰራተኛ በትስስር በሦስት ወራት በደሞዝ ክፍያ ብድር የሚሰጥ መሆኑን አመላክተዋል::

# ወጣቶች ከፀጥታ ኃይሉ ጋር በመቀናጀት የመዲናዋን ሰላም ለማስጠበቅ እንዲሰሩ ጥሪ ቀረበ

**በኃይሉ አበራ**



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- ህብረ ጠብቆ የኖረውን ሕዝብ አካላትን ለመከላከል ከጸጥታ ኃይሉ ጋር እንዲሰሩ የአዲስ አበባ አስተዳደር ቢሮ ጥሪ የአዲስ አበባ ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ዙሪያ ከመዲናዋ ነዋሪ ውይይት አካሂዷል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ፤ በመዲናዋ የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ማሳካት የሚፈልጉ አካላት ሃይማኖትን፣ ብሔርንና ሌሎች ጉዳዮችን ሽፋን በማድረግ እንደሚንቀሳቀሱ ገልጸዋል።

የመዲናዋ ወጣቶች ግጭት ለመቀስቀስ የሚጥሩ አካላትን ለመከላከል ብሎም የሀገርን ሰላም ለማስጠበቅ ከጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰሩ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ተቋማት መቀመጫ የሆነችውን የአዲስ አበባን የጸጥታ ሁኔታ ከሚያወሳስቡ ፖለቲካዊ ይዘት ካላቸው የጥፋት አጀንዳዎች በመራቅ ችግሮችን በጋራ መከላከል እንደሚያስፈልግም መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበራ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አብዛኛው የሰላምና የጸጥታ ማስከበር ስራ የሚከናወነው ማህበረሰቡ በሚሰጠው ጥቆማና ትብብር ነው።

ፀጉረ ልውጥ እንቅስቃሴዎች፣ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ ሕገወጥ ድርጊቶች የሚፈፀምባቸው አዋኪ ቦታዎች እና ሌሎችም ላይ ማህበረሰቡ የሚሰጠውን መረጃ ግብዓት በማድረግ ስለሚሰራ ወጣቱ አካባቢውን በመጠበቅ በንቃት ሊሳተፍ ይገባል ብለዋል።

ህብረተሰቡ ከሚሰጣቸው ጥቆማዎች መካከል ሰሞኑን በሕገወጥ መንገድ የተከማቸ የቴምር ምርት ወደህብረተሰቡ ሊወጣ ሲል መያዙንም ጠቁመው፤ በተመሳሳይ ህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ መሳሪያዎችና የተለያዩ ንብረቶች እንዲያዙ ምክንያት የሆነው የህብረተሰቡ ትብብር መሆኑን ገልጸዋል።

ወጣቱ የማይሳተፍበት የሰላምና ጸጥታ ስራ በአንድ እጅ ማጨብጨብ ነው። በከተማዋ ያለውን ሰላም ለማረጋገጥ ባለቤት የሚሆነው ማህበረሰቡ በመሆኑ መረጃን ለሚያመጣ አካል የሕግ ሽፋን ይሰጣል ሲሉ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ የፀጥታ የኦፕሬሽን ዘርፍ ዳይሬክተር ወይዘሮ ሮማን በቀለ በበኩላቸው፤ በከተማዋ ሕገወጥ የጦር መሳሪያ፣ ኮንትሮባንድ እና አዋኪ ድርጊቶች እየተስፋፋ በመሆኑ ወጣቱ ከፀጥታ አካላት ጋር በመሆን የከተማውን ፀጥታ ሊጠብቅ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ወጣቱ በከተማዋ በቤተ እምነት አካባቢ፣ በየትምህርት ተቋማት፣ በትላልቅ የገበያ ቦታዎች፣ በአደባባይ በዓላት በመሳሰሉት የፀጥታ ችግር እንዳይፈጠር በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የታገዘ የቅድመ ወንጀል መከላከል ስራና መረጃ በመስጠት አገራዊ ግዴታውን ጭምር እየተወጣ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በቀጣይ ወጣቶች በከተማዋ ለሁከትና ብጥብጥ መንስኤ ከሆኑ ማናቸውም ድርጊቶች ራስን በማግለል ከፀጥታ አካል ጋር ለከተማዋና ሀገራዊ ሰላም በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

# ኢፕድ ለ22ኛ ጊዜ ለኮሙኒኬሽን ባለሙያዎችና አመራሮች ሲሰጥ የነበረውን ሥልጠና አጠናቀቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለ22ኛ ዙር ለአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ከፌዴራል፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከኦሮሚያ ክልል ለተውጣጡ ለኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያዎች ሲሰጥ የነበረውን ሥልጠና አጠናቀቀ::

ሥልጠናው የተሰጠው ወቅቱ የሚፈልጋቸውን የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን፤ በቴሌቪዥንና የራዲዮ ፕሮግራም፣ የዶክመንታሪና ፕሮሞሽን ዝግጅት፣ በዜናና የዜና ሀታታ አጻፃፍ፣ በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስትራቴጂና እቅድ እንዲሁም በዲጂታል ኮሙኒኬሽን ዘርፍ እንደሆነ ተገልጿል::

በሥልጠናው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የይዘት ዘርፍ ምክትል ስራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ እንደተናገሩት፤ የሁሉም ቤት የሆነውን የኢትዮጵያን ፕሬስ ድርጅት መርጣችሁ እውቀት እንገበያለን፤ ክፍተታችንን እንሞላለን ብላችሁ በመምጣታችሁ እናመሰግናለን ብለዋል::

በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃንና የሥነ-ጹሑፍ ታሪክ ውስጥ ትልቅ አሻራ ያስቀመጠ ተቋም እንደሆነ ገልጸው፤ ላለፉት 82 ዓመታት የሀገሪቱን ሁነቶች በመዘገብና በመሰነድ ሃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን፤ ዘኢትዮጵያን ሄራልድና አል አለም ጋዜጦች



ፎቶ፡ ሳሙኤል ተስፋዬ

ላይ ስለአባይ ግድብ የጦር ሜዳ ውሎ ያህል ለኢትዮጵያ ጥቅምና ሉዓላዊነት ኢትዮጵያን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል::

ኢትዮጵያ ብዙ ችግሮች በገጠሟት ወቅት እንኳን ለአንድም ቀን የጋዜጣ ህትመትን ሳያቋርጥ ሃላፊነቱን እየተወጣ ያለ ተቋም እንደሆነ ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት ተደራሽነቱን በማስፋት ከጋዜጣ በተጨማሪ በኦንላይን ሚዲያም ተጠቃሽ ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል::

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ እውቅ የሥነ-ጽሑፍና የሚዲያ ባለሙያዎች መፍለቂያ መሆኑን የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ በዲዛይን፣ በፎቶ፣ በኦንላይንና በተለያዩ የሚዲያና በኮሙኒኬሽን ዘርፎች ተቋሙ ያካበተውን ልምድ ለሌሎች ሰልጣኞችም ለማካፈል ዝግጁ እንደሆነ ጠቁመዋል::

የስልጠናው ተካፋይና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር የሆኑት ወይዘሮ ፈትለወርቅ ደስታ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት ካለው የሚዲያ ዘርፍ መሻሻል ጋር ተያይዞ ከሥልጠናው ዘርፊ ብዙ እውቀቶችን አግኝቻለሁ:: ከዚህ በፊት በተቋማቸው በሚያከናውኑት ስራ የነበራቸውን ክፍተት መሙላት የሚያስችላቸውን እውቀት እንዳገኙና ለቀጣይ ስራቸው ተገቢውን ሙያ እንደቀሰሙ ተናግረዋል::

ወይዘሮ ፈትለወርቅ አክለውም የሚዲያ ዘርፍ ፈጣን ምላሽን የሚፈልግና በየጊዜው ተለዋዋጭ ስለሆነ እንዲህ አይነት ሥልጠናዎች መሰጠታቸው ለሙያው መሻሻል ሲባል ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም ጠቁመዋል::

ሥልጠናውን ለመካፈል ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የመጡት የኮሙኒኬሽን ባለሙያ አቶ ሳምሶን ሳሙኤል በበኩላቸው፤ ሥልጠናው አስደሳች እንደነበረ በመግለጽ፤ ዘመኑ የሚፈልጋቸውን የሚዲያና ኮሙኒኬሽን እውቀቶች በዘርፉ የረጅም ጊዜ ልምድና ችሎታን ካካበቱ ባለሙያዎች እንዳገኙ ተናግረዋል::

በተቋማቸው የሚከናወኑ ተግባራትን ወቅቱን ጠብቀው ትክክለኛውን መረጃ ተደራስያን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ በማድረግ እንዴት ማድረስ እንዳለባቸው ሙያዊ ድጋፍ እንዳገኙ አብራርተው፤ ወቅቱን የጠበቀ ሥልጠና እንደሆነ ገልጸዋል::

በሥልጠናው ማጠቃለያ ላይም የተሰጠው ሥልጠና ወቅቱ የሚፈልጋቸውን የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፎች የሚያሟላ እንደሆና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የሥልጠናው ተሳታፊዎች ጠቁመዋል::

ዜና

# “ግድቡ የደረሰበት ደረጃ ኢትዮጵያ ፍላጎቷን ማሳካቷን የሚያሳይ ትልቅ ድል ነው”

-አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ
የዓባይ ግድብ ተደራዳሪና ዓለም አቀፍ የሕግ ምሁር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ባለፉት ዓመታት የነበሩ ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁሞ አሁን የደረሰበት ደረጃ ኢትዮጵያ ፍላጎቷን ማሳካቷን የሚያሳይ ትልቅ ድል መሆኑን የግድቡ ተደራዳሪና ዓለም አቀፍ የሕግ ምሁሩ አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ ገለጹ፡፡

አምባሳደር ኢብራሂም እንድሪስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት 12 ዓመታት እንደ አገር ከባድ ጫናዎችንና የድርድር ሁኔታዎችን አሳልፈናል፡፡ የነበሩ ውጣ ውረዶችን አልፎ ግድቡ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱ ኢትዮጵያ ፍላጎቷን ማሳካቷን የሚያሳይ ትልቅ ድል ነው፡፡

ግድቡ አሁን የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ ከሕዝቡ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት የእውቀት፣ የገንዘብና የሃሳብ ድምር ድጋፍ ከፍተኛ እንደነበረ የጠቆሙት አምባሳደር ኢብራሂም፤ ይህም እንደ አገር የትኛውንም ፕሮጀክት ጀምሮ ለመጨረስ የሚያስችል ትልቅ አቅም እንዳለን ያሳየንበት ፕሮጀክት ነው ብለዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ አባቶቻችን ባቆዩልን አገርና ቅርስ እንደምንኮራው ሁሉ እኛ ለልጆቻችን የምናወርሰውና ልጆቻችን የሚኮሩበት ትልቅ ሀብት ነው ብለዋል፡፡

የታችኞቹ ተፋሰስ አገራት በተለይም ግብጽ የዓባይን ውሃ መጠቀም መብታችን እንደሆነ ሊገነዘቡት ይገባል ያሉት አምባሳደር ኢብራሂም፤ ምክንያቱም ውሃው የጋራ ውሃ ስለሆነ እንዳንጠቀም ሊከለክሉ የሚችሉበት ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የላቸውም ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ግብጽ ኢትዮጵያ የድርሻዋን ውሃ እንዳትጠቀም የምትከለክልበት ዓለም አቀፋዊ ሕግ እንደሌለ ዓለም ያውቃል ያሉት ተደራዳሪው፤ ሆኖም አንዳንድ ምዕራባውያን ፍላጎታቸው ተገደን ስምምነት ውስጥ እንድንገባና የእነሱ እስረኛ ሆነን እንድንኖር ማድረግ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በአንድ በኩል የልማታችን ደጋፊ መሆናቸውን እየተናገሩ በሌላ በኩል ደግሞ የድርሻችንን ውሃ እንዳንጠቀም የሚያደርጉት ጫና ለዚህ ጥሩ ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1959 ግብጽና ሱዳን የዓባይን ውሃ ሙሉ በሙሉ መካፈላቸውን አስታውሰው፤ በዛን ወቅት 84 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ እንዳለ ታሳቢ ተደርጎ 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ለግብጽ፣ 18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ደግሞ ለሱዳን የተሰጠ ሲሆን ቀሪውን 10 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትሩን ውሃ ደግሞ ለትነት ብለው አስቀምጠውታል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ስለዚህ ከድርሻችን ምንም ዓይነት ውሃ እንድትነኩብን አንፈቅድም ካሉ በተዘዋዋሪ የ1959ኙን ስምምነት ተቀበሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ የምታበረክተው 85 በመቶ የዓባይ ውሃ የግብጽ እንጂ የኢትዮጵያ አይደለም ማለት ስለሆነ እየታገልን ያለነው ይህንን ኢ-ፍትሃዊነት ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጥያቄ ውሃውን በጋራ አልምተን በፍትሐዊነት እንጠቀም የሚል ስለሆነ በዓለም አቀፍ ሕጎችም ምንም ዓይነት ተጠያቂነት የለብንም ያሉት ምሁሩ፤ የግብጾች አንዱ ስጋት ኢትዮጵያ ውሃ መጠቀም ስትጀምር ሌሎችም የተፋሰሱ አገሮች መጠቀም ይጀምሩና ውሃው ላይ ያለን ቁጥጥር ይቀንሳል የሚል ነው፡፡ በግብጽ በኩል እየተስተጋባ ያለው የራስ ወዳድነት አካሄድ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ መታሰብ ያለበት ውሃውን ከተፋሰሱ አገራት ጋር እንዴት በጋራ አልምተን እንጠቀም የሚል መሆን እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ኢብራሂም ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ያላት ዋንኛ ሀብት መሬት፣ ውሃና የሰው ኃይል ነው፡፡ የዓባይ ግድብም ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት የመጠቀም መብት እንዳላት ያረጋገጠችበት ነው፡፡ በመሆኑም ሁላችንም ግድቡን መጠበቅ፣ መንከባበብና ግንባታው ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድጋፋችንን አጠናክረን መቀጠል አለብን ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## “የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተሻለ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የዓለምን ኢኮኖሚ ለማረጋጋት እንደ እ.ኤ.አ 1944 የተፈጠሩ ተቋማት ናቸው፡፡

የዓለም ባንክ በአብዛኛው ለማህበራዊ ልማት የሚሆን ብድር የሚሰጥ ነው ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ አገራችን ውስጥ በነበረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በኢትዮጵያ በነበረው አለመረጋጋት እንዲሁም ዓለም ላይ ባለው የአቅርቦት ሰንሰለት መበላሸት ኢኮኖሚው በብዙ መንገድ ሊጎዳ ችሏል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ዓለም አቀፍ ተቋማት ለኢትዮጵያ የብድር ጊዜን በማራዘም ድጋፋቸውን ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከውጭ የምታገኘው ገንዘብ እስከ 2020 ድረስ ወደ 5 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ የአውሮፓ ህብረትና ሌሎች ድርጅቶች እየቀነሱ መጥተዋል፡፡ ሌሎቹም ተቋማት በነበረው የአገር ውስጥ አለመረጋጋት ምክንያት የነበረውን ብድርም ሆነ ሌሎች እርዳታዎች እየቀነሱ ያተኮሩት ሰብአዊ እርዳታ ላይ ነበር፡፡ ሆኖም ከተቋቋሙበት ዋና ዓላማ አንጻር ኢኮኖሚውን የማረጋጋት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ስለዚህ ከእነሱ ጋር ለመነጋገር የሚያበቃንን ምቹ ሁኔታ መፍጠርና የመደራደር አቅምን ማሳደግ ይገባል፡፡

አለመረጋጋቱ መወገዱ ብቻ ለድጋፍ በቂ አይደለም ያሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ እንደ አገር የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች አገሪቱን ሊያሳድጉ እንደሚችሉ ማሳየት መቻል አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ላይ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ችግር እንዳለባት የገለጹት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ መንግሥት በተለያዩ መንገዶች እየሰራባቸው ያሉ የካፒታል የገበያ ሥርዓት ለማቋቋም እያደረገ ያለውን ጥረት መደገፍ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

አገር ውስጥ ያሉ ባንኮች በሙሉ ተደምረው አንድን ግድብ ወይም መንገድ ፋይናንስን ማድረግ የሚችል የብድር ካፒታል የላቸውም፡፡ ስለዚህ የውጭ ባንኮች እንዴት መግባት እንደሚችሉ መስራት ተገቢ ነው፡፡ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት የሚደረገው ጥረት ያለብን እዳ ሊያዘዋውር ወይም ሊሰረዝ የሚችልበት መንገድ ላይ ከተቋማቱ ጋር በብቃት መደራደር አስፈላጊ ነው ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ቻይና የ19 አገሮች ዕዳ አራዝማለች፡፡ ኢትዮጵያ ዕዳ መክፈል ብታቆም በዓመት ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚሆን ገንዘብ ለልማት ስራ ማዋል ትችላለች፡፡ ስለዚህ ኢኮኖሚው ተረጋግቶ እንደገና የተሻለ ደረጃ እስኪደርስ ከሚሰጡን ገንዘብ ይልቅ ያለብንን ዕዳ ቢያዘዋውሩ ትልቅ ድጋፍ ነው ብለዋል፡፡


# የቅጥር ማስታወቂያ

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰልጣኝ የመንገደኛ አገልግሎት ኤጀንት (Trainee Customer Service Agent)

አመልካቾችን አወዳድሮ ማሰልጠን ይፈልጋል፡፡

Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA

- **የስልጠናው መጠሪያ**፡- ሰልጣኝ የመንገደኛ አገልግሎት ኤጀንት (Trainee Customer Service Agent)
- **ተፈላጊ መስፈርት**፡- በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ በሌቭል 03 ወይም 10+3 ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የትምህርት ማስረጃ ያላት/ያለው ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የወሰደች/የወሰደ
- **እድሜ**፡ 18-35 ዓመት የሆነ/ች

**የምዝገባ ጊዜ፡-**
**ከሚያዝያ 21 እስከ ሚያዝያ 24፣2015ዓ.ም**

* ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ አመልካቾች በድርጅቱ ድህረ ገፅ www.ethiopianairlines.com/AboutEthiopian/careers/vacancies በመግባት ኦንላየን መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**bole International Airport, P.O.Box 1755 Addis Ababa. Ethiopia Tel:(251-011) 617 9900, Hotline Number 6787, Fax (251-001) 661 1474**
**www.ethiopianairlines.com**

STAR ALLIANCE

Ethiopian
የኢትዮጵያ
THE NEW SPIRIT OF AFRICA


# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት



የሕዝብ ጥያቄን የሚመልሰው የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ በሆሳዕና

ገጽ 14



## ‹‹ግብጽ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ የጎዳቻት ስለመሆኑ የሚገልጽ ምንም ዓይነት ማስረጃ የላትም››

- ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ
የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ

ገጽ 6



ያልተሰበረ ልብ

ገጽ 16

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ የደረሰበት ደረጃ

ሶሎሞን በየነ

የቤት ጉዳይ አንገብጋቢ በሆነበት አዲስ አበባ የዜጎችን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ ባይቻልም ከተማ አስተዳደሩ ችግሩን በተለያየ መንገድ ለማቃለል ከተለመደው የቤት ልማት ፕሮግራሞች (10/90፣ 20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራሞች) ባሻገር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቤት ግንባታን ተግባራዊ በማድረግ በአጭር ጊዜ ግንባታቸው ተከናውኖ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚተላለፉ ተገጣጣሚ ቤቶችን ገንብቶ ለቤት ፈላጊዎች ለማስረከብ በግንባታ ላይ ይገኛል። ከነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ የአቃቂ ቃሊቲ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ተጠቃሽ ነው። የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች አጠቃላይ የግንባታ ሥራው እና አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ የሰጡንን መረጃ እንደሚከተለው አሰናድተን ይዘን ቀርበናል።

እንደ ኢንጅነሩ ገለጻ፤ የተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞችን ቀርጾ ለሚመለከተው አካል በኃላፊነት ሰጥቶ ቤቶችን የማሠራት ሥልጣኑ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ነው። ቢሮውም የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ፕሮጀክትን ቀርጾ ወደ ሥራ ካስገባ በኋላ ፕሮጀክቱን በበላይነት የማስተባበር፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠርና በጀት ጭምር አስመድቦ በማቅረብ እንዲመራ ለአዲስ አበባ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በኃላፊነት ሠጥቷል። ስለዚህ ኮርፖሬሽኑ የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታን በባለቤትነት ይዞ እያስተባበረ ይገኛል።

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጥራትና ቀነ ገደብ እንዲጠናቀቅ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል። አንደኛው ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን



ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ፤

ፋይናንስ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በጀት አጸድቆ ያቀርባል። ወይም የፋይናንስ አቅርቦት ሥራ ይሠራል። ሌላው ኮርፖሬሽኑ ግንባታው በሚከናወንበት ሳይት ላይ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከፍቶ ፕሮጀክቱን በበላይነት እያስተባበረ፣ እየመራና ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል። ከዚህ አኳያ ቀደም ሲል ወይም ከሶስት ዓመት በፊት ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሚሆን ግብዓት የሚያቀርበው መንግሥት ነበር። በዚህም በየሳይቱ በርካታ የግንባታ ግብዓት (ብረት፣ የፍሳሽና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ... ወ.ዘ.ተ ግብዓቶች) አቅርቦት ክምችት አለ። ይህን ለአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ግብዓትነት በማዋል አንድም ለፕሮጀክቱ ስኬታማነት የጀርባ አጥንት ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ በጋራ መኖሪያ ቤቶች የግንባታ ሳይት ተከማችተው ለብልሽት ሊዳረጉ የነበሩ የግንባታ ግብዓቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ተችሏል። ስለዚህ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና የግንባታ ግብዓቶችን ኮርፖሬሽኑ እያቀረበ ይገኛል።

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ ግንባታውን በባለቤትነት ስለሚመራ ከግንባታ ሥራው ጋር ተያይዞ አንዳንድ ማስተካከያዎች ሲኖሩ እንዲስተካከሉ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል። እንዲሁም የኮንትራት አስተዳደርና የሱፐርቪዥን ሥራዎችን ያከናውናል። በጥቅሉ ኮርፖሬሽኑ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን በጀት ከመመደብ ባሻገር አስፈላጊውን ግብዓት ጭምር በማቅረብ ፕሮጀክቱ በተያዘው እቅድ መሰረት እንዲሳካ ፈርጀ ብዙ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ይናገራሉ።

የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ፕሮጀክት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቤት ግንባታን ተግባራዊ በማድረግ በፈጣን የቤት አቅርቦት የከተማዋን ነዋሪ የቤት ፍላጎት ለማሟላት የታለመ ፕሮጀክት መሆኑን ኢንጅነሩ ጠቁመው፤ ፕሮጀክቱ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን፤ ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ነው ወደ ሥራ የተገባው። ሆኖም ፕሮጀክቱ በተቀመጠለት መርሐ-ግብር መሠረት እንዳይከናወን በዋናነት እንቅፋት የሆነው የወሰን ማስከበር ሥራው ነው። ግንባታው የሚከናወንበት ቦታ የይገባኛል ጥያቄ ስለነበረበት በዚህም ፕሮጀክቱ ለአንድ ዓመት ያህል ዘግይቷል። ከዚህ ባለፈ የግንባታ ግብዓት በተለይ የሲሚንቶ አቅርቦት እና የገበያ ዋጋ ንረት ፕሮጀክቱ እንዲስተጓጎል ማድረጉን ገልጸዋል።

ኢንጅነር ቶማስ፤ የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢኮሥኮ) እየተከናወነ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ ሲጀመር አምስት ሺ ተገጣጣሚ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ የተገባ ቢሆንም በሳይቱ ዙሪያ ያሉ ክፍት ቦታዎችን በማካተት ተጨማሪ አምስት ሺ ያላነሰ በድምሩ 10 ሺ ተገጣጣሚ ቤቶች በቀጣይ ተገንብቶ ለህብረተሰቡ የሚቀርብ ይሆናል። ፕሮጀክቱ አሁን ላይ ያለበት የአፈጻጸም ደረጃ ሲታይ ደግሞ በሳይቱ ላይ ካሉት 66 ብሎኮች ወይም ህንፃዎች ውስጥ ግንባታቸው እየተከናወነ ያለው 34ቱ ናቸው። የ34ቱ ብሎኮች ወይም ህንፃዎች ግንባታቸው ከ35 በመቶ በላይ መከናወኑን ተናግረዋል።

"የጋራ መኖሪያ ቤቶች በዋናነት ታሳቢ ተደርገው የሚገነቡት በነባርና በአዲስ ምዝገባ ተመዝግበው እየቆጠቡ ለሚገኙ ቤት ፈላጊዎች ነው። ነገር ግን የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ከተገነቡ በኋላ በአንድም በሌላ መንገድ ለልማት ተነሾች፣ በምደባ ወ.ዘ.ተ ይተላለፋሉ" የሚል ቅሬታ በህብረተሰቡ ዘንድ እንደሚነሳ ኢንጅነሩ ገልጸው፤ ፕሮጀክቱ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቤት ግንባታን ተግባራዊ በማድረግ በፈጣን የቤት አቅርቦት እየቆጠቡ የሚገኙ የከተማዋን ነዋሪ የቤት ፍላጎት ከመመለስ ባሻገር በከተማዋ ካለው ሰፊ የልማት ፍላጎት አኳያ ለልማት ተነሾች እንዲሁም ከተማ አስተዳደሩ በልዩ ውሳኔ ለሚያቀርበው የቤት ጥያቄ ለማስተናገድ ይረዳል። ስለዚህ ከዚህ በፊት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አንድ ህንፃ እንዲሁም በልደታ ክፍለ ከተማ ሶስት ህንፃዎች በድምሩ አራት ተገጣጣሚ ቤቶች ቴክኖሎጂን በመጠቀም በሚገርም ፍጥነት በ69 ቀን ተጠናቀው ለህብረተሰቡ ተላልፈዋል። በተመሳሳይ የአቃቂ ተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታን በፍጥነት በማጠናቀቅ የህብረተሰቡን የቤት ጥያቄ ለመመለስ የተዘረጋ አንዱ የቤት አማራጭ ነው። በመሆኑም ፕሮጀክቱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል የቤት ጥያቄን በሚመልስና ማህበራዊ ቁርኝቱን በሚያጠናክር እንዲሁም የአካባቢውን ገጽታ በሚቀይር መልኩ እየተሠራ መሆኑን ኢንጅነር ቶማስ ደበሌ ተናግረዋል።

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ግብጽ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ የጎዳቻት ስለመሆኑ የሚገልጽ ምንም ዓይነት ማስረጃ የላትም››

*- ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ*
*የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ*


ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

አስቴር ኤልያስ

ሲያስተምሩም ሆነ በፖለቲካ ሳይንሱ መስክ ሲመራመሩ (በተለይ በናይል ውሃ ጉዳይ) በታላቅ ደስታ ነው፡፡በታላቁ የዓባይ ግድብ ድርድርም ሆነ በዓለም አቀፍ ኮንፍራንሶች ላይ በአዘጋጅነትም ሆነ በተሳታፊነት ሲንቀሳቀሱ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት፤ ኃላፊነታቸውን የሚወጡት በጥልቅ አገራዊ ፍቅርና በተነቃቃ ምሁራዊ ስሜት ነው፡፡

በርካታ ምሁራንን ያፈሩ መምህር እና የሀይድሮሊክ ፓወር ፍትሐዊ አጠቃቀም ፖለቲካ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ተንታኝ በመሆናቸው በሚገባ የሚታወቁት እንግዳችን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፤ በአፍሪካ ዓለም አቀፍ ጉዳይና በፖለቲካል ሳይንስ መስክ አሜሪካ ከሚገኘው ኦሐዮ ዩኒቨርሲቲ ሁለት የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ሦስተኛ ዲግሪያቸውን (ፒኤች.ዲ) ደግሞ ስዊዘርላድ ከሚገኘው፣ ከታዋቂው ዙሪክ ዩኒቨርሲቲ በናይል ውሃ ጉዳይ፣ በፖለቲካል ሳይንስ መስክ ተቀብለዋል፡፡

እንግዳችን ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት መስክ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር፣ በመመራመርና በማማከር ሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡በተጨማሪም የፖለቲካ ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር፣ የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ዲን፤ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ፕሬስ ዳይሬክተር በመሆን የሰሩም ናቸው - የዛሬው የዘመን እንግዳችን መምህርና ተመራማሪ፤ እንዲሁም የፖለቲካል ሳይንስ ምሁሩ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ፡፡

ዶክተር ያዕቆብ የአፍሪካ፣ የእሲያና የአውሮጳ ዩኒቨርሲቲዎች የውሃና ማህበረሰብ ምርምር አባልና የኢትዮጵያ አስተባባሪ፤ እንዲሁም የሰሜንና የደቡብ አህጉራዊ ምርምር የምሥራቅ አፍሪካ ዘርፍ አማካሪ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነው ሠርተዋል፡፡የኢትዮጵያ የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ኮሚሽን አባልም ናቸው፡፡ እርሳቸው በኢትዮጵያ የጠፉ ወንዞችና የውሃ ሀብቶችን የመመለስ እንቅስቃሴ አስተባባሪም ናቸው፡፡በብዙ ደርዘን የሚቆጠሩ ሙያ ነክ የምርምርና የስርጸት ጽሑፎችንም ያበረከቱ ሲሆን፣ በአፍሪካ፣ እሲያ፣ አውሮጳ እና በአሜሪካ ተዘዋውረው ትምህርታዊ ሌክቸሮችን ሰጥተዋል፡፡የድንበር ተሻጋሪ የኢትዮጵያ ወንዞች የድርድር ጉዳይን በተመለከተ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካሪ ናቸው፡፡የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ብሔራዊ ፓናል አባልና ምክትል ፕሬዚዳንት፤ የሕዳሴ ግድቡ ብሔራዊ የድርድር ቡድን አባል፤ እንዲሁም፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ብሔራዊ ምክር ቤት አባል ናቸው፡፡ዶክተር ያዕቆብ ሰፋ ያለ ሥራና ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣታቸውን ተከትሎ ከውጭና ከአገር ውስጥ በርከት ያሉ ሽልማቶችን ማግኘት የቻሉም ናቸው፡፡ካገኟቸው በርካታ ሽልማቶቻቸው መካከል አንዱ የ2012 ዓ.ም የዓመቱ በጎ ሰው ልዩ ተሸላሚ መሆናቸው ተጠቃሽ ነው፡፡እኚህ የዛሬው እንግዳችን በዓባይ ግድብ ላይ በድርድሩም ሆነ አስፈላጊ በሆነው ተሳትፏቸው ከፍ ያለ ሚና የተጫወቱ ሲሆኑ፣ እኛ የዓባይ ግድብን 12ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በጉዳዩ ዙሪያ ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ ስላላቸው ከዶክተር ያዕቆብ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እነሆ ብለናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በግድቡ ዙሪያ የተጣለብዎትን ኃላፊነት እየተወጡ እንደሆነ ይታወቃል፤ ከግድቡ ጋር ተያይዞ ያዘኑበት አልያም የተደሰቱበት አጋጣሚ ካለ እሱን በማስቀደም ወደ ጭውውታችን እናምራ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እኔ በዚህ ግድብ በአጠቃላይ ደስተኛ ነኝ። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ከ1958 ኣ.ም ጀምሮ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ለመሥራት ጥናቶች ተካሂደው አመቺ ጊዜ እየተጠበቀ ነበር የቆየው። የተወሰኑ አነስተኛ ሥራዎች እየተሠሩ ቢቆዩም የተፈለገውን ያህል ባለመሆኑ ቅር ያሰኛል። የሕዳሴ ግድብ የዛሬ 12 ዓመት ሲጀመር ግን እጅግ የሚያስደስት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህም አገርን የሚያስከብር፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከፍ የሚያደርግ፣ ኢትዮጵያ ባላት ሀብት የመጠቀም ችሎታ እንዳላት የሚያመላክት በመሆኑ ኩራት ይሰማኛል። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ የውጭ ብድር ሳታገኝና ሳትፈልግ፤ በእሱም ሳትገደብ ኅብረተሰቡን ዳር እስከዳር አስተባብራ፤ ከመንግሥትም በጀት ተጠቅማ ይህንን ትልቅ ግድብ በብዙ ተግዳሮትም ውስጥ ሆና ቢሆንም ዛሬ ላይ መድረስ ችላለች። በየመሃሉ የተነሱ ማደነቃቀፊያዎች ቢኖሩም እዚህ ደረጃ መድረሱ እና ለማጠናቀቅም ጥቂት ጊዜ የቀረው በመሆኑ በጣም የሚያስደስት ነው።

ይህ ግድብ ተሠርቶ ሲያልቅ በዓባይም ሆነ በሌሎች ወንዞች ላይ በዚሁ መጠንም ይሁን ከዚህም ከፍ ባለ ደረጃ እንደሚሠሩ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በተደጋጋሚ ለኅብረተሰባችን ሲናገሩ ቆይተዋል። ከሁሉም በላይ የዚህ ግድብ አጀማመር እና አካሄድ እንዲሁም የዚህ ግድብ አጨራረስ ሁሉንም ችግር ተቋቁሞ እዚህ መድረስ ቁርጠኛነትንና አገራዊ የሆነ ታላቅ ፍላጎት እና ችሎታን የሚያሳይ ይመስለኛል። ይህ በጣም ያስደስተኛል። ደግሞም ተገቢ ነገር ነው። እንደማገኘውም የአጭር ጊዜ ሥራ በአንድ ዓመት በሁለት ዓመት ተሠርቶ የሚያልቅ ነገር ስላልሆነ ረጅም ጊዜና ሰፊ ትዕግስት፤ ብልሃትም የሚፈልግ ሥራ ስለሆነ ይህን ሁሉ ለመሥራት ኢትዮጵያ ያገኘችው ችሎታና ብልሃት ትልቅ ነው። ከዚህም የተነሳ የትኛውንም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ተግባር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት በተፈለገው ደረጃ እንዳልተጠቀመች ይነገራል፤ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ኢትዮጵያ ለውሃ አጠቃቀሟ ልዩ ትኩረት ልትሰጥ ይገባታል ብዬ አስባለሁ። የውሃ አጠቃቀም በእጅጉ መሻሻል ይኖርበታል። ከሁሉም በላይ እየደረቁ ያሉ የውሃ ምንጮች እንደገና እንዲጎለብቱ ማድረግም ይጠበቅብናል። እየደረቁ ያሉ ገባር ጅረቶችና አነስተኛ ወንዞች እንደገና ሕይወት መዝራትም ይኖርባቸዋል።

እንደ ሳንባ የሚያገለግሉ ጨፌዎችና የውሃ ማቆሪያዎች እየደረቁ በመሆናቸው ጥበቃ ሊደረግላቸው የግድ ይላል። በወንዞቻችን ላይ ትንንሽ (ካስኬድ) ግድቦች እየተገነቡ ለእርሻ፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ለዓሣ ሀብት ልማት እና ለጠቅላላው ሥነ ምህዳር መንከባከቢያ መዋል ይኖርባቸዋል። በኢትዮጵያ ያለው የውሃ ችግር ከውሃ አስተዳደር ድክመትና ከመሬት አጠቃቀም ጉድለት የሚመነጭ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። የገጠር መሬት ልማትም ሆነ የከተሞች ግንባታ ተገቢና ዘላቂ የውሃ አጠቃቀምን መሠረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ግብጽ ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን እንዳትጠቀም ከመገዳደሯ ጎን ለጎን ፈተናው ዓለምአቀፍ ይዘት እንዲኖረው እየጣረች ነው፤ ይህ በአገራቱ መካከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሀዊ አሠራር እንዳይሰፍን አያደርግም?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እንደሚታወቀው ግብጾች ከኢትዮጵያ ጋር የውሃ ሀብት ይጋራሉ። በተለይ ዓባይ፣ ተከዜ እንዲሁም ባሮ አኮቦ ሱዳንን ተሻግረው ከኢትዮጵያ ወደ ናይል ግብጽ ስለሚሄዱ በተፈጥሮ እኛና ግብጽ የምንጋራው የውሃ ሀብት ነው። ይህን የውሃ ሀብት በተቻለ መጠን በመተሳሰብና በመመካከር መጠቀሙ መልካም ነው። በተለይም በውሃው ላይ የትኛው አገር ምን ቢሠራ ይሻላል በሚል እቅድ በማውጣት ተጠቃሚ መሆን ይገባል። «ከውሃ የሚገኝ የኢኮኖሚ ሥርዓት ምን ቢሆን ይሻላል?» በሚል ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሱዳንም ሆነች ግብጽ፤ እንዲሁም ሌሎችም በውሃ አጠቃቀም የሚጋሩ አገሮች እቅድ እያወጡና እየተሳሰቡ በአንድ መዓዝን የግድ የሚል ነው። ለምሳሌ ብዙ በውሃ የሚለማ ልማት እንዳለ ይታወቃል። ለአብነት ያህል አንደኛው አገር ከፍተኛ የእርሻ ልማት ላይ የሚሰማራ ከሆነ ሌላኛው ደግሞ ከፍተኛ የኃይል ምንጭ ላይ ሊሠራ ይችላል። ስለሆነም በዚህ መልኩ በምክክር መሄድ ይገባል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ሀብቷን በምታለማበት ጊዜ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ልማት ግብጽን የሚጎዳ እየመሰላት ወይም ደግሞ የሚጎዳት እንደሆነ እያስመሰለች ግብጽ ብዙ ለማሳመን ርቀት ለመሄድ ሞክራለች። ይሁንና ኢትዮጵያ በውሃዋ ለማልማት በተነሳች ጊዜ ግብጽ የኢትዮጵያ ልማትና የውሃ አጠቃቀም እየጎዳኝ ነው ትበል እንጂ በዚህ በዚህ መንገድ፣ ወይም

> **በወንዞቻችን ላይ ትንንሽ (ካስኬድ) ግድቦች እየተገነቡ ለእርሻ፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ለዓሣ ሀብት ልማት እና ለጠቅላላው ሥነ ምህዳር መንከባከቢያ መዋል ይኖርባቸዋል**

ደግሞ በዚህ ሁኔታ የእኔ ልማት ተደናቀፈ የሚል ማስረጃ እስካሁን ማቅረብ አልተቻላትም። ምንም እንኳ ግብጽ ማቅረብ ባትችልም ‹‹ኢትዮጵያ ትጎዳናለች›› የሚለውን ተደጋጋሚ ሐሳብ ለሕዝቧ እንደ መሠረታዊ የፖለቲካ ትምህርት እያደረገች በፕሮፖጋንዳ ደረጃ በመግለጽ ዛሬ ላይ ደርሳለች። ለወዳጆቿም ‹‹ኢትዮጵያ ውሃዬን እየወሰደችብኝ ነው፤ ከአሁን ቀደም በአግባቡ እጠቀምበት የነበረውን ውሃ እንዳልጠቀም ኢትዮጵያ እያጠፋችብኝ ነው›› በማለት ከመናገር ቦዝና አታውቅም። ይህንን ሐሳቧን ኢትዮጵያ በሌለችበትና ባለችበትም ጭምር ከመናገር ወደ ኋላ የቀረችበት ጊዜ የለም።

ግብጽ በየመድረኩ ‹‹ኢትዮጵያ ውሃዬን እንዳልጠቀምበት እያደረገች ነው›› ትበል እንጂ ግብጽ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ የጎዳቻት ስለመሆኑ የሚገልጽ ምንም ዓይነት ማስረጃ የላትም። «ግብጽ ለምን ሰጋች?» ብሎ መናገር አይቻልም። ስጋቷ ግን መሠረት እንደሌለው መናገር ይቻላል። ስለዚህ የግብጽ ወዳጆችም ሆኑ የግብጽ ሕዝብ ‹‹ኢትዮጵያ ውሃውን በመጠቀሟ ግብጽ ተጎዳች›› የሚሉት የተሳሳተ መረጃ ስለሚደርሳቸው እና በተሳሳተ መንገድ የግብጽን ሐሳብ በመቀበላቸው ነው እንጂ ሐሳቡ ትክክል ሆኖ አይደለም። በእርግጥ ግብጽና ኢትዮጵያ በአግባቡ ውሃውን ተሳስበው ወደ መጠቀም ብልሃት ቢመጡ መልካም ነው፤ ይህ ብልህነትም ጭምር ነው። ምክንያቱም ከውሃው ለሁለቱም የሚበቃ ልማት ማግኘት ይችላሉ። ከውሃ የሚገኝ ጥቅም፣ ሀብት፣ ምቾትም ሆነ ብልጽግናም ጭምር ይገኛል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ግብጽ የዓባይ ግድብ ጉዳይ በአረብ ሊግ ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን አስደርጋለች፤ ይህ አካሄድ አረቦቹን ያልተገባ ጣልቃ ገብነት አያስመስልባቸውም? የግብጽንስ ሁኔታ እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ግብጽ ለአረብ ሊግ የግድቡን ጉዳይ ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን ማጸደቋን እርግጠኛ አይደለሁም። ይህንን ማረጋገጥ ያስፈልግ ይሆናል። በእኔ በኩል የማውቀው ቋሚ አጀንዳ እንዲሆን መጠየቋን ነው። እናም ስትጠይቅ የአረብ ሊግ አገሮች ውስጥ የኢትዮጵያም ጎረቤቶች አሉበት። እነዚህ ጎረቤት አገሮች ደግሞ ኢትዮጵያን የሚጎዳ አጀንዳ ግብጽ አቅርባ ኢትዮጵያ እንድትጎዳ ከግብጽ ጥቅም አንጻር ለዘለቄታ የሚቆሙ አይመስለኝም።

ደግሞም የኢትዮጵያ ጎረቤት ያልሆኑ አረብ አገሮችም ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነትም ብሎም ሞቅ ያለ ግንኙነትም ያላቸው ናቸው። በተለይ በንግድም ሆነ በፖለቲካ ያላቸው ከፍ ያለ ግንኙነት እንደሆነም ይታወቃል። ስለዚህ እነዚህም አገሮች ግብጽ የምትለውን በደረቁ ተቀብለው ለዘለቄታው አጀንዳው አጀንዳችን ነው ብለው ከያዙ የተሳሳቱ ይሆናሉ ማለት ነው።

ሌሎች ለግብጽ እጅግ በጣም ይቀርባሉ የሚባሉት አረብ አገሮች እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ትልቅ አገር፣ ያውም ለአካባቢው ብዙ ጥቅም የምትሰጥ፣ በኢኮኖሚም በፖለቲካም ልትከበር የሚገባት ሆና ሳለ የመከባበርን መስመር ሊያበላሽ የሚችልን መንገድ በዘለቄታ ተከትለው ከግብጽ ጋር የሚያብሩ አይመስለኝም። በእርግጥ ግብጾች አባል በሆኑበት በአረብ ሊግ በእነሱ ከተማ ተቋቁመው በብዛት በግብጽ ፖለቲከኞች የሚስተናገድና የሚመራ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ግብጽ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ የጎዳቻት ...

የአረብ ሊግን ቀርቶ በአውሮፓና በአሜሪካም እየዞሩ አገራቱ የግብጽን ፖሊሲና ፕሮፓጋንዳ ተከትለው ኢትዮጵያ ላይ ዱላ እንዲያነሱ ሁሉ ግብጽ ስታግባባ እንደቆየች የታወቀ ነው::

እንዲያም ሆኖ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ልማት ጉዳይ የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ ለመጥቀም፣ የኢትዮጵያን ልማት ከፍ ለማድረግ፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መብትና ጥቅም ለማስከበር ነው። ስለሆነም ግብጾች በአረብ ሊግም ሆነ በሌላ ቦታ በኢትዮጵያ ላይ የሚያጠነጥኑት አሉታዊ የሆነ ፕሮፖጋንዳም ሆነ የማሳሳት ዘመቻ መሠረት አይኖረውም። ኢትዮጵያ፣ ግብጽን ለመጉዳት አስባ ሳይሆን ልማቷን በቁርጠኝነት ለማሳለጥ በጥንቃቄ በመሥራት ላይ ትገኛለች:: እንዲሁም ምንም እንኳ ሦስተኛ ወገን ከግብጽ ጋር ቢያብርም የጋራ ውሃ እንደመሆኑ መጠን ግብጽም በከፋ ሁኔታ እንዳትጎዳ ጥንቃቄ በመውሰድ ኢትዮጵያ ውሃውን መጠቀም ትችላለች:: ይህንን መብቷን ደግሞ ሊከለክላት የሚችል ኃይል አይኖርም::

ኢትዮጵያ በግብጽ ላይ የኢኮኖሚም የማህበራዊም ጉዳት አምጥታለች ወይም ደግሞ ኑሮዋ እንዲስተጓጎል አድርጋለች የሚባል መረጃ እስከሌለ ድረስ በውሃ ሀብቷ መጠቀም አጠያያቂ አይሆንም። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚያበላሽ አይመስለኝም:: ለጊዜው ፕሮፓጋንዳው የሚያሳስት እንኳ ቢሆንም አገሮች በራሳቸው ነፃ በሆነ መንገድ ሁኔታውን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ የሚል አተያይ አለኝ:: እነሱም ቢሆኑ የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ከኢትዮጵያ ጋር ጠላትነት የሚፈልጉ አይመስለኝም:: ስለዚህም የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት የሚያበላሽና ዘለቄታ ያለውን ስህተት ግብጽ ልትሠራ የምትችል አይመስለኝም::

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የግብጽ አካሄድ፣ በተለይ ቀደም ብሎ የተቀመጠውን ‹‹ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ›› የሚለውን መርህ የሚጻረር ነው። በመሆኑም ግብጽ በኅብረቱ ያለመተማመኗ ምክንያት ምን ይሆን?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እንደሚታወቀው ግብጽ ምንም እንኳ በመልክዓምድራዊ አቀማመጧ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ የምትገኝ ብትሆንም በባህልም ሆነ በኢኮኖሚ እንዲሁም በታሪክም ሆነ በፖለቲካ ተያያዥነቷ በአብዛኛው ወደ አረቡ አተኩራ የምትሠራ አገር ናት። በሌላ በኩል ደግሞ የአፍሪካ አገሮች ግብጽ ላይ የሚያመጡት ተጽዕኖ ከባድ ነው ብላም ስለማታስብ ልክ እንደማናቸውም የአውሮፓ እና የሰሜን አሜሪካ አገራት ሁሉ አፍሪካውያን መፍትሔ ማምጣት አይችሉም የሚል አተያይ ስላላት ይሆናል:: በተለይ የአፍሪካ የፖለቲካ መሪዎች የአፍሪካን ችግር መፍታት የሚያስችል ቁመና ያላቸው ናቸው ብላ ስለማታምንም ጭምር ነው:: ስለዚህ አፍሪካዊት አገር እንደመሆኗ የውሃ ሀብቷ ከአፍሪካ ውሃ አመንጪ አገሮች ጋር የሚያያይዛት መሆኑን እንኳ ብትረዳ ተጽዕኖ ለመፍጠር ከአፍሪካ ውጪ ካሉ ኃይሎችና አገሮች ጋር በአፍሪካ ላይ ለመሥራት እንደዋና አማራጭ አድርጋ ስትንቀሳቀስ ቆይታለች::

በዚህ በሕዳሴ ግድብ ጉዳይ በግብጽ በኩል ብዙ ተቃውሞ ተነስቶ በኢትዮጵያ በኩል ብዙ ማብራሪያዎች የተሰጡበት ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ ሰነዶችም እየቀረቡ ውይይትም እየተደረገባቸው ነው። ይህ ባለበትም ጊዜ ከዓለም መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት እና ከአፍሪካ ውጪ ካለው ሒደት ኢትዮጵያ ሐሳብ አቅርባ የአፍሪካ ጉዳይ መፈታት ያለበት በአፍሪካ ነው ብላ ወደ አፍሪካ ማምጣት ችላለች:: ይሁንና ኢትዮጵያ ጉዳዩን ወደ አፍሪካ መድረክ ካመጣችው ወዲህ ግብጽ በአፍሪካ መድረክ ላለመገኘት እግሯን እየጎተተች ቆይታለች:: በመሆኑም ከኢትዮጵያ ጋር አግባብነት ያለው ውይይት አሊያም ረብ ያለው ንግግር አድርጋ ‹‹ችግሬ ይህ ነው፤ መፍትሔውም ይህ ነው›› ብላ ልታቀርብ አልቻለችም። ስለዚህ የአፍሪካ መድረክ ለግብጽ የሚመች አይደለም። ምክንያቱም ግብጽ የምትፈልገው ሌሎች ዜሮ እርሷ ደግሞ ሙሉውን ማግኘት ነው:: ስለዚህ የአፍሪካ መድረክ ለግብጽ አመቺ አይሆንም። ምክንያቱም የአፍሪካ አገሮች ትክክለኛውን ነገር አመዛዝነው የኢትዮጵያ መብትና ጥቅም እንዲታይ፣ ግብጽም በከፋ መንገድ ያልተጎዳች ስለመሆኗ አመዛዛኝ የሆነ ነገር መመልከታቸው አይቀርም ብላ ታስባለች:: ደግሞም በአፍሪካ መድረክ የሕዳሴ ግድብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከግብጽ በኩል የረባ ማስረጃ በማቅረብ የተጎዳችበትን ማሳየት ስላልቻለች እሷ የምትፈልገው ውሳኔና ድጋፍ ከአፍሪካ መድረክ እንደማይገኝም አውቃለች:: ስለዚህ አጽንዖት ሰጥታ አረብ አገራት ወዳጆቼም ዘመዶቼም ናቸው በማለት ከእነርሱ ጋር ለመስራት ትፈልጋለች::



**አዲስ ዘመን፡- በአገራቱ መካከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያለውን ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት የተሻለው አማራጭ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ውሃ የሚጋሩ አገሮች ውሃውን በየአገሩ አግባብነት ባለው መንገድ መጠቀሙ መልካም ነው:: የአገሩ፣ የመሬቱና ውሃውን ለማልማት ያለው አመቺ መልክአምድራዊ አቀማመጥ ከግምት ውስጥ ገብቶ ቢሠራበት የተሻለ ይሆናል:: የአየር ሁኔታውም በሚያመች መንገድ ስትራቴጂክ የሆነ እቅድ አውጥተውና ሥራ ተከፋፍለው ቢሠሩ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው:: ለምሳሌ አንዱ አገር በውሃ ልማት ላይ ቢያተኩር፤ ሌላው አገር ደግሞ በኃይል ማመንጨቱ ቢሠራ ጥሩ ነው። እያንዳንዱ አገር በውሃ ልማት የሚገኝ ጥቅም በተለያየ አመቺ በሆነ መንገድ፤ አገሮች በገበያ መርም ሆነ በሌላ በኩል ሊዳረሳቸው በሚችል አካሄድ ለመጠቀም ቢያቅዱ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው::

ኢትዮጵያ የመብራት ኃይል ለማመንጨት የመሬት አቀማመጧና የውሃ ፍሰቷ በጣም አመቺ ስለሆነ የሕዳሴ ግድብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ግድቦች መሥራት ትችላለች:: ከዚህ ቀደም በዋቤ ሸበሌም ላይ እንዲሁም በዓባይ ላይ በርካታ ልማቶች ተሠርተዋል:: በኦሞም፣ በግቤ ላይም እየተሠራ ነው ያለው:: በዓባይ ገባርና በተከዜም ላይ እንዲሁ እየተሠራ ይገኛል:: ይህ ሁሉ የመብራት ኃይል የመሬቱ ሁኔታ አመቺ ስለሆነ ነው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ ኃይል የማመንጨት አቅም እንዳላት ስለመሬቱ ሁኔታም ስለ ውሃ ፍሰቱም ብዙ አዋቂዎች የደረሱበት ጉዳይ ነው:: እናም አሁን በጀመረችበት እውቀትና ልምድ የበለጠ ብታመርት ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ታዳሽ ኃይል እና በተሻለ ዋጋ የሚገኝ ኃይል ከማግኘቷ በተጨማሪ ለግብጽም፣ ለሱዳንም ሊዳረስ ይችላል::

ሱዳን ውስጥ ደግሞ ሰፊ የእርሻ ቦታ አለ። እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ውሃ አጠር ናቸው:: የሚያመርቱት ሰብልና ከእርሻ ጋር የተገናኙ ብዙ ነገሮች በገበያ መርህ ለኢትዮጵያም ለግብጽም ሊዳረስ ይችላል:: ስለዚህ የትኛው የውሃ አጠቃቀም የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፤ በምን ዓይነት አደረጃጀት ቢሆን የተሻለ ጥቅም ሊሰጥ ይችላል የሚለው የመተሳሰብ መንገድ መሆን የሚችል ነው:: ስለዚህ የሥራ ክፍፍል (ዲቪዥን ኦፍ ሌበር) የሚባለው ወይም ደግሞ እያንዳንዱ አገር የሚሠራውን የውሃ ልማት አንጻራዊ ጥቅማቸውን (ኮምፓራቲቭ አድቫንቴጅ) ጠብቀው ከሠሩ አንዱ አገር የሌላው አገር የውሃ ልማት ደጋፊ ነው እንጂ ተጻራሪ አይሆንም::

ከእያንዳንዱ አገር የሚገኝ የውሃ ልማት ፋይዳ ለሌሎች አገሮችም ሊዳረስ የሚችልበትን መንገድ አብሮ ማቀድ እና አብሮ መተሳሰብ፤ ይህንንም የበለጠ ከፍ ለማድረግ በተቻለ መጠን ስትራቴጂ ተዘርግቶ ለዚህም የሚሆን እውቀት፣ ስልጠና በቅርብ እየተመካከሩ ልማቱን ሊያሳልጡ ይችላሉ። በመሆኑም ዘለቄታ መፍትሄ ሊመጣ የሚችለው በዚህ ዓይነት አግባብ ሲሠራ ነው አገሮች በውሃ ሀብቱ አብረው ሊጠቀሙ የሚችሉት። ግጭት በሌለበት መንገድ እየተስማሙ እየተመካከሩ የሚጠቀሙት በዚህ ነው::

በጋራ ውሃ የጋራ አስተዳደርም ያስፈልጋል። በጋራ የሚያስተሳስር የሕግ መሠረትም ያስፈልገዋል:: እነዚህ ደግሞ በስምምነት የሚደረጉ እንጂ አንዱ አገር ‹‹ይኸውላችሁ! ሕግ ሠርቻለሁ፤ እናንተንም ይገዛል›› ሊል አይችልም:: ወይም ደግሞ ‹‹ይኸውላችሁ! ውሃ የሚተዳደርበትን ተቋም አበጅቻለሁ፤ ለእናንተም ጥሩ ነው›› ሊል አይችልም:: አሊያም ደግሞ ‹‹በውሃ እውቀት እኔ እስካሁን ሠርቼበታለሁ፤ እናንተ በዚህ ሥሩበት›› ብሎ ሊያዝ አይችልም:: እነዚህ ነገሮች ሁሉ በመመካከርና በመተሳሰብ እውቀትንና ፍላጎትን በማቀናጀት የሚሠሩ ሥራዎች ናቸው:: በመሆኑም አገሮች ለወደፊት ተፈጥሮ በአንድ ላይ በውሃ አማካይነት ያስተሳሰራቸው እንደመሆናቸው መጠን ልማታቸውም መሆን ያለበት በትብብር ነው:: አገሮች ሌላውን አገር በመግፋት ለራሳቸው ብቻ በሚጠቅም መንገድ መጓዝ አይችሉም። የሚያስኬደው ይህ ዓይነት ሁኔታ ሳይሆን በአንድ ላይ በትብብር የሚሠሩበትን መድረክ በማመቻቸት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- 12ኛ ዓመቱን የያዘው ታላቁ የዓባይ ግድብ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። በእስካሁኑ ሒደት ያጋጠመው ተግዳሮት ሰፊ እንደሆነም ይነገራል። በእርስዎ አተያይ በጣም ከባድ ተግዳሮት ነበር የሚሉት የትኛውን ነው?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እኔ እንደተከታተልኩት ከሆነ በታቀደበት መሠረት ሊሠራ እንዳይችል በመካከል አደናቃፊ የሆኑ ሁኔታዎች ተፈጥረውበት ነበር:: ስለዚህ ተስተጓጉሎ በመቆየቱ በጊዜም ሆነ በሀብት፤ እንዲሁም ደግሞ ፕሮጀክቱ በመዘግየቱ ባመጣው በሞራልም የሚጎዳ ነገር ነው ያጋጠመው:: ይህ ትልቅ ችግር ይመስለኛል:: ነገር ግን ያ በመሃል የመጣ ተግዳሮት በኋላ ላይ ተደርሶበት በተለይ በለውጡ አስተዳደር አማካይነት ማስተካከያ ተደርጎበት እንደገና ማንሰራራት መቻሉ የሚዘነጋ አይደለም:: በአዲስ ጉልበት በቴክኒክ የነበሩ ችግሮች ተስተካክለው በገንዘብም የነበረው ክፍተት ከግምት ገብቶ እንደገና በተጨማሪ ወጪና በጀት የኅብረተሰብም እርዳታ ታክሎበት በአሁኑ ሰዓት ጥሩ መስመር ለመያዝ በቅቷል። ወደ ማጠናቀቂያውም እየተቃረበ መሄዱ የሚያስደስት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ግብጽ "በዓባይ ግድብ ዙሪያ ሁሉም አማራጮች ክፍት ናቸው የማለቷ አካሄድ እንደማስፈራሪያ የሚቆጠር ነው' የሚሉ አሉ፤ የግብጽ አካሄድ ይህ ከሆነ ደግሞ ሦስቱም የተፈራረሙትን የመርሆዎች ስምምነት፣ እንዲሁም የአፍሪካን ህብረት ድንጋጌ የሚጥስ አይሆንም?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** በየጊዜውና በየዘመኑ ግብጽን ለማስተዳደር የሚመጡ መሪዎች የኖሩት ውሃ አመንጪ አገሮችን፣ በተለይ ኢትዮጵያን ‹‹ውሃውን ከነካሽ ወየውልሽ›› ሲሉ ነው:: ኢትዮጵያ ትልቅ ግድብ እየገደበች እነሱ ደግሞ ግድቡን የሚያስቆሙ እየመሰላቸው እዚህ መድረስ ተችሏል:: ኢትዮጵያ ደግሞ ይህ ግድብ የሚጠቅመኝ ስለሆነና ልማቴን ከፍ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በገዛ ግዛቴ ውስጥ ብሎም በገዛ ገንዘቤ የምሠራው ግድብ ስለሆነ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነኝ እያለች ነው:: በተለይ ማንንም በከፋ ሁኔታ ሳልጎዳ እያካሄድኩ ያለሁት ግድብ ስለሆነ ግብጽም ሆነች ሌሎቻችሁ ይህንን ካልተረዳችሁ እንድትረዱ እጠይቃለሁ በማለት ላይ ናት። ከተረዳችሁ ደግሞ የማይሆን ጨዋታ ውስጥ አትግቡ ስትልና ስትመክርም ቆይታለች::

ስለዚህ ግብጾች አሁን ብቻ ሳይሆን ሁሉም አማራጭ ጠረጴዛ ላይ ነው ያለው በማለት ቆይተዋል:: እንዲሁም ሁሉም አማራጭ በእጃችን ነው ያለው፤ ሁሉንም አማራጭ ከመጠቀም ወደ ኋላ አንልም ሲሉ ሰንብተዋል። ባለፉት 12 ዓመታት ከኢትዮጵያ ጋር በተቻለ መጠን ለመወያየት ተሞክሮ ስምምነት ባይኖርም ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የቆየችው እየተነጋገረች ነበር:: በእርግጥ ሱዳን አንዴ ኢትዮጵያ ዘንድ አንዴ ደግሞ ግብጽ ዘንድ ወዲህ ወዲያ እያለች ብትቆይም ኢትዮጵያ ግን እየተወያየች እዚህ ደርሳለች:: ግብጽ ኢትዮጵያ ሌሎች ግድቦችንም በዓባይ ላይ እንዳትሠራ፤ የሠራችም እንደሆነ ግብጽን እያስፈቀደች እንዲሆን ነው ምኞቷ:: ይህንን ምኞቷን በጉልበት ለመጫን ብዙ ፍላጎት አላት:: የቅርብ ጊዜ አባባሏ ትርጉሙ በሌላ አገር ላይ «ሁሉም አማራጭ አለ» ሲባል ጦር ማዝመትንም ይጨምራል እንደማለት ነው። ይህ ደግሞ እስካሁን ሊደረግ አልተቻለም:: ቢደረግም አይቻልም:: አይገባምም:: ሐሳቡም ጭምር የተሳሳተ ነው:: ስለዚህም ልማዳዊ አባባል ነው የሆነባቸው:: እንኳን ይህንን ግብጾች መረር ያለ ቀልድ ሲያምራቸው ሁሉም አማራጭ በእጃችን ነው ይላሉ:: ነገር ግን ሁሉም አማራጭ በእጃቸው እንደሌለ የታወቀ ነው፤ ለወደፊትም አይኖራቸውም ብዬ አስባለሁ::

የጋራ ውሃ ላይ የምታደርጉት ልማት ይጎዳናል ካሉ ጉዳቱ የሚደርስ መሆኑ ከተረጋገጠ ያንን ጉዳታቸውን ማሳየትና ለእሱ መፍትሔ በሚሆን ነገር ላይ መነጋገር ያሻል:: ስለዚህ እንዲያ ማለቱ ኢትዮጵያን የሚያሸማቅቃት አይደለም:: ግብጾች፣ የሕዝባቸውን ጥቅም ለማስከበር ኢትዮጵያ ውሃ ላይ የምትሠራውን ፕሮጀክት ተቃውመዋል፤ አሁንም እየተቃወሙ ነው:: ሲፈልጉም የግብጽን ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ ሁሉንም አማራጭ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ይናገራሉ:: ይህ ለሕዝባቸው የሚያቀርቡት ፕሮፓጋንዳ ይመስለኛል። የሚፈጽሙትና ሊፈጽሙት የሚገባ ነገር አይመስለኝም::

የአፍሪካ ኅብረትም ሆነ መመሪያው አገሮች ጉዳያቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከሌሎች አገሮች ጋር በመመካከር እና አስፈላጊም ሲሆን በመደራደር መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ እንጂ አንዱ ሌላውን በማስፈራራት እንዲሆን የሚል መንፈስ የለውም:: ሌላው ግብጽ፣ ኢትዮጵያና ሱዳን እኤአ በ2015 ካርቱም ላይ የፈረሙት የመርህ ፊርማ ነው:: ይህ የመርህ ፊርማ አንደኛ ኢትዮጵያ ግድቧን እንዳትገነባ የሚከለክል ምንም ዓይነት ሕግ ፊርማው ውስጥ የለም:: ሁለተኛ ኢትዮጵያ ግድቧን ግንባታውን እያካሄደች መሙላት ትችላለች የሚል በመርህ ስምምነቱ ውስጥ አለ:: ሌላው በመካከላቸው ለምሳሌ ግብጾች ተጎዳንበት የሚሉት ነገር ካለ በጉዳዩ ዙሪያ በመመካከር እና በመስማማት ይጨርሱት እንጂ ከዚያ ውጪ በሆነ መንገድ አገሮች እርምጃ እንዲወስዱና አንዱ ሌላውን እንዲያስፈራራ የሚያመላክት ምንም ነገር የለም::

ስለዚህ፣ ግብጾች አሁን የሚያደርጉት ማስጠንቀቂያ እና ዛቻ ያንን መርህ ጭራሽ ወደ ጎን የተወና የአፍሪካ ኅብረትም አገሮች በሰላማዊ መንገድ ጉዳያቸውን ከሌሎች አገሮች ጋር በመከባበር ይፈጸማሉ የሚለውንም ወደ ጎን የገፉ ነው:: በመሆኑም፣ በማስፈራራት የሚፈጽሙት ነገር የለም የሚል መርህ አለ:: ግብጽ ግን ከዚህ ሁሉ መርህ ውጪ ናት ብሎ ማሰብ ይቻላል:: ግብጽ በቅርቡ ያሰማችው ዛቻ ሕገ ወጥም ዲፕሎማሲያዊ አካሄድን ያልተከተለ ብሎም ወዳጅነትን የማያከብር እንዲሁም ጉርብትናንም ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ የተሳሳተ ይመስለኛል::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ::

## ማህደረ ጤና

# ፆምና የጤና በረከቶች

**እፀገነት አክሊሉ**

የሰው ልጅ መፆምን መቼ እንደጀመረ እርግጠኛ ሆኖ የሚናገር ተመራማሪ ሳይንቲስት ባይኖርም፣ የኃይማኖት አባቶች ግን ፆም በመጀመሪያው ሰው በአዳም እንደተጀመረ ያስተምራሉ። ዘመኑና ምክንያቱ ይለያይ እንጂ አብዛኞቹ ኃይማኖቶች ተከታዮቻቸው እንዲፆሙ ይመክራሉ፤ አልያም ያስገድዳሉ።

ፆምን መፆም ከአንድ ምዕመን የሚጠበቅ ግዴታ ነው ቢባልም፣ ከመፆም የሚገኘው ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ጥቅም ከኃይማኖት ኃይማኖት ይለያያል። በአብዛኛው ከዓለማዊ ክፉ ሥራ ለመራቅ፣ መንፈሳዊ ፀጋን ለመላበስ፣ ምድራዊ ኃጢያትን ለማሠረይ እንዲሁም የተለያዩ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ጥቅሞችን ለማግኘት አስፈላጊ እንደሆነ ይነገራል፤ ይታመናልም።

‹ሬድ ኢንዲያን› ከሚባሉት የጥንት የአሜሪካ ነዋሪዎች በባሕላቸው መሠረት ከሚፆሙት ፆም አንስቶ፣ የተለያዩ ኃይማኖቶች እንደ አንድ መስፈርት አድርገው ጊዜና ሥርዓት ተበጅቶለት የሚከናወን በርካታ ዓይነት ፆም አለ። በአንዳንድ እምነቶች ምዕመኑ እንደፈለገ በአሰኘው ጊዜና መንገድ ከፍላጎቱ በመቆጠብ የሚፆማቸው ዓይነቶች ቢኖሩም፣ በአብዛኛው ግን ተመሳሳይ ይዘት አላቸው።

እድሜ ልካቸውን ሥጋ ነክ ነገሮችን ከመብላት ተቆጥበው ከሚኖሩት የሒንዱ እምነት ተከታዮች ጀምሮ፣ ምግብ ሳይመርጡ የሚበሉ፣ ሰዓት በማራዘም የሚፆሙ እንዲሁም ሁለቱንም ጊዜንና የሚበሉትን ዓይነት መርጠው የሚያከናውኑ አሉ። በአንድ እምነት ተከታዮች ዘንድም ልዩነት ያላቸው ዓይነትና የጊዜ ምርጫ ቢኖሩም፣ በአፈፃፀምና በሚመርጡት የምግብ ዓይነት ግን በአብዛኛው ተመሳሳይ እንደሆነ ይታወቃል።

የአይሁድ፣ የኦርቶዶክስ፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ፣ የሒንዱ፣ የቡዲሒዝምና የሌሎች እምነት ተከታዮች ሕግና ሥርዓት ባለው መንገድ ወጥ በሆነ ሒደትና ጊዜ ይፆማሉ። የእምነቱ ተከታዮችም ከሚታዘዙት ዋና ዋናዎቹ አፅዋማት በተጨማሪ፣ በግላቸው ሱባዔ ለመያዝ አልያም ከሠሩት ኃጢያት ለመንፃት ታዘውም ሆነ በፍላጎታቸው መፆም ይችላሉ። መፆምን የሚከለክል ኃይማኖትም ሆነ የፍልስፍና አስተሳሰብ እስካሁን ስለመኖሩ የተሠማ ነገር ባይኖርም፣ በአብዛኛው ጠቃሚነቱ ለነፍስ እንደሆነ ስለሚታሰብ ለመንፈሳዊ ተጋድሎና ጥቅም ብቻ የሚፆም ተደርጎ ይወሠድ ነበር።

ከሰሞኑ ይፋ የተደረገ ሳይንሳዊ የጥናት ውጤት ግን፣ ፆም ለነፍስና ለመንፈሳዊ እርካታ ብቻ ሳይሆን፣ ለዓለማዊ ኑሯችን ለሥጋችንም ጭምር እንደሚጠቅም የተረጋገጠበት ነው። መፆም ራስን ማድከምና ለበሽታ ማጋለጥ እንደሆነ በተለምዶ ጥቂቶች ይናገሩ የነበረውን አስተሳሰብ ውድቅ ያደረገው ይህ የጥናት ግኝት፣ ሁሉም ሰው በፆመ ቁጥር ጥርት አድርጎ ማሰብን ጨምሮ ጤናማ ስሜት እንዲሰማውና መንፈሳዊ እርካታን በአንድ ላይ ማግኘት እንደሚችል ያመላከተ ነው።

ፆም ከክፉ ምግባር የምንርቅበት ብቻ ሳይሆን ከበሽታና ከመጥፎ አስተሳሰብ የሚከለክል እንደሆነም ተመራማሪዎቹ ይናገራሉ ። በሳይንሳዊ መንገድ፣ አንድ ሰው ሲርበው ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማውና ምን ዓይነት የፀባይ ለውጥ እንደሚያመጣ ማወቅ ይቻላል። ውስጣዊ የሰውነት ለውጦችን እንዲሁም ውጫዊ ልዩነቶችን በማጥናት ምን ጥቅም እንደሚያስገኝ መለካት ይቻላል። እንደተመራማሪዎቹ ዕይታ፣ በፆም ውስጥ ያለ ሰው ከሚሰማው እርካታ በተጨማሪ፣ ረጋ ብሎ ማሰብ እንዲችል እና ብልሃት እንዲኖረው ያደርጋል።

ከአሪስቶትል ዘመን ጀምሮ መፆም ለጤና ይጠቅማል ስለሚባል ታማሚዎች በተለይ ከቀዶ ጥገና በፊት እንዲያከናውኑት ይመከር ነበር። አሁን

> **ከሰሞኑ ይፋ የተደረገ ሳይንሳዊ የጥናት ውጤት ግን፣ ፆም ለነፍስና ለመንፈሳዊ እርካታ ብቻ ሳይሆን፣ ለዓለማዊ ኑሯችን ለሥጋችንም ጭምር እንደሚጠቅም የተረጋገጠበት ነው:: መፆም ራስን ማድከምና ለበሽታ ማጋለጥ እንደሆነ በተለምዶ ጥቂቶች ይናገሩ የነበረውን አስተሳሰብ ውድቅ ያደረገው ይህ የጥናት ግኝት፣ ሁሉም ሰው በፆመ ቁጥር ጥርት አድርጎ ማሰብን ጨምሮ ጤናማ ስሜት እንዲሰማውና መንፈሳዊ እርካታን በአንድ ላይ ማግኘት እንደሚችል ያመላከተ ነው**

ድረስ ለሚጥል በሽታም ሆነ ምግብ አልፈጭ እያለ ለሚያስቸግራቸው ፆም እንደሚጠቅም ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለስኳር በሽተኞች፣ ለልብ ሕሙማን እና ለሪህ ታማሚዎች ሕክምና እንደሚያግዝም ተመራማሪዎች ይናገራሉ።

ከዓመታት በፊት ስለፆም የተደረጉ ጥናቶች እንደጠቆሙት፣ ሰውነት ምግብ እንዲያጥረው በተደረገ ቁጥር፣ እንዲሁም ከፍተኛ ካሎሪ ያላቸው ፕሮቲን ነክ ምግቦችን ትተው ወደ ካርቦኃይድሬት በማዘውተር ሰዎች አመጋገባቸውን ከቀየሩ ሰውነታቸው ውስጥ የሚፈጠር ኬሚካል ደስተኛ እንደሚያደርጋቸው ነው። ‹ኢታኖል› የተሰኘውን አልኮል ከመውሰድ ጋር እምብዛም ልዩነት የሌለው ደስታ ይሰጣል ብለው ሳይንቲስቶቹ ቢናገሩም፣ የኃይማኖት መሪዎች ግን ‹ሐሴት› ብለው የሚጠሩትን ውስጣዊ ደስተኛነት እንደሚያጎናፅፍ ይናገራሉ።

‹ኒውትሪየንትስ› በተሰኘው የሆላንድ መጽሔት ላይ ስለፆም ጠቃሚነት በወጣ የጥናት ውጤት ላይ እንደተገለፀው፣ ቢያንስ ለስድስት ወራት እያቆራረጡ የሚፆሙ ሰዎች ስሜታቸው ጥሩ እንደሚሆን ተረጋግጧል። ይህ ዓይነት ጥናት ሲካሄድ የመጀመሪያው ሳይሆን ከዚህ በፊት መሠል ጥናቶች በቻይና እና በተለያዩ ሀገራት ተካሂደዋል። የተለያዩ ኃይማኖቶች የሚያደርጉትን የፆም ሒደት በመከተል ጥናት ተደርጎ እንደሚታመነው፣ ፆም ለነፍስ ብቻ ሳይሆን ለሥጋም/ለሰውነትም ጠቃሚ እንደሆነ ተነግሯል።

በጥናት እንደተረጋገጠው ፆም ሰዎች ድብርት እንዳይሰማቸው፣ እንዳይናደዱ፣ ውጥረት እንዳይሰማቸው፣ ግራ መጋባት እንዳያጋጥማቸው ከማድረጉ ባሻገር፣ አእምሮ ውስጥ ‹ዶፓሚን› የተሰኘው ንጥረ ነገር እንዲመነጭ በማድረግ በተለይ ዕድሜያቸው በገፋ ሰዎች ላይ የደስታ ስሜት እንዲመጣ ያደርጋል።

ይህ የፆም ጥቅም ከሰው ሰው የተለያየ ስለሆነ፣ በባለሙያዎች ዘንድ አሁንም አከራካሪ እንደሆነ ይነገራል። ከፆም ዓይነቶችና መንገዶች አኳያ የሚያመጣው ተጽዕኖም የተለያየ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን፣ በአብዛኛው ግን አሁን እንደተጠናው ጠቃሚነቱ ላይ ይስማሙበታል።

በአንጻሩ ብዙዎች ፆም የሚያስገኘው ጥቅም ላይ ቢስማሙም፣ ጥቂቶች ደግሞ የማይቆይና የማይዘልቅ ስለሆነ በተከታታይ መሆን እንዳለበት ይናገራሉ። መፆም ማለት ራስን ከአቅም በላይ ማስራብ እንዳልሆነ የሚናገሩት ተመራማሪዎቹ፣ ጉዳት እንዲያስከትል ሳይሆን ሰውነትም ሆነ መንፈስ እንዲጠቀምበት መሆን አለበት ይላሉ።

ፆም የማሰብ ብቃትን እንደሚያጎለብት የሚናገሩት ሳይንቲስቶቹ፣ ንጹሕ የሆነ አዕምሮ ይፈጥራል፣ ያለምንም ውጥረት ጥሩ ጥሩ እሳቤዎች እንዲኖሩ ያደርጋል ይላሉ። በመደበኛነት የሚፆሙና የካሎሪ መጠናቸውን የሚገድቡ ሰዎች ደግሞ የበለጠ ጤናማ ከመሆናቸው ባሻገር፣ ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር ቶሎ እንዳይገረጅፉ ያደርጋቸዋል ተብሏል። ይህም ብቻ ሳይሆን ፆም የማስታወስ ብቃትን ለመጨመርም እገዛ እንደሚኖረው መታወቁ ተነግሯል። ለመርሳት በሽታ ሕክምናም ሊያገለግል እንደሚችል ጥቆማ የተሰጠ ሲሆን፣ ለወደፊቱ በምርምር የሚረጋገጥ ይሆናል ሲሉ አሳውቀዋል።

ለረጅም ጊዜ ሳይበሉ መቆየት ከመደበኛ ፆም አንፃር ምን ያህል የተለየ ጥቅም እንደሚያመጣ ገና አልታወቀም ያሉት ተመራማሪዎቹ፣ በዘርፉ የተለያዩ ጥናቶች እንደአስፈላጊነቱ ተደርገው ይፋ መደረግ እንደሚኖርባቸው ጠቁመዋል። ፆም ብዙ ያልታወቁ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ቢገመትም፣ እስከ አሁን ግን በእርግጠኝነት አስተሳሰብ ላይ በጎ የሆነ ለውጥ በማምጣት የሚፆመውን ሰው እንደሚጠቅም ለማወቅ ተችሏል።

አንድ ሰው ሲፆም የሚያገኛቸው ጥቅሞች እንደሚፆመው የሰዓት ልዩነት ይለያያል የሚሉት ተመራማሪዎቹ በመጀመሪያው ወቅት የተከማቸ ስብን ለማስወገድ ይረዳል። በቀጣይነት በደም ውስጥ የሚገኝ የስኳር መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል ። ‹ታይፕ2› የተሰኘውን የስኳር በሽታ ለመከላከል ያግዛል ሲሉም ያክላሉ። በመቀጠል የበለጠ ሰዓት በተፆመ ቁጥር አስተሳሰብ የተቃና እንዲሆን በማድረግ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ማተኮር እንዲችሉ እንዲሁም ያልተረበሸ አዕምሮ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ለ20 ሠዓት ያለማቋረጥ መፆም የሚችሉ ደግሞ ሰውነታቸው ራሱን በቀላሉ የማደስና ቁስል ቶሎ የመጠገን ዕድል እንዲኖረው ያደርጋል ሲሉ ስለፆም ጠለቅ ያለ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ሲናገሩ ይሰማል። ‹ዶክተር ክሊትዝ› የተሰኘው ድረ-ገጽ ላይ ስለአጠቃላይ የፆም ጥቅም የተዘረዘረ ሲሆን፣ ከላይ ከጠቀስናቸው ባሻገር ሰውነት ያለምንም እንከን ተግባሩ እንዲሳለጥና ውጤታማ እንዲሆን፣ ጤነኛና ደስተኛ ለመሆን ያስችላል ሲሉ ያመለክታሉ።

ከዚህ ቀደም በኒው ሜዲካል ጀርናል መጽሔት ላይ የወጣው የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በቀን ከ16 እስከ 18 ሰዓት ምግብ ሳይመገቡ ማሳለፍ የተለያዩ የጤና በረከቶችን ያስገኛል።

በመሆኑ ከፆም የሚገኙ የጤና ጠቀሜታዎች ምንድ ናቸው

**1. በደም ውስጥ ያለውን የስኳር መጠን ለመቆጣጠር ያስችላል፣**

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጾም በደም ውስጥ ያለውን የስኳር መጠን በተሻለ መንገድ ለመቆጣጠርና በተለይም የስኳር በሽታ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ጠቃሚ መሆኑ ነው የተጠቆመው።

**1. እብጠትን በመከላከል ሰዎች ጤናማ እንዲሆኑ ያስችላል**

ከዚህ ጋር ተያይዞ የወጡ ጥናቶች በጾም ወቅት ሰውነት የሚያገኘው የካሎሪ መጠን ከመቀነሱ ጋር ተያይዞ ሰውነት ላይ የሚከሰት እብጠት እንደሚቀንስ ያሳያሉ።

በአንድ ጥናት ላይ የተሳተፉ 50 ሰዎች ለአንድ ወር እንዲፆሙ የተደረገ ሲሆን በዚህም ከፍ ባለሁኔታ የእብጠት መጠን እንደቀነሰላቸው ተጠቁሟል።

ሌላኛው ጥናትም ሰዎች ለ12 ሰዓታት ሲፆሙ ተመሳሳይ ውጤት እንደተመለከቱ ተነግሯል።

**1. የደም ግፊትን እና የኮሌስትሮል መጠንን ለመከላከል**

ለከፍተኛ ክብደት የተጋለጡ ሰዎች በተደጋጋሚ እንዲፆሙ ተደርጎ የሰውነት ክብደታቸው መቀነሱ ተጠቅሷል።

የሰውነት ክብደታቸው መቀነሱ ደግሞ የደም ግፊታቸውና የኮሌስትሮል መጠናቸው እንዲቀንስ ረድቷቸዋል፤ ይህ ደግሞ ከልክ በላይ በሆነ ውፍረት ሊከሰት የሚችለው የልብ ጤንነት ችግር መቅረፍ ያስችላልም ነው የተባለው።

ፆም የአዕምሮ የመሥራት አቅምን ያፋጥናል፣ ከነርቭ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ይከላከላል፣ የሰውነት ክብደትን ለመቀነስ ይረዳል፣ ካንሰርን ለመከላከል እና ለምግብ መፈጨትና ለሥርዓት ምግብ መንሸራሸርን ለማፋጠን ይረዳል።

እንዲሁም ክብደት ለመቀነስ እና አጥንትን ለማጠናከር ወሳኝ የሆነውን ሆርሞን እድገት ለመጨመር እንደሚረዳም ነው የተጠቆመው።

በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች የዐቢይን ፆም ከጀመሩ ከአንድ ወር በላይ ያስቆጠሩ ሲሆን የእስልምና እምነት ተከታዮችም ከሳምንት በፊት የረመዳን ፆምን ጀምረዋል።ስለዚህም እነዚህ ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጾም የሚሰጣቸውን በረከቶች እንደሚያገኙ እናምናለን፡፡

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "በተጠየቅ" እና በጸሎት ምልጃ የምንሞግታቸው ሀገራዊ ስብራቶቻችን

(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

**"አንዳንዴም በዋልድባ..."፤**

ወደ መቶ ፐርሰንት የሚጠጋው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድም ይሁን በሌላ፤ ባሕርይውና ስያሜው ቢለያይም፤ በሃይማኖቶችና በእምነቶች ጥላ ሥር መሰባሰቡን አስረግጦ የሚያስረዳን የሀገራዊ እስታስቲካችን ውጤት ነው:: "የአይሁድ፣ የክርስትና፣ የእስልምና ሃይማኖቶችና ባሕላዊ እምነቶች ተጎራብተውና ተዋደው የሚኖሩባት" እየተባለች በዓለም ፊት ሞገስ ያገኘችው ሀገራችን በአድናቆት ስሟ የሚነሳው ሙሉ ለሙሉ ከችግሮች የጸዳች ስለሆነ ሳይሆን በአንጻራዊነትም ቢሆን የመልካሙ እሴት መዓዛ ይበልጥ ስለሚያውድና ብርሃኑ ከጨለማው ይልቅ የበረታ ጉልበት ስላለው ነው:: እርግጥ ነው ለሃይማኖት ቁብ የማይሰጡ፤ ከፈጣሪም ጋር ጠብ እስከ መግጠም ወደ ኋላ የማይሉ ጥቂት "አምላክ የለንም ባዮች" እንደሚኖሩም አይጠፋንም::

ስለዚህም "አንዳንዴ በዋልድባ..." እንዲሉ አልፎ አልፎም ቢሆን ይህንን በጎ እሴት እያስታወሱ መዘከሩ ለሀገራዊ ሰላማችን የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ ስለሆነ የምንደረደረው በዚሁ ሃይማኖታዊ ጉዳያችን ላይ ይሆናል:: "ኢትዮጵያ በሰሞኑ የዐብይ ጾምና በረመዳን ‹ቅዱስ ወር› ምክንያት በጾምና በጸሎት ላይ ነች" ይህን አባባል የሰማሁት ከአንድ የቅርብ ወዳጄ ነው:: ድንቅ ምልከታ ነው:: በርግጥም ይህ ወር ሀገሬ እጆቿን ወደ ጸባኦት ዘርጋት ጉልበቶቿን መሬት ያስነካችበት የምሕላ ወራቷ ነው ቢባል ተገቢም አግባብም ይሆናል::

አብዛኞቹ የሀገራችን ቤተ እምነቶች በቀኖናቸው፣ በዶግማቸውና በአስተምህሯቸው መሠረት "የጾምና የጸሎት አዋጅ በማወጅ" ምዕመናቸው የፈጣሪን ፊት እንዲፈልጉ ማበረታታቸው በሰውም ዘንድ ሆነ በፈጣሪ ዘንድ የሚያስመሰግናቸው ተግባር ነው:: የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በዐብይ ጾም፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች በረመዳን፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፣ የወንጌል አማኞች፣ በዝርዝር ያልተገለጹ ሌሎች የልዩ ልዩ ቤተ እምነቶችና የባሕላዊ እምነት ተከታዮችም እንዲሁ በሥርዓተ አምልኳቸው መሠረት በጸሎት፣ በዱዓና በምልጃ እየቃተቱ ስለመሆናቸው ምድርና ሰማይ ምስክሮች ናቸው::

ከአብያተ ክርስቲያናት እስከ መስጊዶች፣ ከምኩራብ እስከ ግለሰቦች ጓዳ ድረስ የሕዝበ ኢትዮጵያ ጉልበቶች ለጸሎት ተንበርክከው ፈጣሪያቸውን ከሚማጸኑባቸው ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱና ምናልባትም ከፍ ያለ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ የሀገራችን ወቅታዊ የሰላም ሁኔታ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አይከብድም::

ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የሚደመጠው የኪራላይሶን መቃተት፣ ለሙስሊሞች በአዛን የሚተላለፈው የጸሎት ጥሪ፣ ወይንም በአይሁዶች ቀንደ መለከት ድምጽ የመሰባሰቡ ዋና ጉዳይ "ኢትዮጵያ ነች "። የዚህ ሁሉ ምዕመን ጸሎት፣ የሚፈሰው እምባና የምሕላ ጩኸት፣ ሶላቱና በንስሐ መቃተቱ ያስፈለገው ለምንም ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕመም እንዲፈወስና የሕዝቧ ሰላም እንዲረጋገጥ ነው::

ይህ ጸሐፊ "ከገዥያችን ሕገ መንግሥት" አናቅጽ መካከል በተለይም የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት ከተገለጸበት አሥራ አንደኛው አንቀጽ ጋር በፍጹም አይስማማም:: "መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም" (ንዑስ አንቀጽ 3) የሚለው ድንጋጌ በተለየ ሁኔታ እውነታነቱና ገለልተኛነቱ እስከ ምን ደረጃ እንደሆነ ሳስብ ድንበሩ ይደበላለቅብኛል:: ተግባሩና ድንጋጌው ስለማይጣጣምም የተአማኒነቱ ጉዳይ ጥርጥር ላይ ይጥለኛል:: ይህንን ንዑስ አንቀጽ አዘውትሬ የምመስለው በሌሊት ወፍ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው::

**ሳብሬራው**:- የሌሊት ወፍ በመብረር ችሎታዋ ከአዕዋፍ ዝርያ፣ ጫጩቶቿን አጥብታ በማሳደጓ ደግሞ ከአጥቢ እንስሳት ትመደባለች:: ከአይጠ መጎጥ መልክ ጋር በመመሳሰሏም በተራ ዜጎች ዘንድ የእነርሱ ዝርያ ትሆንን አሰኝታ ግራ የምታጋባ አስተኔ (ብጤ) ፍጡር ነች:: "የሌሊት ወፍ ሁለት እንቁላል ትጥላለች፤ አንዱን ሲሰብሩት አስኳል፤ ሌላውን ሲሰብሩት ፍላጻ" እየተባለም ብሂል ተነግሮላታል:: በሕገ መንግሥታችን ጉዳይ ላይ ጊዜው ቀን ቆርጦ እስከንወያይበት ድረስ እኔና መሰል አስተሳሰብ የሚያራምዱ አስተኔዎቼ (ብጤዎቼ) በዚህ አንቀጽ ላይ ለመሟገት አጀንዳውን በይደር አስተላልፈን ቀኑ ቀን ሲያመቻችልን "ይግባኝ!" ብለን ክርክሩን እንቀጥላለን::

ለማንኛውም በየቤተ እምነት አጥቢያዎቻቸው ደጀ ሰላም ላይ ተደፍተው "በኤሎሄ!" ድምጸት ለሚቃትቱ፣ በየመስጊዳቸው የአላህን ስም እየጠሩ በተሰበረ ልብ ለሚጸልዩ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እየተማጸኑ "እግዚኦ!" ለሚሉ፣ በየምኩራባቸው ተሰባስበው በያህዌ ቅዱስ ዙፋን ሥር በመንበርከክ ለሚተጉ እና እንደየእምነታቸው በየጓዳቸው በራቸውን ከውስጥ ቆልፈው በፈጣሪያቸው ፊት ለሚያነቡትና በየሥራ መስካቸው "አምላክ ሆይ ስለ ኢትዮጵያ ተለመነን!" እያሉ ልባቸውን ከእጃቸው ጋር ከፍ አድርገው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በፈጣሪ ፊት በእምነት ለሚያቀርቡት ሚሊዮኖች በሚከተለው መልካም ቃል እንባርካቸዋለን::

"የፍጥረተ ዓለም ፈጣሪ ፈጥኖ ጸሎታችሁን ይስማ፤ ጾማችሁንም ይቀበል:: ፊቱን ያብራላችሁ፤ የርህራሄውን ድምጽም ያሰማችሁ:: የምታለቅሱላት ኢትዮጵያ በጸሎታችሁ ትፈወስ:: የዜጎቿ ልብም በሰላም ይረፍ:: ለመንግሥት ሹመኞች ጥበብና ማስተዋሉን ያብዛላቸው። ለከፋት በርትተው የጥፋት ክንዳቸውንና ልባቸውን ላደነደኑትም ከሰይጣናዊ ድርጊታቸው መመለስ ይሁንላቸው:: የሀገራችን ጠላቶች ሴራ ይክሸፍ:: አሜን!" - "አንዳንዴ በዋልድባም..." ብለን ተንደርድረናልና እነሆ የወቅቱን የሕዝባችንን ጾምና ጸሎት አስታውሰን "በምሥጢረ ሃይማኖት ጉዳይ" ይህንን ያህል ለማለት ሞክረናል:: ወደ ሌላው ምልከታ እናቅና::

**ስተጠየቅ ሙግት ግድ የሚሉን ስብራቶቻችን፤**

ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ "ባለን እንወቅበት" በሚል ርዕስ በ1961 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሐፋቸው ውስጥ የሀገራችንን ነባር ልማዳዊ የተጠየቅ (በላ ልበልሃ) የሙግት አካሄድ የገለጹት እንዲህ በማለት ነበር:: "ሕዝባችን ብልህ ነው፤ ፈጥኖ የመረዳትና የማስረዳት ችሎታ አለው። የነገርን አካሄድ ይመረምራል፤ የአስተዳደር ምክር፣ ክርክር፣ ዳኝነትና ፖለቲካ የተፈጥሮ ገንዘቡ ናቸው" (ገጽ 18)::

የተጠየቅ ሙግቱ (የበላ ልበልሃ) ፍልሚያው ፍዝ አይደለም:: ማራኪና ተውኔታዊ ባሕርይ የሚንጸባረቅበት ጭምር ነው:: አካሄዱን በተመለከተ ደራሲ ስለሺ ለማ "ተጠየቅ" በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ይገልጹታል "ተውኔታዊ ባሕርይ የነበረው የከሳሽና የተከሳሽ አለባበስ፣ አቋቋም፣ ዘንግ አያያዝ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የነገር አቀራረብና ባጠቃላይ ሞቅና ደመቅ ያለው ጥምር የአሞጋገት ስልት በእጅጉ ያስደንቃል::

ተሟግቶ ለመርታት፣ ረትቶም እርካታን፣ ዝናንና ክብርን ለመቀዳጀት በቅድሚያ የተሟጋቹን ንቃት ብልህነትና ብርታት ይጠይቃል:: ከዚህም የተነሳ ከሰውነት እንቅስቃሴ ሌላ በተለይ የመሚገቻ ቋንቋው በተዋቡ ቃላት፣ በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በተረት፣ በአፈታሪክ፣ በእንቆቅልሽና በመሳሰሉት ዘዬዎች የበለጸገ ነው:: የእነዚህ ሁሉ ውሕድ የችሎት ነጻ ትርዒት ነው እንግዲህ ወጪ ወራጁን፣ አላፊ አግዳሚውን ሁሉ ይማርክ የነበረው" (ገጽ 15)::

አሁን ወደ ተጠየቁ ሙግት ዘልቀን እንግባ:: ለመሆኑ ሀገራዊ ስብራታችን ስለምን በረታብን? የሀገሪቱ ቀዳሚ ለውጥ ናፋቂ ብኩን ትውልድ በእንጉርጉሮ፣ ደርግ በጠብመንጃ፣ ኢሕአዴግ በግፍ ለበስ አስተዳደሩ፣ ብልጽግና በእሹሩሩ ማባበያ እያዘመሩንና እያዘየሩን በመካደም ቤትኛ እንዲሆን የሙጥኝ ያለነው "ዲሞክራሲ" ለምን ሥር አልይዝ አለን? ስለምንስ ጣፋጭ ፍሬ ያፈራል ብለን ከሃምሳ ዓመት በላይ በትዕግስት ስንጠባበቅ ሆምጣጣ ፍሬ አፍርቶ ተስፋችንን ለማምከን ምክንያት ሆነ?

ቀደም ባለው ጽሑፌ "ኦ ዲሞክራሲ በስምህ ስንት ግፍ ተሠራ?" በማለት የቆዘምኩበት ጽሑፌ ብዙ ጉዳዮችን ስለነካካ "የአዋጁን በጓዳ" እንዳይሆንብኝ አንባቢ ቤትኞችን ደግሜ አላሰለችም:: በአጭሩ ለመግለጽ ካስፈለግ ግን "ዲሞክራሲውም ሆነ ዲሞክራት ተብዬዎቹ ሁለቱም ታመው እያቃሰቱ ነው:: ስለዚህም በስመ ዲሞክራሲ ስም ተስፋ የተገባልን ሁሉ እንኳን ሊተገበር ቀርቶ ያሉን ነባር እሴቶች ራሳቸው ተሰነጣጥረው ተሰባብረዋል::

የመጀመሪያው ስብራታችን ከፍትሕ ሥርዓታችን ጋር የተያያዘ ነው:: በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ትንቢተ ዕንባቆም የሚል ርዕስ የተሰጠው አንድ አስደናቂ መጽሐፍ አለ:: ነብዩ ልክ በእኛ ዘመን አብሮ የኖረ ይመስል "ጩኸታችንን ነጥቆ" እንዲህ እያለ ፈጣሪን ይሞግታል:: "እኛ ስንጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው? ስለ ግፍ ወደ አንተ እንጮኻለን አንተም አታድንም::

ሕግ ላልቷል ፍርድም ድል ነስቶ አይወጣም:: ስለዚህ ፍርድ ጠማማ ሆኖ ይወጣል" (ትንቢተ ዕንባቆም 1:2 - 4):: ስብራታችንን የከፋ የሚያደርገው "ከማታ ተኩላ ይልቅ ጨካኞች" በየጊዜው የሚፈጽሙት ግድያና እገታ የወትሮ ልማድ ሆኖ እስኪቆጠር ድረስ እንድንለምደው መደረጉ ነው:: ፍትሕ ሆይ ወዴት አለህ? "ይህንን ያህል ሺህ ሰው ተገደለ፣ አካለ ጎዶሎ ሆነ፣ ተፈናቀለ፣ ተሰደደ" የሚለው መርዶ መቼ ነው የሚቆመው? እኛ እንጠይቃለን መላሹም መልስ ይሰጠን::

ሁለተኛው ስብራታችን የፖለቲካ ስብራት ነው። ምናልባትም ለስብራቶቻችን በሙሉ "አብሾ አጠጥቶ" ያሳከረን ይሄው የግሪኮችን ስም የያዘውና በውሰት አምጥተነው ቤታችንን እያናጋ ያለው በዲሞክራሲ ስም የተለበጠው ፖለቲካችን ሳይሆን አይቀርም:: ድሮ ድሮ የመረዳት አቅማችን ጨቅላ በነበረበት ዘመን መምህራኖቻችን "Politics is a bad game" ሲሉን አይገባንም ነበር::

ዛሬ በጉልምሳናና በዘመነ ሽበት እያስተዋልን ያለነው በእርግጥም ፖለቲካ ይሉት "የሥልጣን መናጠቂያ ዕቃ ዕቃ" እብደቱ ለይቶለት ጭርሱኑ ጨርቁን ጥሎ አደባባይ መውጣቱን ነው:: ለሥልጣን ሲባል ምንም ነገር ከማድረግ ማንም እንደማይመለስ በብዙ ማስረጃዎች ካረጋገጥን ሰንብተናል::

ሦስተኛው ስብራት የሞራልና የግብረ ገብ ስብራታችን ነው:: ሽቅብ አንጋጦ አባቶችን መሳደብ፣ ታላላቆችን ማዋረድ፣ የእምነት መሪዎችን መዘለፍና ማንጓጠጥ የባሕል ያህል ተጣብቶናል:: ማኅበራዊው ሚዲያ አቅላችንን ሰልቦ ካስገበረን ውሎ አድሯል:: "እኔን የወለደኝ ፌስ ቡክ ነው እንዴ?" በማለት ወላጆችን እንደሞገተችው ልባም ሕጻን "እኛስ እንደ ሀገር የምንመራው በማኅበራዊ ሚዲያ ሆነ እንዴ?" ብለን "እንጠያየቅ" ብለን ብንዋቀስ ተገቢ ይመስለናል::

ከሰብዓዊ ክብር ይልቅ የቁስና የነዋይ ጫና የበረታበት፣ አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ ያለባቸው ዜጎች ያለመማለጃ የዜጎችን ጉዳይ ላለመፈጸም መጨከን ሌላው ስብራታችን ነው:: የሕሊናን ጨርቅ ጥለው ባበዱ ገዳዳ ነጋዴዎች የሚፈጸመው የኢኮኖሚ አሻጥርና ሴራ ሕዝብ ሲያለቅስ እነርሱ ቤታቸውን ቆልፈው "ወይን ያስተፈስህ ለልበ ሰብ" እያሉ "ዋንጫ ኖር - Cheers" መባባላቸውን ቤታቸው ተገኝተን የዐይን ምስክር ባንሆንም በአደባባይ የገነነው ጠረናቸው ግን በሚገባ ድርጊታቸውን ያሳብቃል።

አራተኛው ስብራታችን በስመ ሃይማኖት አቅል የሳቱ ልምምዶች አየሩን መበከላቸው ነው:: አንዳንዶች ፈጣሪን ራሱን ሻምላ አስጨብተው ከእነርሱ ጋር ቆሞ እንዲፋለምላቸው በአደባባይ ሲፎክሩና ሲያስፎክሩ ስንመለከት "እግዚኦ!" እያልን ብናማትብም ጸሎታችን አቅም አንሶት ሳይሆን አይቀርም፤ በነጋ በጠባ የምናስተውለው ክፋቱ እየበረታ ሲሄድ እንጂ ሲቀዘቅዝ አይደለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ የበላ ልበልሃ ሙግቱን ከማን ጋር እንደምናደርግ ግራ ስለሚያጋባ በለመድነው "ሆድ ይፍጀው" ሽሽት "ፈጣሪ ሆይ ክብርህን አስጠብቅ" ብለን ማምለጡን መርጠናል::

በብሔርና በቋንቋ ምክንያት የደረሰብንን ስብራት በተመለከተ ግን "በተከድኖ ይብሰል" ትዝብት ነካክተን የምናልፈው ሳይሆን በየቦታው በአፈርሳታና በአውጫጭኝ እየተጠራራን "ሌባው ለማ፣ ጀንበር በሰረቀ ቁጥር እየተቃጠልን እንዴት እንዘልቀዋለን" እንዳሉት ሸንጎኞች እኛም ዳር ዳር ከመዞርና ከማሳበብ ወጥተን በበላ ልበልሃ ሙግት ልንበረታ ይገባል:: በነገራችን ላይ "ሌባው ለማ..." የሚለውን ታሪክ ለአንባቢያን ፈታ አድርጎ ማለፉ አግባብ ስለሆነ ፍቺውን ሳንርቅ በቅርቡ አስታውሰን እንለፍ::

"በድሮ ጊዜ" እንዲሉ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በተደጋጋሚ ጊዜ ንብረታቸውን እየተዘረፉ ተቸገሩ ይባላል። ሌቦቹ ከሩቅ የመጡ ሳይሆኑ እዚያው በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸው በሹክሹክታም ቢሆን ነዋሪው ከአፍ አፍ እየተቀባበለ ማንነታቸውን አውቆታል:: "ሌቦቹ እኔ አከሌ ናቸው" ለማለት ፍርሃት የተጫነው ነዋሪ እህህ እንዳለ ውሎ አምሽቶው የአውጫጭኝ ጉባዔ ብቻ ሆኖ ቀረ:: ይህን መሰሉን የፍርሃት አዚም ለመግፈፍ አንድ ጠቢብ አባት ተገኙ ይባላል። እንደተለመደው አውጫጭኙ በተጠራ እለት በሕዝቡ መካከል ቆመው ከላይ የተነገረውን ቅኔ ለበስ ንግግር በማድረግ ሌቦቹ "ለማ፣ ሰረቀ እና ጀንበር" መሆናቸውን በጥበብ ንግግር አፈረጡት ይባላል። የበላ ልበልሃ ሙግታችንና የተጠየቃችን ፍልሚያ ገና አልተጠናቀቀም። ኢትዮጵያ ሆይ! ስብራትሽን ገና ዘርዝረን ስላልጨረስን ሳንታክት እንቀጥልበታለን:: ዜጎችሽ በጾም ጸሎት እኛ ብዕረኞችም በተጠየቅ ሙግት ፈጣሪያችን "ብርሃን ይሁን ብሎ፤ ብርሃን እንደሆነው" የምሥራች እስኪያሰማን ድረስ በጥልቅ ጨለማ ከሚመስሉት ሀገራዊ ችግሮቻችን ጋር የምናደርገውን ፍልሚያ ጠንክረን እንቀጥላለን:: ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ::

# ተናጋሪው ዶሴ

# ያዲያቆነ ሰይጣን ሳያቀ'ስ አይለቅም. . . እንዲሉ

አስመረት ብስራት



ቀኑ የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ.ም ነበር። ብሩህ፣ ፍክት ያለ ቀን። ብዙ ሰው ማልዶ ወደ ጉዳዩ ለመድረስ ጠደፍ ጠደፍ እያለ የሚንቀሳቀስበት ማለዳ። ሁሴን አህመድ አይል ሊቢያ፣ የመኪና ዘይት እና ቅባቶች ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችም በጠዋቱ ነው የሥራ ገበታቸው ላይ የተገኙት። እንደወትሯቸው አስፈላጊውን የሥራ ዝግጅት አድርገው ደንበኞቻቸውን እየተጠባበቁ ነው።

በዕለቱ ከወትሮው የተለየ እንቅስቃሴ ባይኖርም ረፈድፈድ ሲል ግን ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ወደ ድርጀቱ ገቡ። የሰዎቹ በአንዴ መምጣት ግርምታን ቢፈጥርም ቀልጣፎቹ የድርጅቱ ሠራተኞች ግን የተለመደው ትህትና በተሞላበት አቀራረብ ግር ብለው የገቡትን ተገልጋዮች ተቀብለው ማስተናገድ ጀመሩ።

ሰዎቹ ግን በትህትና የተቀበሏቸውን ሠራተኞች መስተንግዶ ከመሻት ይልቅ ዓይናቸው እዚህም እዚያም ይቅበዘበዝ ነበር። እጃቸውም ይሄንንም ያንንም እያነሳ ይጥላል፤ እዚህም እዚያም በመርገጥ ትንሽ ወከባ የሚመስል ነገር ከፈጠሩ በኋላ ምንም ዓይነት ነገር ሳይገዙ ድርጅቱን ለቀው በሰላም ይወጣሉ።

በተጠንቀቅ ሥራቸውን ሲሠሩ የነበሩት የድርጅቱ ሠራተኞች በሁኔታው ግራ ቢጋቡም ሰዎቹ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳያደርሱ በመውጣታቸው ተረጋግተው የዕለቱ ሥራቸውን መሥራት ጀመሩ።

በአቶ አባይነህ ወርቁ እየተመራ ሁሴን አህመድ አይል ሊቢያ የመኪና ዘይት እና ቅባቶች ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ የገባው ቡድን ለዝግጅት በቂ የሆነ መረጃ መያዙን እንዳረጋገጠ ነበር ድርጅቱን ለቆ የወጣው። በወከባና በማደናገር መካከል መውጫ መግቢያውን በተገቢው መልኩ እንዲያጠኑ ተልዕኮ የወሰዱት ገብረ አበሮች ተገቢውን መረጃ ማግኘታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በዓይን ጥቅሻ ምልክት ሰጥተው ወደ መሰብሰቢያ ቦታቸው አቀኑ።

### የዘራፊው ቡድን ዝግጅት

ገና በጠዋቱ ዝግጅቱን የጀመረው በአቶ አባይነህ የሚመራው የዘረፋ ቡድን ሁሴን አህመድ አይል ሊቢያ የመኪና ዘይት እና ቅባቶች ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ ግብቶ ለዘረፋው የሚሆን መረጃ ካሰባሰበ በኋላ ማን ምን ማደረግ እንዳለበት የሥራ ክፍፍል ለማደረግ በድብቅ ወደ ተዘጋጀው መሰብሰቢያ ቦታ ያቀናል።

መግቢያ መውጫውን፤ የቱ ጋር ዋጋ የሚያወጡ ዕቃዎች እንደተቀመጡና፤ በምን ሰዓት ዘረፋው ቢፈፀም ከስጋት ነፃ ይሆናል የሚለውን ተከፋፍሎ ያጠናው የዘረፋ ቡድን ሁሉንም ጥናት በአንድ በማድረግ የሥራ ድርሻ ክፍፍል ያደርጋል።

ለዚህ ድርጊትም መቀላጠፍ መኪና ማግኘት የግድ ስለነበር በማታ፣ በራሱ በቡድኑ አባላት ሊሾፈር የሚችል የመኪና ኪራይ ፈልገው ያዘጋጃሉ። ድንገት ችግር ቢፈጠር እንኳን ለማስፈራራት፤ ባስ ካለም ሰው ለማጥፋት የሚያስችል የጦር መሣሪያም ተዘጋጀ። በምሽት ሊካሄድ ለታሰበው ዘረፋ ማንም እንቅፋት እንዳይሆን ከአልባሳት አንስቶ በቂ እንቅልፍ እስከመተኛት ድረስ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀው የምሽቱን መግፋት በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር።

እንዳይደርስ የለም የታቀደው እቅድ መፈፀሚያ ሰዓት ደረሰ። ተራ በተራ ከጎሬያቸው የወጡት የዘረፋ ቡድኑ አባላት ቀን ላይ ወደ አዘጋጁቸው ሁለት አይሱዙ የጭነት ተሽከርካሪዎች አቀኑ። ልክ በሥራ መደባቸው መሠረት በየመኪኖቻቸው ተጭነው ለዘረፋ ወደ ተዘጋጀው ድርጅት አቀኑ።

### በጥናት የተካሄደው ዘረፋ

ቀን ሲዘጋጅ የዋለውና በአቶ አባይነህ የሚመራው ቡድን ቦታው ደርሷል። የዕለቱ ተረኛ የነበሩት የጥበቃ ሠራተኞች አገር ሰላም ብለው እንደወትሯቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ። በሞባይል የተከፈተው የሬዲዮ ፕሮግራምን ተመስጠው እየሰሙ፤ የዕለት ግዳጃቸውን እየተወጡ የነበሩት የጥበቃ ሠራተኞች ጠንከር ባለ ምት በሩ ሲንኳኳ ሰሙ። በዚህ ሰዓት ሊያውም በኃይል ማን ሊያንኳኳ ይችላል የሚለውን ለመመልከት ሬዲዮውን ዘግተው ወደ በሩ ቀረብ አሉ።

«ማነው ....» አሉ ጠንከር ባለ ድምፅ።

«ፖሊሶች ነን ...» የሚል ምላሽ ተሰማ።

«ምን ፈልጋችሁ ነው?» አሉ ጥበቃው በጥርጣሬ።

«ሌባ ገብቷል፤ ፖሊሶች ነን፤ ክፈት።» አሉት ከውጭ በትእዛዝ። ምንም ዓይነት የሚያሰጋ እንቅስቃሴ ያልሰሙት ጥበቃ በሩን ቀስ አድርገው ከፍተው ወደ ውጭ ተመለከቱ። እውነትም የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ ናቸው። ልባቸው ረጋ አለ። በሩን በሰፊው ከፈቱት።

ሁለት የጭነት አይሱዙ መኪና ይዘው በመምጣት የፖሊስ የደንብ ልብስ ለብሰው ሽጉጥ በእጃቸው በመያዝ ወደ ውስጥ የገቡት ዘራፊዎች የጥበቃ ሠራተኛውን በማነቅ ዘረፋቸውን ይጀምራሉ።

ድርጊቱ የተፈፀመው የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 7፡10 ሲሆን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 04፣ አበበ ቢቂላ ስታዲየም እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነበር። የግል ተበዳይ ሁሴን አህመድ አይል ሊቢያ የመኪና ዘይት እና ቅባቶች ማከፋፈያ ድርጅት ውስጥ የሚገኘውን 6 ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ለመውሰድ ሁለት አይሱዙ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ይዘው የመጡት የዘረፋ ቡድን፤ ለጊዜው ያልተያዘ ተጠርጣሪ የድርጅቱን አጥር ዘሎ ወደ ውስጥ ሲገባ ተከሳሹ እና ሌላ አንድ ለጊዜው ያልተያዘ ተጠርጣሪ የፖሊስ የደንብ ልብስ ለብሰው፣ ሽጉጥ በእጃቸው በመያዝ ወደ ድርጅቱ ግቢ የገባውን ተጠርጣሪ ተከትለው በመምጣት የድርጅቱን ጥበቃ ሠራተኛ «ሌባ ገብቷል፤ ፖሊሶች ነን፤ በር ክፈትልን።» በማለት እንዲከፍትላቸው አድርገዋል።

ከዚያም በኋላ ከሌሎች ግብረ-አበሮቻቸው ጋር ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ አንደኛው ግብረ-አበር አንዱን የዐቃቤ ሕግ ምስክርን በሁለት እጁ አንቆ ሲይዝ ሌላኛው ያልተያዘው ተጠርጣሪ የጥበቃውን ዓይን በእጆቹ ሸፍኖ በመያዝ መሬት ላይ ጥለው ራሱን እንዲስት ያደርጉታል።

ሌሎች ያልተያዙ ተጠርጣሪዎች ጥበቃውን በመያዝ ዓይኑን ሸፍነው መሬት ላይ በመጣል ንብረቱን ለመውሰድ እንዲያመቻቸው መከላከል እንዳይችሉ በማድረግ ላይ እያሉ የጥበቃ ተራውን ጨርሶ በሌላኛው የድርጅቱ በር የጥበቃ ማማ ላይ የተኛው ጥበቃ ከእንቅልፉ በመንቃት የቆርቆሮውን በር በኃይል ሲከፍተው ተከሳሹና ግብረ-አበሮቹ ሌላ ጥበቃ እንዳለ አይተው የወንጀል ድርጊቱን እስከመጨረሻው ለመከታተል ሳይችሉ ሸሽተው ሄዱ።

ምንም እንኳን ቡድኑ ያሰበውን ቢያደርግም ወንጀል ፈፃሚዎቹ ከድርጅቱ በተደረገ ጥቆማ መሠረት ክትትል ይደረግባቸዋል። ፖሊስም አስፈላጊውን አሰሳ በማድረግ ዋናውን ወንጀል አድራጊ በቁጥጥር ስር በመዋል (ምንም እንኳን ዘረፋውን አቋርጠው የሄዱ እና ድርጊቱም የተቋረጠ ቢሆንም) በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ከባድ ውንብድና ሙከራ በወንጀል ሊከሰሱ ችለዋል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ተከሳሽ ካልተያዙ ግብረ-አበሮቹ ጋር በመሆን ሁለት አይሱዙ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ይዘው በመምጣት የፖሊስ የደንብ ልብስ ለብሰው፤ ሽጉጥ በእጃቸው በመያዝ ሌባ ገብቷል፣ ፖሊሶች ነን፣ በር ክፈትልን በማለት የድርጅት ጥበቃውን እንዲከፍትላቸው በማድረግ፤ ንብረቶችን ለመዝረፍ የውንብድና ሙከራ ወንጀል የፈፀመው አባይነህ ወርቁ የተባለው ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/፣ 32/1/ሀ/፣ እና 671/1/ለ/ ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ክስ ቀርቦበታል፡፡

### የፍርድ ቤት ክርክር

ከላይ የተጠቀሰውንና የካቲት 3 ቀን 2013 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 7፡10 የተፈፀመውን የወንጀል ድርጊት በመፈፀም ከሌሎች ግብረ-አበሮቹ ጋር ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ አንደኛው ግብረ-አበር አንዱን የዐቃቤ ሕግ ምስክርን በሁለት እጁ አንቆ ሲይዝ ሌላኛው ያልተያዘው ተጠርጣሪ የጥበቃውን ዓይን በእጆቹ ሸፍኖ በመያዝ መሬት ላይ ሲጥሉት ሌሎች ያልተያዙ ተጠርጣሪዎች ጥበቃውን በመያዝ ዓይኑን ሸፍነው መሬት ላይ በመጣል ንብረቱን ለመውሰድ እንዲያመቻቸው መከላከል እንዳይችሉ በማድረግ ላይ እያሉ የጥበቃ ተራውን ጨርሶ በሌላኛው የድርጅቱ በር የጥበቃ ማማ ላይ ተኝቶ የነበረው ከእንቅልፉ በመንቃት የጥበቃ ማማውን የቆርቆሮ በር በኃይል ሲከፍተው ተከሳሹና ግብረ-አበሮቹ ሌላ ጥበቃ እንዳለ አይተው የወንጀል ድርጊቱን እስከመጨረሻው ለመከታተል ሳይችሉ ሸሽተው የሄዱ እና ድርጊቱም የተቋረጠ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀመው የከባድ ውንብድና ሙከራ ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶበታል፡፡

ተከሳሹ ክሱ በችሎት ተነቦለት የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም ያለ ሲሆን አቃቤ ሕግም ተከሳሹ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሚያስረዱ የሕግ ምስክሮቻችን ስላሉ ይሰሙልኝ በማለት 5 የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የአቃቤ ሕግ ምስክሮችና ማስረጃዎችም በተከሳሹ ላይ በክሱ መሠረት ያስረዱ በመሆኑ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ እንዲከላከል የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቀጠሮ በተሰጠው መሠረት 2 የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ቢያሰማም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን ሊያስተባብል ባለመቻሉ ተከሳሹ ይከላከል በተባለበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነህ ብሎታል፡፡

### ውሳኔ

ጉዳዩን የተመለከተውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ልደታ ምድብ 2ኛ ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎትም መጋቢት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ባስቻለው ችሎት ተከሳሹ ከዚህ ቀደም በ26/04/04 ዓ.ም በ8 ወር እስራት፤ እንዲሁም፣ በቀን 8/5/2007 ዓ.ም በ7 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሲሆን፤ ይህም ተከሳሽ በተደጋጋሚ ወንጀል ፈፅሟል የሚያስብል በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ 2 የቅጣት ማክበጃ ያቀረበበት ሲሆን፤ ተከሳሽ በበኩሉ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ እና ሌሎች 4 የቅጣት ማቅለያ ተይዞለት፣ እንዲሁም ወንጀሉ በሙከራ የቀረ በመሆኑ በቅጣት እርከን 33 ስር ቅጣቱ ተሻሽሎ በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኖበታል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የፕላስቲክ ከረጢቶች መዘዝ

ደቤ ከደጃች.ውቤ

አዲስ አበባን በመሳሰሉ ከተሞች አነስተኛ ሸቀጣ ሸቀጦች በተለይ እንደ ጫት ያለ ቅጠላ ቅጠል፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ፣ ምግብና ወዘተ ስንሸምት ለመያዣነት የምንጠቀመው የፕላስቲክ ከረጢቶችን (ፌስታል) ነው፡፡ ቀድሞ ካኪ/ኪስ ወረቀት እንጂ ፌስታል ለቁሳቁስ መጠቅለያነት አይውልም ነበር፡፡

ከልኳንዳ ሥጋ ሲገዛ ኪሎው ተመዝኖ በጋዜጣ ተጠቅልሎ ይሰጥ የነበረበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፡፡ ቅቤ እንኳን ሲሸጥ መያዣው የኮባ ቅጠል ነበር፡፡ መርካቶ ዱባይ ተራና ሚሊተሪ ተራ ጨርቃ ጨርቅ ብትገበዩ፤ ሽራ ተራም ሆነ አመዴ ገበያ ጫማ ብትሸምቱ በጋዜጣ ተጠቅልሎ አልያም ትንሽ ሳጥን በሚመስል ጠንከር ያለ ካርቶን እንጂ ፌስታል ለመያዣነት አይውልም ነበር፡፡ ያኔ አብዛኛው ነጋዴ ጋዜጣ እየገዛ ዜናውንና መረጃውን ካነበበ በኋላ የሚሸጠውን ቁሳቁስ ለመጠቅለያነት ያውለው ነበር፡፡ እናቶች እንኳን ለዕለት፣ ለሳምንት በሉት ለወር የሚሆን አስቤዛ ሲሸምቱ ከሰሌን የተሠራ ዘንቢል አልያም በስስ ጨርቅ የተሠራ አነስተኛ ዕቃ መያዝ የሚችል ጨርቅ ነገር ነው የሚጠቀሙት፡፡ ይህን አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ተክቶ አሁን ላይ የትም የሚገኘው ስስ ፌስታል በገበያ አልነበረም፡፡ አልፎ አልፎ ቢኖር እንኳን ከካኪ ወረቀት የማይተናነስ ጠንካራ ፌስታል ነው፡፡

ፌስታል ገበያ ላይ ውሎ በየቦታው እቃ መያዣ መሆን ከጀመረ ቢበዛ ሦስት አስርተ ዓመታት አይሆንም፡፡ የዛሬን አያርገውና ሳንቲሞች አቅም ሳያጥራቸው በፊት አንዱ ፌስታል 15 ሳንቲም ይሸጥ ነበር፡፡ ይህም ለአጠቃቀም ምቹ ከመሆኑ ጋር ተደምሮ ቀስ በቀስ የፌስታል ገበያ ተፈላጊነቱ እየጨመረ ሲሄድ ቀድሞ የካኪ ወረቀት የሚሰጠውን አገልግሎት ሙሉ በሙሉ እንዲተካ አድርጎታል። አሁን ላይ የትኛውም ቁሳቁስ ሲሸመት መያዣው ፌስታል ነው። ሥጋ እንኳን በጋዜጣ ቀርቶ በፌስታል ተጠቅልሎ ነው የሚሰጠው። ያውም ከመሳሳቱ የተነሳ የያዘውን ሸቀጥ ከሱቅ ቤት ድረስ የማድረስ አቅም በሌለው።

ፌስታል አገልግሎቱ ባልከፋ ነበር። ከአገልግሎቱ በላይ በአካባቢ ብክለት የሚያደርሰው ጉዳት አንድና ሁለት አይደለም። ለመጪው ትውልድ ጭምር ዘመን ተሻጋሪ ችግር ጥሎ የሚያልፍ ነው፡፡ በፌስታል መጠቀም ጊዜያዊ ችግር ቀባሪ ቢመስልም ዘላቂ ችግር ፈጣሪ ነው። ፌስታልና ሌሎች ላስቲኮች በመቶ ዓመት እንኳን አለመበስበሳቸው ለመሬት መከላት ዋነኛ ምክንያት ናቸው። በተለይ በገጠር አካባቢዎች የወዳደቁ ፌስታሎች ለእርሻ ትልቅ ተግዳሮት ናቸው። ፌስታሎች በወደቁበት አካባቢ ሳር፣ ቅጠላ ቅጠል እንዳያድግና እንዳይለመልም ምክንያት ይሆናሉ።

እንደ ጎረቤታችን ኬንያ የመሳሰሉ አገሮች በፌስታል መገበያየት የታገደ ስለሆነ አይታሰብም፡፡ በዚህም ለአካባቢ ጥበቃ ከሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ጎን ለጎን ለከተሞቻቸው ንጽሕና ሚናቸው ቀላል አይደለም፡፡

እኛ አገር ከተማው ገጠሩ ሳር ቅጠል ሳይሆን በፌስታል የተሞላ ነው። የፌስታል ችግር ይበልጥ የሚገባን በክረምት ወቅት ነው፡፡ በክረምት እንደ አዲስ አበባ በመሳሰሉ ከተሞች ፌስታሎች በየቦታው ተጥለው ይታያሉ፡፡ በየአጥሩ ጥጋ ጥግ ፣ በፍሳሽ ቱቦዎች መተላለፊያ ውስጥ እና በከተማዋ ወንዞች ሁሉ ፌስታል የተጣለ ሳይሆን ከዝናብ ጋር ከሰማይ የወረደ ሊመስል ይችላል፡፡

በእምነት ቦታዎች፣ በኳስ መጫወቻ ሜዳዎች፣ በወንዞች፣ በፍሳሽ ቱቦዎች በፌስታል ተሞልተው ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ዝናብ ሲዘንብ ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በፌስታል ስለሚደፈኑ በዚያ ላይ ፍሳሽና ጎርፍ ሲጨመር ፍሳሹ ትቦውን ጥሶ አስፋልት ላይ እንዲፈስ ያደርጋል።

ወደ ገጠር ከተሞች የሚያደርሱ ዋና ዋና የአስፋልት መንገዶች ዳርቻ በፕላስቲክ ‹ጠርሙሶች› እና በፌስታል እየተሞላ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግብርናውንና የአካባቢ ብክለትን ከመጨመሩ ባሻገር ከብቶች እየበሉት የሚጎዱበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም።

በአገራችን እያንዳንዱ ዜጋ በዓመት በአማካይ 238 ፕላስቲክ ሻንጣዎችን እንደሚጠቀም የቅርብ ጥናቶች ያመላክታሉ። ይህ ብዛት 97.000 ቶን ይሆናል፣ በዚህ ሁሉ ብክነት እንደገና ጥቅም ላይ የዋለው 10% ብቻ መሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

ስርጭትንና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ጉዳዮችን የማስተማር አስፈላጊነት ግን አልተሠራበትም፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረት ቢደረግም ፕላስቲክ ከረጢቶችን መልሶ የመጠቀም ባሕል በጣም አነስተኛ ነው፡፡

በፕላኔታችን ላይ በብዛት በብክለት ደረጃ ከሚጎዱና የሰው ልጆች በስፋት ከሚያመነጩት አካባቢያዊ ችግሮች መካከል አንዱ የፕላስቲክ ከረጢቶች ሲሆኑ በምድራችን በየትኛውም ማዕዘን እየተከማቹ እንደሚገኙ በርካታ መረጃዎች አሉ፡፡ ይህ ማለት ከአካባቢ አልፎ በአጠቃላይ በዓለም ዙሪያ ዓለም አቀፍ ብክለትን ያስከትላል ማለት ነው፡፡

አንድ የፕላስቲክ ሻንጣ ለአያያዝ አመቺና በቀላሉ የሚቀመጥ በመሆኑ ብክለት አያመጣም ብለን እናስብ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በፕላስቲክ ከረጢቶች የውሃ መበከል በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን፣ እንስሳትን፣ ኤሊዎች እና አዕዋፎችን ለሞት ይዳርጋል፡፡

የፕላስቲክ ከረጢቶችን ለማምረት ከፍተኛ መጠን ያለው ኃይል ያስፈልጋል፣ እናም የእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ከዘይት የሚመነጩ ንጥረ ነገሮች የአካባቢ ጠንቅ ሆነው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መርዛማ የብረት ቅሪቶችን የያዙ የፕላስቲክ ከረጢቶች ግን ዛሬም ያለ ምንም ዓይነት ቁጥጥር በየቦታው ይጣላሉ፡፡

ሀገራት የፕላስቲክ ከረጢቶችን አጠቃቀም ለመቀነስ የተለያዩ መንገዶችን እያጤኑ ነው፡፡ አንደኛው መፍትሔ በእነዚህ ሻንጣዎች ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሙሉ በሙሉ ሊበሰብሱ በሚችሉ ሌሎች ንጥረ ነገሮች መተካት ነው። እኛም ትኩረት አልሰጠነውም እንጂ ቢያንስ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የምንጠቀምባቸውን የፕላስቲክ ከረጢቶች መጠን መቀነስ እንችላለን፡፡

ለዚህም የጨርቅ ሻንጣዎችን ወይም አንዳንድ ተመሳሳይ ቁሳቁሶችን ብንጠቀም አንድ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ማለት ወደ ገበያ በምንሄድበት እያንዳንዱ ጊዜ ብዙ የፕላስቲክ ሻንጣዎችን መጠቀም አያስፈልገንም ማለት ነው ፡፡

የራሳችንን የግዢ ሻንጣ ይዘን ወደ ሸመታ ብንወጣ፣ ጥቂት ነገሮችን ብቻ የምንገዛ ከሆነና እጃችን ሊሸከም ከቻለ የፕላስቲክ ከረጢቶችን አለመጠቀምም ካሰብንበት ቀላል መፍትሔ ሊሆን ይችላል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ብራዚል እና ቻይና ከዶላር ውጪ በሆነ ገንዘብ ለመገበያየት ተስማሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ብራዚል እና ቻይና ከዶላር ውጪ በሆነ ገንዘብ ለመገበያየት ተስማሙ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ የዓለማችን ሀገራት ከዶላር ውጪ ባሉ ገንዘቦች ለመገበያየት ስምምነቶችን በመፈራረም ላይ ናቸው መሆናቸው ተገልጧል፡፡

ብራዚል እና ቻይናም ከዶላር ውጪ በሆነ ገንዘብ ለመገበያየት ተስማምተዋል፡፡ ቻይና ከአሜሪካ ጋር ያላት ግንኙነት ወደ መካረር ማምራቱን ተከትሎ ከዚህ በፊት በአሜሪካ ዶላር ስታደርጋቸው የነበሩ የንግድ ልውውጦችን በመቀየር ላይ ትገኛለች።

ቤጂንግ ከዚህ በፊት ከሩሲያ፣ ሳውዲ ዓረቢያ እና ሌሎችም ሀገራት ጋር የመገበያያ ገንዘቧን በዩዋን እና ከዶላር ውጭ እንዲሆን አድርጋለች። አሁን ደግሞ ከላቲን አሜሪካዋ ባለ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ከሆነችው ብራዚል ጋር ዶላርን ላለመጠቀም ተስማምታለች ሲል ኤኤፍፒ ዘግቧል።

የብራዚሊያ እና ቤጂንግ አዲስ የንግድ ስምምነት ዶላርን በመተው በየራሳቸው ገንዘቦች ለመጠቀም ተስማምተዋል ተብሏል። የቻይና እና ብራዚል ዓመታዊ የንግድ ልውውጥ ከ150 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደደረሰ ተጠቅሷል።

ሁለቱ የብሪክስ መሥራች ሀገራት በተለይም አዲሱ ፕሬዚዳንት ሉላ ዳ ሲልቫ በምርጫ ማሸነፋቸው ለሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሻሻል አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሏል። ሩሲያ ከቀጣዩ ክረምት ወራት ላይ ከሚካሄደው አፍሪካ-ሩሲያ ጉባኤ በኋላ የንግድ ግንኙነቷን ከዶላር ውጪ እንደምታደርግ ይጠበቃል።

ብዙ የዓለም ሀገራት በውጭ ምንዛሪ እጥረት እየተፈተኑ ሲሆን ከዶላር ውጪ የሚደረጉ የንግድ ልውውጦችን ብዙ ሀገራት እንደሚመርጡት ይጠበቃል። ጎረቤት ሀገር ኬንያ በዶላር እጥረት ምክንያት ከሳውዲ ዓረቢያ ጋር የነዳጅ ግብይቷን በሽልንግ ለማድረግ መስማማቷን አስታውቃለች።

## ሩሲያ ምግብ ለሰሜን ኮሪያ ሰጥታ በምላሹ ጦር መሳሪያ ልትቀበል መሆኑን አሜሪካ ገለጸች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ምግብ በጦር መሣሪያ ለመለወጥ ልዑካን ቡድን ወደ ሰሜን ኮሪያ ልትልክ መሆኗን የአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ ተናገሩ።

ቃል አቀባዩ በሰሜን ኮሪያ እና በሩሲያ መካከል የሚደረግ ማንኛውም የጦር መሣሪያ ስምምነት የተባበሩት መንግሥታትን የጸጥታ ምክር ቤት ውሳኔዎችን ይጥሳል ብለዋል።

አሜሪካ ከዚህ ቀደም ሰሜን ኮሪያ በዩክሬን ለሚገኘው የሩሲያ ጦር እና ለሩሲያ ተቀጣሪ ዋግነር ግሩፕ መሣሪያ ታቀርባለች የሚል ክስ አቅርባ ነበር። ፒዮንግያንግ ግን የቀረበባትን ክስ ውድቅ አድርገዋለች።

የደኅንነት ቃል አቀባዩ በሰጡት መግለጫ ሩሲያ እና ሰሜን ኮሪያ ስለሚያደርጉት ስምምነት አሜሪካ አዲስ መረጃ አላት ብለዋል። “ሩሲያ በምግብ ጥይት ለመለወጥ ወደ ሰሜን ኮሪያ ልዑክ ልትልክ እንደሆነ አውቀናል” ብለዋል።

ቃል አቀባዩ ጨምረውም አሜሪካ ሁኔታውን እና የተባለውን ስምምነት በአንክሮ እየተከታተለች እንደሆነም ገልጸዋል።

ሰሜን ኮሪያ በዓለም ላይ ድሃ ከሆኑ አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን እንደ ከአውሮፓውያኑ 1990 አጋማሽ እስከ መጨረሻው ድረስ የተከሰተውን የከፋ ረሃብን ጨምሮ ለአስርት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት አጋጥሟታል።

የካቲት ወር ላይም ባለሙያዎች በዓለም ላይ አምባገነን ከሆኑ መንግሥታት አንዱ የሆነውን የሰሜን ኮሪያ መንግሥት በአየር ንብረት ለውጥ፣ ጥብቅ በሆነ የድንበር ቁጥጥር እና በዓለም አቀፍ ማዕቀብ ምክንያት የምርት እጥረት በማጋጠሙ አስከፊ የሆነ የምግብ ቀውስ እንደሚከሰት አስጠንቅቀው ነበር።

ከደቡብ ኮሪያ ባለሥልጣናት የተገኘ የሳተላይት ምስል እንደሚያሳየው ሰሜን ኮሪያ በ2022 ከ180 ሺህ ቶን ያነሰ ምግብ ያመረተች ሲሆን ይህም ከቀደመው



ዓመት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። ሐሙስ ዕለት የአሜሪካ ግምጃ ቤት በሰሜን ኮሪያ እና በሩሲያ መካከል እንደ ደላላ ሆኖ ሲያገለግል ነበር የተባለ ስሎቫኪያዊ ግለሰብን በጥቁር መዝገብ ላይ መዝግቧል።

ግምጃ ቤቱ እንዳለው የ56 ዓመቱ ግለሰብ አሾት ሚክርይቼቭ፣ በ2022 መጨረሻ እና በ2023 መጀመሪያ ላይ ሰሜን ኮሪያ ወደ ሩሲያ መሣሪያ ለመላክ የሚያስችላትን ስምምነት ሲያስተባብር እና ሽያጭ ሲያመቻች ነበር። በምላሹም ፒዮንግያንግ ጥሬ ገንዘብ፣ አውሮፕላን፣ ቁሳቁሶችና ጥሬ እቃዎችን ተቀብላለች ብሏል።

በማዕቀብ ጥቁር መዝገብ ውስጥ መግባት ማለት የአሜሪካ የንግድ ተቋማት ከሚክሪቼቭ ጋር ግንኙነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ሲሆን በአሜሪካ ያሉት ንብረቶቹ በሙሉ እንዲታገዱ ያደርጋል።

የምዕራባውያኑ ማዕቀብ ሩሲያ በዩክሬን ጦርነት የተጠቀመችውን እና የወደሙባትን የጦር መሣሪያዎች ለመተካት የሚያስችላት አቅም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ከዚህም በተጨማሪ ማዕቀቡ ሩሲያ የጦር መሣሪያ ለማግኘት ፊቷን ወደ ሌሎች ሀገራት እንድታዞር አስገድዷታል። ባለፈው ዓመት ታኅሣሥ ወር ላይ አሜሪካ ኢራን ዋና የሩሲያ ጦር ደጋፊ መሆኗን ገልጻ እንደነበር የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# እምቢታ ማንን ገደሰ ?

**ሰሚራ በርሄ**

በማኅበረሰባችን ውስጥ ልክ እንደሌሎቹ ባሕሎቻችን የምንገለፅበት አልያም ብዙዎቻችንን የሚያመሳስለን ነገር ነው፡፡ በእንግሊዘኛ ቋንቋ courtesy ይሰኛል፡፡ ትርጉሙ ይበልጥ ሲብራራ ደግሞ መልካም እርዳታ ይባላል፡፡ ሆኖም የሚደረገው መልካም እርዳታ ከራስ ሙሉ ፍላጎት ሳይሆን ሰዎች ምን ይሉኛል ብሎ ከመጨነቅ አልያም ከማፈር ይመነጫል ይለናል የይሉኝታ ጭብጥ ሀሳብ፡፡

ይሉኝታ በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ትልቅ ቦታ እንደመስጠት አልያም እንደማክበር ተደርጎ ይወሰዳል። ለረጅም ጊዜ ተለማምድነው የኖርነው ባሕሪ ውጤትም ነው። ይሉኝታ የሚያጠቃው ሰው በማኅበረሰብ ውስጥ ምስጉን፣ የመልካም ባሕሪ ባለቤትና ትሑት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን ነገሩን ከዚህ አስተሳሰብ ወጣ ብለን ከተመለከትነው ‹‹ይሉኝታ ማንን ይጠቅማል?›› ብለን መጠየቅ ግድ ይለናል፡፡

ምክንያቱም ይሉኝታ መልካም እርዳታ ከሚለው አጭር ማብራሪያ በዘለለ እኛ በምንሠራው ፣በምንናገረው፣ አለፍ ሲልም በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ሌሎች ሰዎች ጣልቃ እንዲገቡ መፍቀድ ወይም በሌሎች ሰዎች ተፅዕኖ ስር ራሳችንን መጣል ከሚለው ትርጓሜ ውጪ ሌላ ማብራሪያ ስለሌለው ነው።

ይሉኝታ ሰዎች ገና አስተያየት ሳይሰጡን ምን ይሉን ይሆናል በሚል ስጋት የምንፈፅመው ድርጊት ወይም የምናሳየው ባሕርይ ነው፡፡ ይህ ባሕርይ ታዲያ በአብዛኛው እኛ ከምንኖርበት አካባቢ በተለያየ ጊዜ እና ሁኔታ በአኗኗራችን ውስጥ በመላመድ ይመጣል፡፡ ለሌሎች ሰዎች ካለን ክብር የተነሳ ስለሌሎች ሰዎች ስሜት እና ባሕሪ ያልተሰጠንን ኃላፊነት ከመሸከምም ይሉኝታ ይመነጫል፡፡

**ሰዎች ይሉኝታ የሚያጠቃቸው መቼ ነው?**

በተደጋጋሚ የተሠሩ የማኅበረሰብ ሳይንስ ጥናቶች የሰው ልጅ ተወልዶ ካደገ በኋላ የሚኖረው ባሕሪ ፣ ስብዕና በአብዛኛው የሚገነባው ከውልደቱ እስከ አስር ዓመቱ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን እነዚህ ባሕሪያት ለቀሪ ሕይወቱ የሚጠቀምበት እና ከዛ በኋላ ለመቀየር አስቸጋሪ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ አንድ ሰው በወጣትነቱ /አስር ዓመታት ውስጥ/ የሚያዳብረው ስብዕና በሚቀጥለው ሕይወቱም የእርሱ ማንነት ሆኖ የሚዘልቅ ማለትም እሱነቱን የሚገልፅ እንደሆነ እነዚሁ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ወላጆች የልጆቻቸውን ሕይወትን እንዲረዱ ሥነ-ምግባር የሚያስተምሩበት መንገድ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ያሳያል ።

በሀገራችን ደግሞ በሁሉም ጫፍ ተመሳሳይ የልጆች አስተዳደግ መንገድ አለ፡፡ ለምሳሌ ልጆች በልጅነታቸው ለሚያቀርቡት ሀሳብ ተቀባይነት የሌለው ከነተረቱ ‹‹ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም›› እንደሚባለው እንግዳ ሲመጣ ልጆች ቦታ ይለቃሉ፡፡ ልጆች የወላጆቻውን ቁጣ እንዲሁ ከዓይናቸው ብቻ ተረድተው እነርሱ የሚፈልጉትን የሚያደርጉበት ጊዜም አለ፡፡ ‹‹ሰው ቤት ተኺዶ ምግብ አይበላም›› ፣ ‹‹ታላቅ ሲያዝ እምቢ አይባልም›› ፣ ቀደም ቀደም አትበል/አትበይና መሰል አነጋገሮች የልጅነት ትዝታዎች ናቸው።

ልጆች በቤተሰቦቻቸው ተወዳጅ ለመሆን እና እነሱን ለማስደሰት ሲሉ እነዚህንና ሌሎች የተግሳፅ አዘል ትምህርቶችን ያለፍላጎታቸውና ስሜታቸው ሳይፈቅድ ይለምዷቸዋል እድሜያቸው እየጨመረ ሲመጣ ደግሞ ከሰዎች ጋር ተስማምቶ ለመኖር ሲሉ የሚያደርጉት ቀላል ጥበብ እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ውስጥ ድብቅ መሆንንና ማስመሰልን ባሕሪያቸው ያደርጉታል፡፡

አንድ ሰው በውስጡ ለሚገነባው የስብዕና መገለጫዎች መጥፎም ይሁን ጥሩ ባሕሪን ለመገንባት ከወላጆች ቀጥሎ ኅብረተሰቡ ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ሲሆን ትውልድን በመቅረፅ ረገድም ሚናው የጎላ ነው። ለአብነትም በማኅበረሰብ ውስጥ ተወዳጅ እና የሚከበር ሰው ብዙውን ጊዜ የሚኖርበትን ማኅበረሰብ የሚመስል አልያም ሕጉን የሚያከብር ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ በባሕሪው ሙገሳን አብዝቶ የሚወድ በተቃራኒው ደግሞ

> **ይሉኝታ መልካም እርዳታ ከሚለው አጭር ማብራሪያ በዘለለ እኛ በምንሠራው፣በምንናገረው፣ አለፍ ሲልም በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ሌሎች ሰዎች ጣልቃ እንዲገቡ መፍቀድ ወይም በሌሎች ሰዎች ተፅዕኖ ስር ራሳችንን መጣል ከሚለው ትርጓሜ ውጪ ሌላ ማብራሪያ ስለሌለው ነው**

ነቀፌታንና ትችትን አብዝቶ የሚጠላ በመሆኑ በዚህ አሳሪ ባሕል ውስጥ ራሱን ያገኘዋል፡፡

ይሉኝታ በእኛ ማኅበረሰብ ውስጥ በተለያየ መንገድ ከመገለፁ በፊት የአንድ ሰው ባሕሪ ፣ ማንነት ውስጥ እንዲገነባ የሚያደርጉ ሌሎች ባህሎች እና ልማዶች በውስጡ ይይዛል፡፡ ይህም ለታላላቆች ካለን ክብር፣ ልጆች ለቤተሰቦቻቸው ፣ ወጣቶች በእድሜ ለሚበልጧቸው ከሚሰጡት ክብር ይመነጫል፡፡ በአጠቃላይ ለሌሎች የምንሰጠው ቦታ እንደግለሰብ እያደገ ሲመጣ እና ከአቅራቢያችን ባሉ ሰዎች ጫና ሲደረግበት በውስጣችን ካለው በተጨማሪ ሌላ ባሕሪ እንድንገነባ ያደርገናል፡፡ ይህም ይሉንተኛ ያስብለናል፡፡ ከዚህ በሁላችንም ዘንድ ቀስ በቀስ የተገነባው መነሻው አክብሮት የሆነ ባሕል ቢሆንም መድረሻው ግን ወደ ይሉኝታ ተቀይሮ ባሕሪው በሰዎች ላይ የራሱን ጉዳት ያስከትላል፡፡

በዚህ ጊዜ ለምንወዳቸውና ለሚቀርቡን ሰዎች ለሚጠይቁን ነገር ሁሉ እሽታን እንመርጣለን፤ አልያም ለምንጠየቀው እርዳታም ሆነ ሌላ ነገር ሳናውቀውም እያወቅን በራሳችን እምቢተኛነትን እናጣለን፡፡ ሰዎችን ላለማስቀየም ስንል ማድረግ የማንፈልገውን ነገር ለነዛ ሰዎች እናደርጋለን፡፡ ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ የራሳችን የሆነን ነገር አሳልፈን እስከመስጠት እንደርሳለን፡፡ በዚህም የይሉንተኝነት ባሕሪ እናዳብራለን፡፡ እየበሰልን ስንመጣ ደግሞ ነገሩ በተደጋገመና ይህንን ችግር በራሳችን ላይ ባስተዋልነው ቁጥር ለራሳችንን ያለን ቦታ ዝቅ ይላል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ራሳችንን ወደመውቀስ እንገባለን፡፡ ይህ ደግሞ ለከፋ የሥነ-ልቦና ችግር ያጋልጠናል ።

**የይሉኝታ ውስታው/ጥቅሙ/**

የምንኖርበት ዓለም የራሷ ሕግ እንዳላት ሁሉ ሀገርም የሚመራበት ሕግ አለ፡፡ በተመሳሳይ ቤተሰብ ከፍ ሲል ማኅበረሰብም አብሮ የመኖር ምክንያት የሆኑ፤ ያልተፃፉና በሰነድ ያልተመዘገቡ ሕጎች አሉ፡፡ እነዚህ ሕጎችም ናቸው በአብሮነት እንድንቆይ የሚያደርጉን። እንግዲህ በዚህ ውስጥ ያን ያህል የማንለውጠው ምናልባትም የማንፈልገው አልያም ደግሞ የማንጎዳበት ነገር ሲያጋጥመን በይሉኝታ እንተወዋለን፡፡

አንዳንድ ጊዜ ጊዜያቸውን ካልጠበቁ እና ጉንጭ አልፋ ብቻ ለሆኑ ክርክሮች ቦታ መስጠት ስለማይኖርብን አልያም ደግሞ ያለንን በጎ ነገር ከማጠልሸት ውጪ የሚጨምሩት ነገር ሳይኖር ሲቀር እንዲሁ ነገሮቹን እንተዋቸዋለን። ይህ ደግሞ በአንድ ሆነን የመኖራችን ሚስጥር ተደርጎ ሊታይ እና ጠቀሜታ አለው ሊባል ይችላል፡፡ ለዚህ አስረጂ ሊሆን የሚችል ሀሳብ ላቅርብላችሁ፡፡

ሥራ ለመሥራት ወይም ጥናት ለማካሄድ አልያም ለጉብኝት ወደ አንዱ የሀገራችን ክፍል ወደሆኑት ሐመር ወይም አፋር ብትጓዙ የነርሱን ባህልና አኗኗር ማጣጣል አልያም ስህተት ነው ብሎ ለማስረዳት መሞከር ተገቢ አይሆንም፡፡ ስለዚህም ጥናት አድራጊው ሥራውን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እነርሱን ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከመጥፎ ይልቅ ጥሩ ጎኑ ያመዝናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዕለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ ከብዙ አዳዲስ ሰዎች ጋር እንገናኛለን፤ እንተዋወቃለን። የተለያዩ ሀሳቦችንም እንለዋወጣለን፡፡ በዚህ የግንኙነት ሂደት ለጓደኝነት የምንመርጣቸው ሁሉ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ምናልባትም ፍፁም የማንስማማበት እና የማንቀበለው ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ከብዙ አልፊ ክርክሮች በኋላ ሀሳቡን ለማይቀይረው ጓደኞችን ስንል ሀሳቡን ሳይቋጭ እናልፈዋለን፡፡ ታዲያ በዚህ ውስጥ መቻልን እና መተውን ተማርን ማለት አይደል! ነገር ግን ይህም ቢሆን ሊሆን የሚችለው እንዲህ ማድረጉን ላወቀበት ነው።

**ሌላኛው ይሉኝታ**

ከላይ ከተጠቀሰው በተለየ መልኩ ደግሞ የሰዎች ባሕሪ የሚገነባበት መንገድ ይኖራል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከገጠማቸው ችግር አልያም መጥፎ አጋጣሚ ተነስተው ጥሩ ነገርን ሲቀስሙ ሌሎች ግን እሾህን በእሾህ የሚለውን መርሕ ይከተላሉ ። በሕይወት ጉዟችን ውስጥ ካወቅናቸው ሰዎች መካከል ቦታ የሰጠናቸው በምላሹ ትኩረት ሳይሰጡን ሲቀር እኛም የተከተልነው መንገድ እንደማይሠራ ስናውቅ እነርሱ ያደረጉትን በማድረግ አፀፋውን እንመልሳለን፡፡ ይህ ነው እንግዲህ እሾህን በእሾህ የሚያሰኘው፡፡

በዚህ ሩጫ በበዛበት ዘመን እንዲህ አይነቱ ባሕሪ የሚታይባቸው ሰዎች ከሰዎች ጋር ማውራትንና ትኩረትን ይሻሉ፡፡ እናም በጊዜ ሂደት ትኩረት ሲነፈጉ ይህን ባሕሪ በመላበስ ለነገሮች ትኩረት የማይሰጡ፣ አይተው እንዳላየ የሚያልፉና ግዴለሽ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ‹‹አርፈህ ኑሮህን ኑር ፣ ምን አገባኝ ፣አልደረሰብኝ!›› በሚሉ መሸንገያ ቃላት ተሸፍነው ቆይተው የአንድ ሰው ቋሚ ባሕሪ ከመሆን አልፈው የማኅበረሰብ ችግር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ሰው ሆይ በአንድ የመኖሪያ መንደር ውስጥ ባልተገባ ቦታ ላይ የተጠራቀመ ቆሻሻ ብትመለከት ‹‹ምን አይነት ሰፈር ነው?›› ከማለትህ በፊት አንድ ቀን በዚያ አካባቢ ስታልፍ ከኪስህ ወይም ከቤትህ ያወጣኸውን ቆሻሻ አለመጣልህን አረጋግጥ። ይህ ደግሞ የሚያመጣቸው የማኅበረሰብ ጣጣዎች በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአካባቢ በቆሻሻ መበከል፣ የስርቆት ወንጀል ከቀን ወደቀን እየጨመረ መምጣት ፣ በሕፃናት እና በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለ ፆታዊ ጥቃት እና ሌሎችም ለዚህ ማሳያ ናቸው፡፡

**ምን ይሻላል?**

**1ኛ. ትኩረት መስጠት**

በየትኛውም የሕይወት መንገድ ውስጥ የምንቀሳቀስባቸውና የምንገኝባቸው ቦታዎች ብሎም የምናጋራቸው ሀሳቦች የኛ ውሳኔ የታከለባቸው መሆኑን ባለመርሳት ሃሳባችን እና ልክ ናቸው ከማለታችን በፊት ደጋግመን ማሰብ ይኖርብናል። ይህም ለአንድ አካል ብቻ የተሰጡ እና ነውር የሚመስሉ ነገሮችን ለምን? ብሎ የመጠየቅ ባሕልን እንድናዳብር እና ባመንበት ነገር ላይ ብቻ የመወሰንን አቅም እንድንለማመድ ያደርገናል። ሙብታችን መሆኑንም ጭምር እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

ይህ በራሳችን ሕይወት ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው ሆኖ ኃላፊነት ለሚሸከሙ ሰዎች ለቁጥር ማሟያ እጃቸውን የሚያወጡ እና በሌሎች ተፅዕኖ ስር ወድቀው የብዙኃኑን ድምፅ የሚቀበሉ ሳይሆኑ ሀሳባቸውን አዋጥተው በበለጠው ላይ ተስማምተው የሚወስኑ መሪዎች በአነስተኛም ሆነ ከፍ ባሉ ዘርፎች ላይ እንዲፈጠሩና እንዲበራከቱ ያደርጋል ።

**2ኛ. የድርሻችንን መወጣት**

ድርሻን መወጣት ሲባል ከታችኛው የማኅበረሰብ ክፍል ጀምሮ እስከላይኛው የሥልጣን እርከን ድረስ ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ድርሻን መወጣት ልጅ፣ አዋቂ፣ ሀብታም፣ ደሃ፣ ሴት፣ ወንድ አይለም፡፡ ለዚህ አስረጂ ይሆን ዘንድ አንድ ታሪክ ላቅርብላችሁ፡-

በአንድ ሀገር የሚኖሩ አንድ ንጉሥ የሕዝቡን የወተት ችግር ለመፍታት አንድ ትልቅ የወተት ገንዳ እንዲዘጋጅ አዘዙ፡፡ የወተት ገንዳውም በታዘዘው መሠረት ተዘጋጀ። ከዚያም በአካባቢው የሚኖረውን ሰው በሙሉ እያንዳንዳቸው አንድ ብርጭቆ ወተት ወደገንዳው እንዲጨምሩ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡ ሕዝቡም እንደታዘዘው ማድረግ ጀመረ፡፡ በአካባቢው የሚኖር አንድ ሰው ግን ሁሉም ሰው ወተት የሚጨምር ከሆነ የኔ አንድ ብርጭቆ ውሀ ምንም ለውጥ አያመጣም በማለት ሄዶ የወተት ገንዳ ውስጥ አንድ ብርጭቆ ውሀ ይጨምራል፡፡ ሆኖም በመጨረሻ የወተት ገንዳው ሲታይ በውስጡ የነበረው ወተት ሳይሆን ሙሉ ውሀ ነበር።

አንድን ነገር ለመደገፍ አልያም ለመቃወም የሌሎች ሰዎች ተሳታፊነት ወይም የአብላጫው ድምፅ መሰማት ሳይሆን የእኛ በነገሩ ማመን ትልቅ ለውጥ ያመጣልና ይመለከተኛል ለማለት የሌሎች ሰዎችን እግር መከተል አይጠበቅብንም፡፡ ‹‹ሁሉም ከሄደበት ሁሉም የተው›› እንደሚለው ተረቱ ለራሳችን ዋጋ በሰጠን ቁጥር በየትኛውም ቦታ ብንጓዝ የሚኖረንን ዋጋ እንረዳለን፡፡ ይህ ደግሞ የሚጠበቅብንን፣የምንችለውንና የድርሻችንን እንድንወጣ ያደርገናል፡፡ ይህ አበርክቶ ታዲያ ከእኛ አልፎ ለሌሎች ይተርፋል፡፡

# የጥንዶቹ ስኬት-በፋሽን ዲዛይን ኢንዱስትሪው

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ሌባ የማይሰርቀው ትልቅ ሃብት ቢኖር «የእጅ ሙያ» ነው:: የእጅ ሙያ ያለው ሰው ምንም ቢያጣ ሙያውን ተጠቅሞ ኑሮን ማሸነፍ እንደሚችል ይታመናል:: በእጅ ያለ ሙያ ከባለቤቱ ጋር አብሮ ያረጀ ይሆናል እንጂ፤ እንደማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ከእጁ አልያም ከደጃፉ ሌባ ሊሰርቀውም አይችልም::

እርግጥ ነው በቀደመው ጊዜ ሰዎች ለእጅ ሙያ የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ የነበረ መሆኑ ዛሬም ድረስ ለሚታየው የሥራ ባህላችን ደካማነት ዋና ምክንያት ነው። ይሁንና አሁን አሁን ብዙዎች ለእጅ ሙያ ትልቅ ትኩረት ሲሰጡና ሲጠቀሙበት ይስተዋላል::

ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣው የእጅ ሙያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሁን ላይ ከዘመኑ ጋር እሽቅድድም የያዘ ይመስላል:: ይህ ሙያ ከዘመኑ ጋር እየዘመነ መጥቷል፤ የእጅ ሙያ ያላቸው ወገኖች በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በሽክላ፣ በብረታ ብረት ሥራ፣ በአገር ባሕል አልባሳት ማምረት ወይም ማዘጋጀት፣ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችና ጌጣ ጌጥ ማምረት ውስጥ በስፋት ተሰማርተው መታየትም ጀምረዋል ምርታቸውም ተፈላጊነቱ እየጨመረ ነው::

መንግሥት እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች በመደገፍ በኩል ሰፋፊ ሥራዎችን ሠርቷል:: መንግሥት በዘረጋው የአሠራር ሥርዓትም ሙያተኞች ከሙያቸው ጋር መገናኘት በመቻላቸው ዘርፉ ለሀገር እና ለሕዝብ አበርክቶ እያደረገ ይገኛል::

በዛሬው የስኬት አምድ እንግዳችንም መንግሥት ለተለያዩ የሥራ ዘርፎች በተለይም ለእጅ ሙያ የሰጠውን ትኩረት መሠረት አድርገው እውቀታቸውን ከሙያው ጋር ማገናኘት ከቻሉ መካከል “የኩል ዲዛይን” መሥራቾችን ይዘንላችሁ ቀርበናል:: «ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ» እንዲሉ ኩል ዲዛይን በሁለት ባለሙያዎች ተመሥርቶ ለስኬት በቅቷል::

ባለሙያዎቹ በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ጥንዶች ናቸው:: ጥንዶቹ ገና ተማሪ እያሉ በትምህርት ያገኙትን ዕውቀት በሥራ ልምድ አዳብረው ሥራውን የማስፋት ዕቅድ ነበራቸው:: ምክንያቱም ሰዎች የተማሩትን በሥራ ልምድ ማዳበር ከቻሉ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት ይችላሉ:: ለሌሎችም ይተርፋሉ የሚል ጽኑ እምነት አላቸውና::


ጥንዶቹ እትብታቸው አዲስ አበባ እምብርት ላይ አይቀበር እንጂ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያደጉትና የተማሩት በመዲናዋ ነው:: የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካቴድራል የተከታተለው አቶ እሸቱ ደጉ ኩል ዲዛይንን የመሠረቱት ከባለቤቱ ሳምራዊት አዲሱ ጋር መሆኑን ይገልጻል:: ጥንዶቹ ወደ ዘርፉ ከመግባታቸው አስቀድሞ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርቻውን የተከታተሉ ሲሆን፤ አቶ ደጉ በቴክስታይል ኢንጅነሪንግ፣ ባለቤቱ ወይዘሮ ሳምራዊት ደግሞ በፋሽን ዲዛይን ትምህርታቸውን ተከታትለው አጠናቀዋል::

የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ባጠናቀቁ ማግስት ሁለቱም በየፊናቸው በሙያቸው ተቀጥረው ሠርተዋል። «ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳል» እንዲሉ ሆነና አቶ እሸቱ፤ በጋርመንትና ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ውስጥ ለስድስት ዓመታት ሲሠራ ባለቤቱ ሳምራዊት ደግሞ የፋሽን ዲዛይን መምህርት በመሆን በተለያዩ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ውስጥ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት አስተምራለች::

ዕውቀትን በሥራ ልምድ ያካበቱት እነዚህ ጥንዶች ወትሮም ሥራቸውን ማስፋፋት ዓላማቸው ነውና የፋሽን ዲዛይን እና የቴክስታይል ኢንጅነሪንግ ዕውቀትን በሥራ ልምድ አስደግፈው ኩል ዲዛይንን መመሥረት ችለዋል::

ኩል ዲዛይን በጨረታ ተወዳድሮ ከሚያገኛቸው የተለያዩ የደንብ ልብሶች የስፌት ሥራ በተጨማሪ ዘመናዊና ባሕላዊ አልባሳትንም ያመርታል:: ድርጅቱ አልባሳትን አምርቶ ለገበያ ከማቅረብ ባለፈም ሙያዊ ሥልጠና በመስጠት ባለሙያዎችን እያፈራ ይገኛል::

ዕውቀትና ልምዳቸውን ይዘው ድርጅቱን ለማቋቋም የተነሱት እነዚህ ጥንዶች መንግሥት ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያመቻቸውን ዕድል አሟጠው መጠቀም እንደቻሉና ዕድለኛም እንደሆኑ አቶ እሸቱ ይናገራል:: ሰባት ካሬ ሜትር ስፋት ያለው የማምረቻ ቦታን ከመንግሥት ያገኙ



አቶ እሸቱ ደጉ



ወ/ሮ ሳምራዊት አዲሱ

ሲሆን፤ አዲስ ካፒታል ከተባለ ድርጅት ደግሞ መስፊያ ማሽኖችን በብድር ማግኘት ችለዋል::

በወቅቱ ለዲዛይን ሥራቸው የሚያስፈልግ ሁለት ማሽንና የተመዘገበ 300 ብር መነሻ ካፒታል ይዘው ወደ ሥራ እንደገቡ የሚያስታውሰው አቶ እሸቱ፤ ባለቤቱን ጨምሮ ሙያው በእጃቸው በመሆኑ ከሰው ከሚጠብቁት 100 ብር በራሳቸው ድርጅት ሠርተው የሚያገኙት አንድ ብር የተሻለ ውጤት ያመጣል የሚል ትልቅ ሕልም እንደነበራቸው ይናገራል::

እነ ደጉ ያነገቡትን ትልቅ ሕልም ዕውን ለማድረግ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ቀን ከሌሊት በማምረት ለገበያ ማቅረባቸውን ቀጠሉ:: ጥንዶቹ ሁለት ማሽን ብቻ ይዘው የተለያዩ ዘመናዊና ባሕላዊ እንዲሁም የደንብ ልብሶችን በጥራት ማምረት በመቻላቸው ገበያው ውስጥ በስፋት መግባት ቻሉ:: ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የመጣውን ሥራ ይበልጥ ማሳደግ የሚቻልበትን መንገድ በመቀየስ ቀድመው የወሰዱትን ብድር መልሰው ተጨማሪ የስፌት ማሽኖችን እና ሠራተኞችን አንድ ሁለት እያሉ አበራከቱ::

ከማምረት ባለፈም አምራች የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሥልጠና ማዕከል መክፈት ቻሉ። መንግሥት ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የሰጠው ትኩረት ለእዚህ ሥራቸው መልካም ዕድል ይዞ መጣ:: ይህን ተከትሎም በርካታ ተቋማት በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እየፈለጉ መምጣታቸውን የጠቀሰው አቶ እሸቱ፤ ወደ ሥልጠናው ለመግባት ይበልጥ ያነሳሳቸው ይሄው ምክንያት እንደሆነ ይናገራል::

እነ አቶ እሸቱ በልብስ ስፌት፣ በፋሽን ዲዛይንና በተዛማጅ ዘርፎች ለሙያው ፍቅርና ፍላጎት ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች የአጭር ጊዜ ሥልጠና እየሰጡ ይገኛሉ:: ሥልጠናው በዋናነት የሚሰጠው ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሲሆን የሦስት ወር፣ የስድስት ወርና የአንድ ዓመት ጊዜን ይፈልጋል::

የአንድ ዓመት ጊዜ ከሚጠይቀው መደበኛ ሥልጠና በተጨማሪም ኦቨር ሎክና ሌሎች ጥቃቅን የሚባሉ የሙያ ዘርፎችን መሰልጠን የፈለገ ደግሞ በ15 ቀናት ውስጥ መሠረታዊ የሆነውን እውቀት ለመጨበጥ መሰልጠን ይችላል:: ለአብነትም አንድ ሰው ወደ ሥልጠና ማዕከሉ መጥቶ የኦቨርሎክ ሙያን ብቻ መሰልጠን እፈልጋለሁ ካለ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ሰልጥኖ በፋብሪካዎች መቀጠርና የሥራ ባለቤት መሆን እንደሚቻል አቶ እሸቱ አጫውቶናል::

አቶ እሸቱም ሆነ ወይዘሮ ሳምራዊት አልባሳትን ከማምረትና ከማሰልጠን በተጨማሪም የእጅ ሙያ ባለቤት እንደመሆናቸው ለድርጅቶች የማማከር አገልግሎትም ይሰጣሉ:: በተለይም የቴክስታይል ኢንጂነሪንግ ምሩቅ የሆነው አቶ እሸቱ፤ በዘርፉ የተሠማሩ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን በጥራትና በፍጥነት አምርተው ውጤታማ መሆን እንዲችሉና ሠርቶ መለወጥ የሚያስችላቸውን የክህሎት ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል። ድርጅቱም በሚያገኘው ሙያዊ የምክር አገልግሎት ማሻሻያዎችን በማድረግ ለለውጥ ይተጋል:: ለአብነትም ኩል ዲዛይን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏት አገር እንደመሆኗ የአለባበስ ባሕሉም በዛው ልክ ሰፊ ቁጥር አለው:: ስለዚህ ይህን እምቅ ሃብት አውጥቶ መጠቀም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታዎችን ከማስገኘት ባለፈ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ የማስተዋወቅ ዕድሉ ከፍተኛ ነው

የመንግሥት ተማሪዎች ዩኒፎርምን ከዲዛይን ጀምሮ አማካሪ ወይም ዲዛይነር በሚል የቁጥጥር ሥራ ሠርቷል::

አንድን ልብስ በጥራት፣ በፍጥነትና ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ማቅረብ በገበያ ውስጥ ተፈላጊነትን ይጨምራል የሚለው አቶ እሸቱ፤ የገበያ መዳረሻቸው በስፋት መርካቶ እንደሆነም ይናገራል፤ የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦችም ደንበኞቻቸው መሆናቸውም ሌላው ገበያ ውስጥ በስፋት መግባት እንዲችሉ እንዳደረጋቸው ይናገራል::

ሁለት ማሽኖችን ይዞ በሰባት ካሬ ሜትር ቦታ ወደ ሥራ የገባው ኩል ዲዛይን፤ የፋሽን ዲዛይን፣ የስፌት ሥራውንና ሥልጠናውን አንድ ሁለት እያለ ማሳደግ ችሏል:: በአሁኑ ወቅት የመስፊያ ማሽኖቹን 65 ማድረስ የቻለ ሲሆን፤ የማምረቻ ቦታውም 80 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታን ይሸፍናል:: 300 ተብሎ የተመዘገበው መነሻ ካፒታልም ዛሬ ላይ ከሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ ተመዝግቧል:: ለሁለት የተጀመረው ሥራ አሁን 47 ለሚደርሱ ሠራተኞች በቋሚነት የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል::

ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ከፋሽን ዲዛይንና ስፌት ሥራው ጎን ለጎን በሚሰጡት ሙያዊ ሥልጠናም በርካቶችን ሌባ የማይሰርቀው የሙያ ባለቤት ማድረግ ችለዋል:: በተለይም ሙያው እንዲኖራቸው ፍላጎት እያላቸው በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ወደ ኋላ የቀሩ የተለያዩ የማኅበረሰቡ አካላትን የሙያ ባለቤት ማድረግ የቻሉ ሲሆን፤ ለአብነትም ከስደት ተመላሽ የሆኑ ዜጎች፣ የገቢ ምንጭ የሌላቸውና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያሉ ዜጎች የዕድሉ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል::

አቶ እሸቱ የኩል ዲዛይን ድርጅት በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ስለሚገኝ እገዛ የሚስፈልጋቸውን ዜጎችንም ከዚያው ከወረዳው እንደሚያገኝ ያስረዳል። ተደራሽነትን ለማስፋት በቅርቡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ሁለተኛውን ቅርንጫፍ እንደከፈቱም ይናገራል። በዚህ አካባቢ ለሚገኙ አቅም ለሌላቸው ዜጎችም ተመሳሳይ እገዛ እንደሚያደርጉ ይገልፃል:: ከድጋፋቸው ባሻገር ተቋሙ በዲዛይን፣ በስፌትና በሌሎች ዘርፎች መደበኛ ሥልጠናውን በአምስት ፈረቃ እየሰጠ ይገኛል:: በአንድ ፈረቃ 30 ሰልጣኞችን በማሰልጠን በአንድ ቀን እስከ 150 ለሚደርሱ ተማሪዎች ሥልጠናው ይሰጣል::

በኩል ዲዛይን የሰለጠኑ ሠልጣኞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወደ ሥራው ዓለም የሚቀላቀሉ እንደሆነ የገለጸው አቶ እሸቱ፤ በተማሪዎች ዩኒፎርም ላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር መሥራቱ ከከተማ ጋርመንቶች ጋር የመተዋወቅ ዕድል ፈጥሮለታል:: በመሆኑም ከእነዚህ ጋርመንቶች ጋር በመነጋገር በኩል በዲዛይን የሠለጠኑ ሠልጣኞችን በእነዚሁ ጋርመንቶች ያስቀጥራቸዋል:: በዚሁ ምክንያትም አብዛኞቹ ሠልጣኞች ሥራ የሚይዙ እንደሆነ ነው ያጫወተን::

በተለይም የነጻ ሥልጠና የሚያገኙ ሠልጣኞችን በፍጥነት ወደ ሥራ የሚያስገባቸው መሆኑን ያነሳው አቶ እሸቱ፤ ለአብነትም በ2014 ዓ.ም 34 የሚደርሱ ሠልጣኞች ሠልጥነው የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል:: በነጻ ሠልጥነው ወደ ሥራ ከተሰማሩት 34 ሰልጣኞች በተጨማሪም በመደበኛው የሥልጠና ጊዜ ገንዘብ ከፍለው ከሰለጠኑት 289 ሰልጣኞች መካከል 115 የሚደርሱት ወደ ሥራ የገቡ ስለመሆናቸው ነው አቶ እሸቱ ያስረዳው::

የተለያዩ አልባሳትን አምርቶ ለገበያ ከማቅረብ በበለጠ በሥልጠናው ዘርፍ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ዜጎች በአጭር ጊዜ የሙያ ባለቤት እንዲሆኑና የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው እየሠራ ያለው ኩል ዲዛይን በዘርፉ ውጤታማ መሆን ችሏል:: የፋሽን ዲዛይን ዘርፍ ብዙ ሊሠራበት የሚችል ዘርፍ በመሆኑ ለውጤት ቅርብ ነው የሚለው አቶ እሸቱ፤ በተለይም ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏት አገር እንደመሆኗ የአለባበስ ባሕሉም በዛው ልክ ሰፊ ቁጥር አለው:: ስለዚህ ይህን እምቅ ሃብት አውጥቶ መጠቀም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታዎችን ከማስገኘት ባለፈ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ የማስተዋወቅ ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ ተናግሯል።

የፋሽን ዲዛይን ከሸመና ጀምሮ በአገሪቱ ያለውን ጥሬ ዕቃ አውጥቶ መጠቀም የሚያስችል ዘርፍ እንደመሆኑ ኢትዮጵያን በፋሽን ዲዛይን ኢንዱስትሪው የማስተዋወቅ ሰፊ ዕድል አለ የሚለው አቶ እሸቱ፤ ዘርፉን ይበልጥ ማስፋት እንደሚገባም ጠቁሟል:: ዘርፉ ከቀደመው ጊዜ በተሻለ መንገድ በተማረና በሠለጠነ የሰው ኃይል እየተመራ መሆኑም ለዘርፉ ዕድገት አይነተኛ ድርሻ አለው:: ስለሆነም ኢትዮጵያ እንደ ቻይና፣ ቱርክና ሕንድ ከመሳሰሉ አገራት ተርታ የመሰለፍና ተወዳዳሪ የመሆን ሰፊ ዕድል አላት::


ኩል ዲዛይን ሱፍ ወይም ሙሉ ልብስን ጨምሮ የሴት፣ የወንድና የሕጻናትን የተለያዩ አልባሳት በተፈለገው ዲዛይን፣ በጥራትና በጊዜ እያመረተ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ በመቻሉ ተፈላጊ ነው የሚለው አቶ እሸቱ፤ የፋሽን ዲዛይን ሥራ የፈጠራ ችሎታን የሚያሳድግ በመሆኑ በቀጣይም ፈጠራ የታከለበት ሥራን በማጎልበት ማራኪ፣ ሳቢና የማኅበረሰቡን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴት የጠበቁ አልባሳትን በማምረት ቀዳሚ ለመሆን ይተጋል:: በዚህም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል በማለት ሀሳባቡን ቋጭተዋል::

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# የሕዝብ ጥያቄን የሚመልሰው የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ በሆሳዕና

**መሳኩ ኤርሴ**



ፎቶ፡- በመሳኩ ኤርሴ

የደቡብ ክልል ሀዲያ ዞና ዋና ከተማ ሆሳዕና ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረች ጉምቱ ከተማ ነች። ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በ230 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ሆሳዕና፣ በአሁኑ ወቅት የሀዲያ ዞን ዋና ከተማ ሆና እያገለገለች ትገኛለች፡፡ የአካባቢው የንግድ ማዕከልም ናት፡፡

ከተማዋ ስፋቷ እየጨመረ እና የሕንፃዎች ብዛት እየተበራከቱባትም መጥታለች፡፡ ይህን የሚመጥን መሠረተ ልማት በማሟላት ረገድ ግን ውስንነት እንዳለባት ነዋሪዎቿ ይጠቁማሉ፡፡ ከከተማዋ ነዋሪዎች አንዱ የሆነው ወጣት ወንደወሰን መንሲዶ ከተማዋ እጅግ በሚያስደስት መልኩ እያደገች መሆኗን ጠቅሶ፣ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማት ችግር እንደሚስተዋልባት ይናገራል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የወጣቶች መዝናኛ ማዕከላት፣ የመንገድ እና የውሃ ችግሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በከተማዋ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች እየታዩ ነው ይላል፡፡

የከተማዋን የመንገድ መሠረተ ልማት ለማሟላት እና የሕዝብ መዝናኛዎችን ለመገንባት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች እጅግ የዘገዩ ናቸው የሚል እምነት አለው፡፡ ከከተማዋ ዕድሜ አንጻር ከብዙ አስርት ዓመታት በፊት መሟላት እንደነበረባቸውም ይጠቁማል፡፡ አሁን የመሠረተ ልማቶቹ ግንባታ መጀመሩም በአድናቆት ይመለከታል፡፡ በተለይም የ‹‹ጆሎ ደቀዬ››የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ እና የቤተመጻሕፍት ግንባታ የከተማዋን ወጣቶች የመዝናኛ ችግር የሚቀርፍ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ተማሪ ከበቡሽ ኤርሚያስ በከተማዋ በሚገኝ የግል ኮሌጅ ውስጥ ትማራለች፡፡ በ‹‹ጆሎ ደቀዬ›› የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ ውስጥ ስታነብ ነው ያገኘኋት፡፡ ከዚህ ቀደም በከተማዋ ውስጥ የቤተመጻሕፍት እጥረት ይታይ ነበር፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ አነስተኛ ቤተመጻሕፍቶች ውጪ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ማግኘት ከባድ ነበር የምትለው ተማሪ ከበቡሽ፣ በአሁኑ ወቅት የ‹‹ጆሎ ደቀዬ›› የሕዝብ መዝናኛ ፕሮጀክት አካል ተደርጎ የተገነበው የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ለከተማዋ ሕዝብ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ተናግራለች፡፡ የንባብ ባህልንም እንደሚያሳድግ ጠቁማለች፡፡

የከተማዋ ከንቲባ አቶ ሊሬ ጀማል እንደሚሉት፤ የከተማዋን የመሠረተ ልማት ጥማት ለማርካት የተለያዩ መሠረተ ልማቶች ግንባታ እየተካሄደ ነው፡፡ ከተማዋ እያደገች እና እየሰፋች ቢሆንም የከተማዋን እድገት የሚመጥኑ የመንገድ፣ የውሃ እና የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች በከተማዋ እድገት ልክ አላደጉም፡፡ የከተማዋን እድገትና መሠረተ ልማት እድገት ለማጣጣም ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ በከተማዋ እየተከናወኑ ካሉት ለሕዝቡ አገልግሎት ከሚሰጡ የመሠረተ ልማት ሥራዎች መካከል የመንገድ፣ የውሃ ፕሮጀክት፣ የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ እንዲሁም የወጣቶች መዝናኛና ቤተመጻሕፍት ግንባታ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የከተማዋን የውሃ ችግር ለመቅረፍም በትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡ የከተማዋን ውሃ ችግር ለመቅረፍ ከዚህ ቀደም ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ጥረቶች መካከል ቀደም ሲል የከተማዋን የውሃ ችግር ይቀርፋል ተብሎ ከ‹‹ሙጎ›› ወደ ሆሳዕና የውሃ መስመር ተዘርግቶ ነበር፡፡ ነገር ግን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ባለው የሕዝብ ብዛት ምክንያት ከ‹‹ሙጎ››የመጣው ውሃ የከተማዋ የውሃ ችግር አልተቀረፈም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ወደ ከተማዋ የሚመጡ ሕዝቦች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ የውሃ ፍላጎት እየጨመረ ነው። በመሆኑም የውሃ አቅርቦት መጨመር የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ውሃ አቅርቦት ለመጨመር የተለያዩ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ ነው፡፡

የከተማዋን የውሃ አቅርቦት ከፍ ለማድረግ ከ‹‹ጀዌ›› እና ከ‹‹ሀይሴ ለሜጃ›› ውሃ ወደ ሆሳዕና ለማስገባት የመስመር ዝርጋታ እና የሪዘርቫይር ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ከንቲባው ጠቅሰው፣ የውሃ ፕሮጀክቱ ከ300 ሚሊዮን በላይ በጀት የተያዘለት መሆኑንም ይናገራሉ፡፡ የሁለቱ የውሃ ማጠራቀሚያዎች /ሪዘርቫይሮች/ ግንባታ እየተጠናቀቀ መሆኑን ጠቅሰው፣ የውሃ መስመር ዝርጋታ ሥራ ወደ ከተማ ውስጥ ገብቷል ይላሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ከሁለቱ አካባቢዎች ውሃ ወደ ሆሳዕና ለማስገባት እየተሠራ ያለው ሥራ ከ50 በመቶ በላይ ተጠናቋል፡፡ በተለይም የ‹‹ጀዌ›› የውሃ ፕሮጀክት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ የ‹‹ሀይሴ ለሜጃ›› ፕሮጀክት ደግሞ አራት ጋኖች ያሉት ሲሆን ከአራቱ ጋኖች የሦስቱ ጋኖች ግንባታ በመገባደድ ላይ ነው፡፡ የውሃ መስመሮች ቀበራ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

በነዚህ አካባቢዎች ከሚገኙ ምንጮች የሚሰበሰበው ውሃ በጋኖቹ ከተከማቸ በኋላ ተገቢው የማከሚያ ሥራ ተሠርቶ ወደ ከተማዋ የሚሠራጭ ይሆናል፡፡ የውሃ ጉድጓዶቹ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ሥራ ከተገባ አንድ ሰው መጠቀም አለበት ተብሎ እንደአገር የተቀመጠውን ደረጃ ማድረስ ይቻላል፡፡ የአምቢቾ ጉደራ ፕሮጀክትም የከተማዋን ፍላጎት እየታየ ግንባታው እንደሚካሄድ አንስተዋል፡፡

አቶ ሊሬ ከተማ አስተዳደሩ የከተማዋን የአስፋልት መንገድ እጥረት ለመቅረፍ የከተማው አስተዳደር ከሕዝብ ጋር በመተባበር የመንገዶች ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያ ዙር የመንገድ ግንባታ 14 ነጥብ 14 ኪሎ ሜትር አስፋልት መንገድ እየተገነባ ይገኛል ያሉት ከንቲባው፣ የከተማዋ ሁሉም አካባቢዎች የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የሁሉም የከተማዋ አካባቢዎች እድገት እኩል እንዲሄድ 14 ነጥብ 14 ኪሎ ሜትሩ በሰባት የተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች እየተገነባ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እንደ ከንቲባው ገለጻ፤ የአስፋልት መንገዶቹ በሄጦ ትምህርት ቤት አድርጎ ወደ አዲስ አበባ ከሚወስደው አስፋልት ጋር የሚገናኝ፣ ከ18 ማዞሪያ እስከ ማረሚያ ቤት ድረስ የሚዘልቅ፣ ከዋንዛ ፊት ለፊት እስከ ቦቢቾ ቃለሕይወት ቤተክርስቲያን የሚሄድ፣ ከዋስገበታ ማዞሪያ እስከ ቦቢቾ ድልድይ የሚሻገር፣ ከእሌኒ መሐመድ መታሰቢያ ሆስፒታል እስከ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የሚዘልቅ፣ እንዲሁም ከእሌኒ መሐመድ መታሰቢያ ሆስፒታል በሀዲያ ባህል ማዕከል ዞሮ ለማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ፊት ለፊት ካለው አስፋልት ጋር የሚያገናኙ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

የአስፋልት መንገዶቹ ግንባታ በስድስቱም ቀበሌዎች ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን የመንገዶቹ አጠቃላይ ግንባታ ከ60 በመቶ በላይ መጠናቀቁን አቶ ሊሬ አስታውቀዋል፡፡ በሁሉም አካባቢዎች፣ የመጀመሪያ አፈር፣ ሁለተኛ አፈር፣ የድንጋይ ሥራ አልቋል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጠጠር የማፍሰስ ሥራ አልቆ አስፋልት የማፍሰስ ሥራዎችም ተጀምረዋል፡፡

ጠጠር አድርጎ አስፋልት የማፍሰስ ሥራ በተቀረው አካባቢ ለማከናወን ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሰሞኑን በአካባቢው መጣል የጀመረው ዝናብ አስፋልት ለማፍሰስ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ ዝናቡ ፋታ የሚሰጥ ከሆነ አስፋልት የማፍሰስ ሥራውን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ እንደሚሠራም አንስተዋል፡፡ አስፋልት ፕሮጀክት ከ450 ሚሊዮን በላይ የተበጀተለት ሲሆን ፕሮጀክቱ የዚህ ዓመት መጨረሻ ድረስ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመዋል፡፡

በከተማዋ በፊት የተገነቡ መንገዶችም ለረጅም ዘመን አገልግሎት ሲሰጡ በመቆየታቸው አዳዲስ አስፋልቶችን ከመገንባት ጎን ለጎን የአስፋልቶቹን ደረጃ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ያነሱት አቶ ሊሬ፤ የመንገዶቹን ደረጃ ለማሳደግ ጨረታ ወጥቷል፡፡ የጨረታ ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ወደ ማስፋፋት ሥራው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ሊሬ ማብራሪያ፤ የከተማው አስተዳደሩ በራሱ ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን ከዓለም ባንክ በብድር የሚሰጠው ገንዘብ እና የከተማውን ሀብት በማቀናጀት ሌሎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራዎችም በትኩረት እየተሠሩ ናቸው፡፡ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል ወደ 235 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የድሬኔጅ፣ የኮብልስቶን፣ የጠጠር መንገድ ጥገና ሥራ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ሥራዎች ከ90 በመቶ በላይ ደርሰዋል፡፡ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ፕሮጀክቶቹ በተባለለት ጊዜ እንዲጠናቀቁ የከተማው ሕዝብ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡

ሕዝቡ በተለይም ለእግረኛ መንገድ ማስፋፊያ አስፈላጊ የሆነ ቦታ በመልቀቅ ጥሩ ትብብር እያደረገ ነው፡፡ ሕዝቡ እያደረገ ባለው ድጋፍ በከተማዋ መንገድ የማስፋት ሥራ በተሳካ ሁኔታ እየተሠራ ነው፡፡ የከተማው ሕዝብ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመተባበር አመርቂ ሥራ እየሠራ ነው። ሕዝቡ ባሳየው መልካም ፍቃድ ዋና መስመሮች ላይ የእግረኛ መንገድ ከማስፋት ባሻገር ውስጥ ለውስጥ ያሉ መንገዶችንም ለማስፋት የተለያዩ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው፡፡ የአስፋልት መንገዶችም እጅግ ጠባብ የነበሩ ሲሆን፣ ሕዝቡ ባደረገው ትብብር እንዲሰፋ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡ በርካታ ሰዎች ቤታቸውን ጭምር ለመንገድ ማስፋፊያ በማፍረስ እና ቢሸጥ ብዙ ብር ሊገኝበት የሚችል መሬት በነፃ እየለቀቁ ይገኛሉ፡፡

ከዚያ ባሻገር የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች፣ የመንግሥት ሠራተኞች እና መላው የከተማው ሕዝብ በመነጋገር ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ይገኛል፡፡ የከተማው አመራሮች እና ሠራተኞች የአንድ ወር ደመወዛቸውን ለከተማው መሠረተ ልማት ግንባታ ለመስጠት ወስነዋል። ከዚህ ወር ጀምሮ ከደመወዛቸው ተቀንሶ ለከተማው ልማት ይውላል፡፡

ከአመራሩና ከመንግሥት ሠራተኛው ባሻገር መላው የከተማው ኅብረተሰብ ድጋፍ ለማድረግ ፍቃደኛ መሆኑንም ተናግረው፣ እያንዳንዱ ቀበሌ 10 ሚሊዮን ብር ለማዋጣት ቃል ገብቷል ብለዋል፡፡ ሕዝቡ ገንዘቡን ማዋጣት ጀምሯል ያሉት ከንቲባው፣ ይህም ሕዝቡ በከተማዋ ውስጥ እየተካሄደ ባለው የመሠረተ ልማት ሥራ ደስተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡ በቀጣይም ሕዝቡ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ከቻለ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይቻላል፡፡ ከተማዋን ከሌሎች ካደጉት ከተማዎች ተርታ ማሰለፍ እንደሚቻል አመላካች ነው ብለዋል፡፡

የ‹‹ጆሎ ደቀዬ››ፕሮጀክትም በዚህ ዓመት ለመሥራት የታቀደውን ሥራ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ተችሏል፤ ዙሪያው ታጥሯል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የሕዝቡን ባህል የሚያስተዋውቁ ሥራዎች ተሠርተዋል። የጥበቃ ቤቶች ተሠርተዋል፤ ቲኬት መቁረጫ ቢሮዎች ተገንብተዋል፡፡ ውስጥ ፋውንቴይን እና ኳስ መጫወቻዎች ተሠርቷል፡፡ ቤተመጻሕፍት ተገንብቷል። ሁለተኛ ምዕራፍ ግንባታ ተጀምሯል፡፡ የ‹‹ጆሎ ደቀዬ›› ዘመናትን የተሻገረ ታሪካዊ ቦታ መሆኑን የሚያነሱት አቶ ሊሬ፤ ቦታው ታሪካዊነቱን ይዞ እንዲቀጥል እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡ በቀጣይ አራት ዓመት ተኩል ተሠርቶ ይጠናቀቃል፡፡ ባለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

የሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ተቋማዊ የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ዘነበ ዳኛቸው በበኩላቸው እንዳሉት፤ ከስድስት ኪሎ ሜትር በላይ የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ ሥራ በስድስቱም ቀበሌዎች በተለያዩ ሳይቶች በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኞቹ ተጠናቀዋል፡፡ ወደ ሰባት ኪሎ ሜትር የሚጠጋ የጎርፍ መውረጃ መንገድ በ12 ሎቶች ተከፋፍሎ የግንባታ ሥራው እየተሠራ ነው፡፡ የዚህም 70 በመቶ የሚሆን ሥራ ተጠናቋል፡፡ ከዚህ ቀደም ከተማዋው የሚታማበት አንዱ ምክንያት የእግረኛ መንገድ ምቹ አለመሆን ነው፡፡ የውስጥ ለውጥ እና ዋና መንገድ የማስፋት ሥራ ስትራክቸራል ፕላኑን በጠበቀ ሁኔታ እየተሠራ ነው፡፡ የማስፋት ሥራዎች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለከተማው ውበት የሚጨምር ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት በከተማዋ ውስጥ እየተሠራ የነበረው የአምስት ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ሥራም ቆሞ እንደነበር የሚያነሱት አቶ ዘነበ፤ አሁን ግን የመንገዱ ግንባታ ዳግም እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል፡፡ በሆሳዕና ከተማ ውስጥ የሚስተዋለውን የመሠረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ እየተደረገ ያለው ጥረት ሊበረታታ የሚገባ እና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የለውጡ ጉዞ ከተግዳሮቶች በላይ የሆነ ጽናትን ይጠይቃል!

ለውጥ ድንገት የሚፈጠርና በሆነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ተጠናቆ የሚያበቃ ክስተት አይደለም። በጊዜ ሂደት ውስጥ ሲብላሉ በቆዩ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ገፊ ምክንያት የሚፈጠር፤ እንደየባህሪው በከፍተኛ ጥንቃቄና ኃላፊነት መመራትን የሚጠይቅ ትልቅ ግለሰባዊ፣ ማኅበራዊ፣ አገራዊ እና ዓለምአቀፋዊ እውነታ ነው።

ለውጥ ከሁሉም በላይ ከትናንት እና ከትናንት ከሆኑ አስተሳሰቦችና አስተሳሰቦቹ ከወለዷቸው ድርጊቶች የመውጣት መነሳሳት የሚታይበትና ለዚህም የሚሆን ቁርጠኛነት የሚስተዋልበት፤ ከውስጥ የሚመነጭና በአስተሳሰብና በድርጊት እየገዘፈ የሚሄድ፤ በኋላም ገዥ ሆኖ ማኅበረሰብን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የሚያሻግር ነው።

በተለይም ድህነት ውስጥ በሚኖሩ ሕዝቦች ውስጥ የሚካሄዱ ለውጦች እና ለውጦቹ ሊገዙላቸው የሚገቡ አስተሳሰቦች፤ በዋነኛነት ድህነትን አሸንፎ መውጣትን ታሳቢ ያደረጉ፤ ድህነትን ከፈጠሩ እና ዕድሜውን ከሚያራዝሙ አስተሳሰቦችና አስተሳሰቦቹ ከወለዷቸው ማህበራዊ ድርጊቶች የራቁ ሊሆን ይገባል። የስኬት አቅምም መመዘኛቸውም ይኸው ነው።

በእኛም አገር የዛሬ አምስት ዓመት የተጀመረው ለውጥ ከመነሻው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ገፊ ምክንያቶች የነበረው፤ በየዘርፉ ለውጥ አምጪ ሪፎርሞችን በመተግበር ድህነትን ታሪክ የማድረግ ዓላማና ተልዕኮ ይዞ የተነሳ ነው። እስካሁን ባለው ሂደትም በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ እያለፈ ተስፋ ሰጪ በሆነ የጉዞ ሂደት ላይ ይገኛል።

አገር እንደ አገር በከፍተኛ የመፍረስ ስጋት ውስጥ በነበረችበት፤ በዚህም ዜጎች ባልተረጋጋ ስሜትና መንፈስ በጭንቀት እና ግራ መጋባት ውስጥ በነበሩባቸው በነዚያ ክፉ ቀናት ወደ ስልጣን የመጣው የለውጥ ኃይሉ፤ በጊዜው የነበረውን አገራዊ ምስቅልቅል ፈር ለማስያዝ የሄደበት ብስለት የተሞላበት መንገድ፤ የዛሬዋን የተረጋጋች አገር እውን ከማድረግ አልፎ በብዙዎች ዘንድ ለነገ ተስፋ የተጣለባትን አገር መፍጠር እየቻለ ይገኛል።

ባዶ ካዝና፣ በብዙ ክፍተቶች የተሞሉ የጸጥታ ተቋማት፣ ማዕከላዊነት የጎደለው የፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት በእጅጉ እየተገዳደሩት አገር የመታደግ ታሪካዊ ጉዞውን በአገር ፍቅር ስሜት በሕዝብ ታምኖ የጀመረው የለውጥ ኃይሉ፤ ብዙም ሳይራመድ ግልጽ በሆነ ጦርነት፤ በየአካባቢው ታቅደው በሚከሰቱ ግጭቶች፤ በኢኮኖሚ አሻጥር፣ ዓለም አቀፍ ጫና፣ ፋታ በሌለው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተፈትኗል።

በአገር ውስጥ ሆነ በውጭ የሚገኙ የሕዝቡን የለውጥ መሻት የመቆመሪያ ካርድ ማድረግ የሚፈልጉ ኃይሎች፤ ዛሬ አልበቃ ብሏቸው ወደ ትናንቶች ተጉዘው፤ ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት ፤ የታሪክ ጠባሳዎችን በመምዘዝ ፤ ለለውጡ ተግዳሮት ሆነዋል። በዚህም የለውጡን ኃይል ብቻ ሳይሆን መላውን ሕዝብ ውድ ዋጋ አስከፍለውታል።

እነዚህ ፈተናዎች ለውጡ ከነበረው ሕዝባዊ ድጋፍ አንጻር፤ የታሰበለትን ያህል በፍጥነት እንዳይጓዝ ተግዳሮት ሆኗል። በተለይም የለውጥ ኃይሉ በአገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ባህል ለማምጣት ገና ከጅምሩ የመጣበትን ትናንቶችን በይቅርታ፤ ዛሬዎችን በውይይትና በድርድር የመሻገር መሻት በከፍተኛ ሁኔታ ተፈታትነውታል፤ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍልም አስገድደውታል።

ይህ ሁሉ በሆነበትና እየሆነ ባለበት አገራዊ አውድ የለውጥ ኃይሉ በአገርና በመንግሥት ላይ የታወጀውን ግልጽ ጦርነት መላውን ሕዝብ ከጎኑ አሰልፎ ከማምከን ጀምሮ፤ አገርን እንደ አገር በጸና መሠረት ላይ ሊያቆሙ የሚችሉ የፌዴራል ተቋማትን /የመከላከያ፣ የደህንነት .ወዘተ / ዘመናዊ እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ እየገነባ፤ በዚህም የብዙዎችን አድናቆት እየተቸረ ነው።

በዴሞክራሲ እና ፍትህ ተቋማት ግንባታ ዙሪያም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ጨምሮ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት የሚሠሩበትን አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ፤ በቀጣይም በመላው ሕዝብ ተሳትፎ ወደ ተሻለ ደረጃ ሊሸጋገር የሚችል እንደሚሆን ይታመናል።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ በየወቅቱ ያጋጠሙትን ውስጣዊና ውጪያዊ አሻጥሮች/ ሴራዎች ተሻግሮ አሁን ላይ ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንት መሳብ የሚያስችል ቁመና ላይ ይገኛል፤ ይህም አሁን ካለው አገራዊ ሰላም አንጻር በቀጣይ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆን፤ በዚህም ዜጎች የለውጡን ትሩፋት የሚያጣጥሙበትን ዕድል የሚፈጥር ይሆናል።

የለውጥ ኃይሉ በአምስት ዓመታት የለውጥ ጉዞው፤ በተለይም ከለውጡ ውስብስብ ባህሪ አንጻር፣ አንድም ለውጡን በአግባቡ ካለመረዳት፣ ከዚያም ባለፈ ከለውጡ ያልተገባ ተጠቃሚ ለመሆን፣ ከለውጥ ኃይሉ ጋር ሰልፍ ባሳመሩ እና ባልተለወጡ ግለሰቦችና ቡድኖች፤ የለውጡን ዓላማና ተልዕኮ የሚፈታተኑ፤ በዚህም ሕዝብንና አገርን ዋጋ ያስከፈሉ ችግሮች ተከስተዋል።

ተመሳሳይ ችግሮች በለውጥ ወቅት የሚያጋጥሙ ቢሆኑም፤ ከእንግዲህ ባለው ቀጣይ የለውጥ ጉዞ ለችግሮቹ ተገቢው ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ለውጥ ሂደት ከመሆኑ አንጻር የለውጥ ኃይሉ በአስቸጋሪ ወቅቶች ከአቅም በላይ በሆኑ ገፊ ምክንያቶች ተከስተው በሕዝቡ ውስጥ ቅሬታ የፈጠሩ ጉዳዮችን በማረም፤ ለውጡ በሕዝቡ ውስጥ የነበረውንና ያለውን አመኔታ ማደስ ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱን የተሻለ ለማድረግ

**ስምስም መንግሥቱ**

ጉድለት ያየንበትን ሰው ማስተዋል የጎደለው ብለን እንወቅሰዋለን:: አዙሮ አለማየቱንም ልናሳየው እንሞክራለን:: ነገሮችን በትእግሥት የሚያልፍ ሰውም እንዲሁ ሆደሰፊነቱን እንመዝነዋለን:: ሆደ ሰፊነት፣ አስተዋይነት፣ አዙሮ ማየት፣ እነዚህ ቃላት ለመባል ብቻ የተቀመጡ አይደሉም:: ሰዎች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ውስጥ የሚያልፉባቸው በመሆናቸው ጭምር ነው::

በዚህ ወቅት ብዙ ዓይነት አለማስተዋል እንታዘባለን። በትራንስፖርት ዘርፍ ላይ የምንታዘበው አለማስተዋል ግን ከሁሉም ይለያል:: አስተዋይነት የጎደለው ነው በሚል ብቻ የሚታለፍ አይደለም:: በተደጋጋሚ ነው የሚፈፀመው:: የሥነምግባር ግድፈት ተደርጎም ይወሰዳል:: እንዲታረም የሚያደርግ አካልም የለም:: ድርጊቱ ትክክል ተደርጎ እየተወሰደ በመሆኑ በሌላውም ላይ እየተጋባ ነው:: ተገልጋዩን ተባባሪ እስከማድረግ ተደርሷል::

ዘርፉን የሚመራው አካልም በዝምታ እያለፈው በመሆኑ የቻለ ተገልጋይ እየተናነቀ መብቱን ለማስከበር ጥረት ያደርጋል::ያልቻለው ደግሞ ተበሳጭቶ ያልፈዋል:: ግን እስከመቼ እንዲህ በትራንስፖርት ዘርፉ የሚስተዋለው ነገር በየጊዜው አዳዲስ ነገር እየፈጠረና መረን እየለቀቀ ይሄዳል:: ለችግሩ ማሳያ ለጽሑፌ መነሻ እንዲሆነኝ አንድ በከተማ ውስጥ እና አንድ ደግሞ በአገር አቋራጭ አገልግሎት ላይ ያለኝን ትዝብት ላካፍላችሁ:: የከተማውን ላስቀድም፤

ከመርካቶ አራት ኪሎ ነው መጓዝ የፈለኩት:: ተራውን ጠብቆ የሚጭነው ታክሲ ውስጥ ለመግባት ስሞክር ከየት መጣ ሳልል ረዳቱ በሩን ይዞ የምሄድበትን ጠየቀኝ:: ወደ አራት ኪሎ እንደምሄድ ነገርኩት:: ቦታ የለም አለኝ:: ክፍት ቦታዎች ግን ነበሩ:: እኔም የዋዛ አልሆንኩለትም ክፍት ቦታውን እያሳየሁት ገፍቼው ገባሁ:: እየተወናጨፈና እየዛተ 20ብር እንደምከፍል ነግሮኝ ዕቃ የያዙ መንገደኞችን መፈለጉን ቀጠለ:: ብዙ ዕቃ ለያዘና ከፍ ያለ ክፍያ ለሚጠየቀው የፊትለፊት መቀመጫ (ጋቢና) ተይዟል:: ገና ተፈልጎ ለሚመጣ ተሳፋሪ ነው እንግዲህ ቀድሞ የተያዘው::

እንደእኔ ብቸኛ ተሳፋሪ መጥቶ የጋቢናውን በር ለመክፈት ይታገላል:: የታክሲው ሾፌር እያሾፈ «ይሄ ቪ አይ ፒ ነው::ዋይፋይም አለው» ይላል:: ስለሌላው መብት ለመናገር ቀርቶ የራስንም ማስከበር እየተቻለ ባለመሆኑ ሰው ዝምታውን መርጧል:: የሚበሳጭም ካለ ብስጭቱን ከመቻል ውጪ አማራጭ የለውም:: ምክንያቱም ሾፌሩ፣ ረዳቱ፣ ተራ አስጠባቂውም ቋንቋቸው ተመሳሳይ በመሆኑ ተሳፋሪው ላይ ይተባበራሉ:: በጉልበት ዝም ስላሰኙት ትራንስፖርት ላይ መብቴ ነው ቀርቷል::

ታስታውሱ ከሆነ አንድ ወቅት ላይ ታክሲ ውስጥ የተለያዩ ጥቅሶች ይለጠፉ ነበር:: ከነዚህ ውስጥ «መብትህን ታክሲ ውስጥ ነው የምትጠይቀው» የሚል ጥቅስ ተጠቃሽ ነው:: አሁን በጉልበት ጭጭ እንዲሉ ማድረግ እየተቻለ ለጥቅስ ለምን ወጪ ይወጣል:: ያሳፈረኝ ታክሲ ላይ ጉልበተኛ ሆኖ እርሱ ያዘዘኝን 20 ብር ሳይሆን፣ ሦስት ብር ትርፍ ጨምሬ 10 ብር ከፈልኩት። ብሩን ሲቀበለኝ ግን ከስድብና ከዱላ ባልተናነሰ እየተርጎመጎመ ከእጄ መንጭቆ ነበር የተቀበለኝ:: እኔ ለእርሱ በምከፍለው እንደሚኖር ማስተዋል እንኳን ቢሳነው በዕድሜም ሊያከብረኝ ይገባ ነበር::

ከአገር አቋራጭ ገጠመኜ ደግሞ አንዱን ላካፍላችሁ። ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ ቢሾፍቱ ነው ጉዞዬ፤ በመናኸሪያው ግቢ ውስጥ በእያንዳንዱ የጉዞ መሥመር የታሪፍ ዝርዝር በደረጃ በግልጽ ቦታ ላይ በሰሌዳ ላይ ተለጥፏል:: ግን ብዙዎች በዚህ መሠረት መብታቸውን እየተጠቀሙ አይደለም:: ሾፌሩ መንገድ ሲጀምር የሚጠይቃቸውን ዋጋ በመልመዳቸው ያንን ነው የሚፈጽሙት:: የሚገርመው ደግሞ በቅጥር ግቢው ውስጥ የተለጠፈውን ታሪፍ አለማየታቸው አይደለም። ከከተማ ከወጡ በኋላ አንዳንዴ ትራፊኮች ደረሰኝ ስለሚጠይቁ አሽከርካሪዎቹ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር መኖሩን ሲሰሙና ጠንቃቃ ለመሆን ሲሉ ታሪፍ የያዘ ደረሰኝ ለተሳፋሪው ያድላሉ::

ደረሰኙ ጉዞ ካለቀ በኋላ የሚመለስ በመሆኑ በጥንቃቄ እንዲያዝ ይጠየቃል:: ደረሰኙ ላይ ያለው ታሪፍና የሚጠየቁት ክፍያ ልዩነት እያለው እንኳን ተሳፋሪው ለምን ብሎ አይጠይቅም:: ታዲያ እኔ ደረሰኙ ላይ በተቀመጠው ታሪፍ መሠረት ክፍያውን ሰጠሁ:: ክፍያውን የሚሰበስበው ተሳፋሪ ነበር:: በትርፍ ክፍያው መሠረት ባለመክፈሌ ሂሳቡን አልቀበልም አለኝ::

እኔም አልተቀበልኩትም በመጨረሻ ግን ልዩነቱን ከፍሎልኝ ነው ሂሳቡን ሰብስቦ የሰጠው:: ተሳፋሪው ይህን ያደረገው መብቷ ነው በሚል እሳቤ ሳይሆን፣ ገንዘብ የላትም:: ወይንም ጨቅጫቃ ናት በሚል ነው:: እንዲህ ያለው ገጠመኝም የተለመደ ነው:: የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ምን ያህል በሰው አእምሮ ላይ ጫና እንደፈጠሩ ካለው ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል::

በአገርአቋራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት በበዓላት ወቅት ደግሞ የባሰ ነው:: በአዘቦቱ ከሚደረገው ጭማሪ በላይ እንዲማረሩ ነው የሚያደርግዎት:: የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎቹ አብዛኞቹ ከመናኸሪያ ግቢ ውጪ ነው የሚሆኑት::ደላላዎች በውጭ በር ላይ ሆነው ከቃሊቲ መናኸሪያ በመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በደረጃ ከ25 እስከ 31 ብር ከፍለው የሚጓዙበትን መንገድ እስከ ሁለት መቶ ብር በመጠየቅ ያሳፍራሉ::

ደላሎቹ ያኔ የግል መኪና ሁሉ በሕገወጥ ትራንስፖርት ስምሪት ውስጥ እንዲገባ ያደርጉታል:: በመደበኛ ትራንስፖርት ለመሄድ ሰልፍ ይዞ ሲጠባበቅ የነበረው ሁሉ ተስፋ ቆርጦ ከግቢ እየወጣ ለሕገወጦች ሲሳይ ይሆናል:: ይሄ የሚሆነው መሽቶ ወይንም አማራጭ ጠፍቶ አይደለም:: ዘርፉን የሚመራውም አካል ተባባሪ በመሆኑ ነው በጠራራ ሰዓት እንዲህ አይን ያወጣ ድርጊት የሚፈፀመው:: በመናኸሪያ ግቢ ውስጥ በበዓል ወቅት ያለው ይብሳል ለማለት እንጂ ከሳምንት እስከ ሳምንት ሰልፍ የተለመደ ሆኗል::

ከሰሞኑ ፖለቲካዊ ይዘት አለው ተብሎ የተነገረለት የባጃጅ ትራንስፖርት አገልግሎትን በመንግሥት በኩል ለጊዜው ተወስዶ የነበረው የማቆም እርምጃ እውነትነት ያለው ነገርም እንዳለው መዘንጋት የለበትም:: የአጭር ጉዞ መነሻ ታሪፍ ከአምስት ብር ወደ አስር ብር ያሳደጉት በራሳቸው ነው:: የጠየቃቸው አካል ባለመኖሩ ታሪፉ ፀድቆ ሲሠራበት ነበር::

የዚህ አገልግሎት ክፍያም በዋና አስፓልት ላይ ለሚጠቀም ነው:: የባጃጅ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲጀመር ግን ውስጥ ለውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ እንደነበር ይታወሳል:: ተከታትሎ ያስፈፀመው አካል ባለመኖሩ የባጃጅ ባለቤቶች እራሳቸውን በራሳቸው ነው የመሩት ማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ከትራንስፖርት ዘርፉ ጋር በተያያዘ ከተደራሽነት ጋር በተያያዘ የተገልጋዩ ቁጥርና አገልግሎቱ አለመጣጣም እንደምክንያት ሊነሳ ይችላል:: የሥነምግባር ጉድለቱና ያለውንም በአግባቡ አገልግሎት እንዲሰጥ በቁጥጥርና ክትትል የሚያስተካክል አካል አለወይ ሲባል የለም:: ምክንያቱም ችግሮቹ እየተባባሱ እንጂ መሻሻል ስለማይታይ ነው::

ለመሆኑ መንግሥት ለትራንስፖርት ዘርፉ ያደረገውን የነዳጅ ድጎማ ስንቶቻችን አስተውለናል:: አገልግሎት ሰጪውም እንዳይጎዳ፣ ተገልጋዩም ክፍያው ከአቅሙ በላይ እንዳይሆንበት የነዳጅ ታሪፍ ድጎማ ድጋፍ አድርጓል:: ይሁን እንጂ «የውሾን ልጅ ያነሳ ውሾ ይሁን» እንደሚባለው ስለዚህ ጉዳይ የሚያነሳ አካል የለም::

የትራፊክ ሕግ የሚተላለፉ አሽከርካሪዎችን ለመቆጣጠር በተጨማሪ የሰው ኃይል በመንገድ ትራንስፖርት እየተሠራ ያለው ሥራ በአገልግሎቱ ላይም በተመሳሳይ መሠራት ይኖርበታል:: በየትራንስፖርት ዓይነቱ ያለውን ፀባይ ለይቶና ፈትሾ በቁጥጥርና ክትትል የማጠናከሩ ሥራ ከመንግሥት ይጠበቃል::

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ያልተሰበረ ልብ

መልካምሥራ አፈወርቅ

ልጅነቷ በሳቅ ጨዋታ የተዋዛ አይደለም:: እናትዋን በሞት ያጣችው በሕጻንነት ዕድሜዋ ነው:: የእናት ወግ ፤ የልጅነት ቅብጠት ይሉትን አላየችም:: ባደገችበት የገጠር ቀዬ በታላቅ ወንድሟ መዳፍ ሥር ቆይታለች:: ነፍስ ማወቅ ስትጀምር ግን ክፉ ደጉን ለየች:: ደግ ወንድሟ እንደ እናት አባት መከታ ሆኗታል:: እየደገፈ፣ እየሰሰተ አሳድጓታል::

አበራሽ ደገፋ በዕድሜ ከፍ እስከትል ከመንደር ቀዬው አልራቀችም:: አቅም ከቻለው፣ ቤት ካፈራው ሳትነፈግ አስር ዓመቷን ደፈነች:: ከዚህ ዕድሜዋ በኋላ ግን ብዙ ዓይኖች ከዓይኖቿ ላይ በረከቱ:: መውጫ መግቢያዋን የሚያዩ፣ አረማመዷን የሚቃኙ ሁሉ ከጀርባዋ ተከተሏት:: ልጅነቷን የሻቱ ፤ ዝምድናዋን ፈለጉት:: ፍላጎታቸው ለጋብቻ ፤ ለትዳር ሆነ::

አበራሽ በዕድሜ ገና ልጅ ናት:: የሰዎቹ ፍላጎት ግን ገብቷታል:: ልጅነቷን አሳበው በግዳጅ ሊድሯት መሆኑን አውቃለች:: እሷ ባለችበት ዕድሜ ባል ማግባትን ፤ትዳር መያዝን አትሻም::

ሰዎቹ በአትኩሮት ክትትል ይዘዋል:: እሷ ሀሳባቸው እንዳይሰምር፣ ትመኛለች:: አጋጣሚው መልካም ሆነላት:: የእሷ ስጋት የእነሱ ዕቅድ ዕውን ሳይሆን ቀረ:: አበራሽ በአንድ የቀን ሙሉ ጫንጮን ድንገት ለቃ አዲስ አበባ ገባች::

### አዲስ አበባ

አዲስ አበባ እንደ ገጠር አይደለም:: ድምቀቱ ፤ መብራቱ፣ ኑሮው፣ ከምታውቀው መንደር ይለያል:: ሁሉም ነገር ደስ አላት:: በዚህ ስፍራ አክስቷና ሌሎች ዘመዶቿ አሉ:: ለእንግድነት አልከበደችም:: መልካም ፊቶች በደስታ ተቀበሏት:: የነበረችበትን ረሳች፣ያሳለፈችውን ዘነጋች::

አበራሽ በአክስቷ ቤት ኑሮን ጀመረች:: የከተማ ሕይወት አላስከፋትም:: ሁሉን መስላ ከሁሉ ተግባባች:: ውሎ አድሮ በእሷ ላይ አዲስ ሀሳብ ተመከረ:: ቤት ከምትቀመጥ ሥርታ ብታድር እንደሚበጅ ነገሯት:: ሀሳቡን አልጠላችም:: እየሠራች፣ገንዘብ ብታገኝ፣ አዲስ ልብስና ጫማ ብትገዛ ወደደች:: እጇን ይዘው ከሥራው ጋር አገናኟት:: በእሷ ዕድሜ የተገኘው ሙያ ሞግዚትነት ሆነ::

አበራሽ ጥቂት የቆየችበትን የአክስቷን ቤት ትታ ሥራውን ጀመረች:: አልከበዳትም:: ከእሷ የሚያንስ ሕጻን አዝላና አቅፋ ትውላለች:: የሰጧትን በልታ፣የታዘዘችውን ሥርታ ታድራለች::

ትንሽዋ አበራሽ ከወር በኋላ የወር ደሞዝ ይኖራታል:: እሱ ሲደርስ የልቧ ይሞላል:: የዛኔ ያሻትን ትገዛለች:: ይህን ስታስብ ፈገግታዋ ይደምቃል:: የልጅነት ልቧ ይሞላል:: ደስ እያላት ሥራውን ቀጠለች:: ሕጻኑ ወደዳት፣ ቤተሰቦቹ መረጧት :: መሽቶ ነጋ፣ ቀናት አለፉ::

አሁን አበራሽ የአዲስ አበባ ልጅ ነች:: ዕድገት ውበቷ ጨምሯል:: ድንቡሼ ሰውነቷ ልጅነቷን ይናገር፣ ያሳብቅ ይዟል :: እንዲህ መሆኑ ከዓይን ጥሏታል:: አሁንም በተለየ የሚያይዋት፣ የሚያስተውሏት አልጠፉም::

አንድ ቀን አበራሽ ልጁን አዝላ‹‹እሹሹ..››ስትል ዋለች:: መሽት ሲል ሕጻኑን ለእናቱ አስረክባ ወደ ማረፊያዋ ሄደች:: እንዲህ ማድረግ አዲሷ አይደለም:: ሥራው ሲያልቅ ክፍሷን ዘግታ ጎኗን ታሳርፋለች:: የዛን ቀንም ልክ እንደወትሮው አረፍ ልትል ገብታለች:: ከአፍታ በኋላ ተስፋዋን እያለመች ዕንቅልፍ ይጥላታል:: አበራሽ የዛን ቀን በመስኮቱ በኩል አንድ ድምፅ የሰማች መሰላት:: ደንገጥ ብላ በእርጋታ አጤነችው:: በትክክል መስኮቱን ለመክፈት የሚታገል እጅ አለ:: የልጅነት ልቧ ደነገጠ:: ደግሞ ደጋግሞ ደለቀ::

ጥቂት ቆይቶ መስኮቱ ብርግድ ብሎ የውጭው ብርሃን ወለል አለ እንደፈራችው ነው:: አንድ ሰው ከፊት ለፊቷ ቆሞ ዘሎ ለመግባት ይታገላል:: አውቀዋለች:: የአሠሪዎቿ፣ልጅ የቤቱ ጎረምሳ ነው:: ፊጥና ጩኸቷን አሰማች:: ድምፅዋን የሰሙ ጩኸት ያስደነገጣቸው እየሮጡ ደረሱ:: የሆነውን ሁሉ ሳትደብቅ ተናገረች::

### ‹‹ውሽታም...››

አሠሪዎቿ ከእሷ የሰሙትን ሐቅ አልተቀበሉም:: የእነሱ ልጅ እሷን ለመድፈር መስኮት ዘሎ እንደማይገባ አምነዋል:: የልጁ ድርጊት ፈጽሞ ከከፋት አልታየም:: አበራሽ ግን ጥፋተኛ ተደርጋ መወቀስ ይዛለች:: ‹‹ውሽታም›› ተብላለች:: ይህ እውነት እሷን ከእነሱ አስታርቆ የሚያዘልቃት አልሆነም:: አፍታ አልቆየችም:: የእጇን ጥላ፣ የያዘችውን ትታ ቤቱን ለቃ ወጣች::

አበራሽ የለፋችበትን፣የጉልበቷን ዋጋ አልጠየቀችም:: ስትገባ በትንሽዋ ቦርሳ ያኖረቻትን ገንዘብ ጭምር ትታ ወጥታለች:: የሆነባት ክፋት ሳይታሰብ ነገሮች በእሷ መሳበባቸው አስከፍቷታል:: ወደ ቤት ስትመለስ አክስቷ ፊት አልነሷትም:: ጥቂት ቀን ተረጋግታ ሌላ አማራጭ ፈለገች:: በየቤቱ እየዞረች ልብስ አጠባ ጀመረች::

አሁን አበራሽ ዕድሜ ጨምራለች፣ ከአምናው ዘንድሮ፣ ውስጧ በስሏል:: የአዲስ አበባን ሕይወት እየገባት፣ እያወቀችው ነው:: ከዚህ በኋላ በአክስቷ ቤት መኖር አትሻም:: ራሷን መቻል ፈልጋለች:: ያሰበችው አልቀረም:: ቤት ተከራይታ ኑሮ ጀመረች::

ሕይወት ራስን በመምራት ቀጠለ:: በገቢዋ ኪራይዋን ከፍላ ቤት ጓዳዋን ትሞላለች:: የቀራትን ጥቂት ይዛ ስለ ነገ ታስባለች:: አከራይዋ ሴት ይወዷታል:: ጨዋነቷን ፤ የዕለት ብርታቷን ያደንቁታል:: አበራሽ ግቢው ‹‹አባዬ›› ብሎ ለሚጠራቸው ወይዘሮ ልዩ ፍቅር አላት:: እንደ እናት ትወዳቸዋለች:: ሁሌም ያሏትን ትሰማለች፣ ቃላቸውን ታከብራለች::

### የአባዬ ምክር

አንድ ቀን አባዬ ማልደው ተነሱ:: አበራሽን እያስተዋሉም እንደሚፈልጓት ነገሯት:: አከባሪያቸው ናትና ከፊታቸው ቆመች:: አባዬ ኮስተር ብለው ንግግር ጀመሩ:: የብቸኝነት ኑሮ እንደማይበጅ ደጋግመው ነገሯት:: ከልብ ሰማቻቸው:: በዚህ ብቻ አልቆሙም:: ያሰቡትን፣ለእሷ የተመኙትን ዕቅድ ዘረዘሩላት፣ለጊዜው ግራ ገባት:: ቀስ እያሉ አስረዷት:: አልተቃወመችም:: በዝምታ አንገቷን ደፍታ ሰማቻቸው::

ወይዘሮዋ ለአበራሽ ለእሷ ትዳርን አስበዋል:: ያጬላት ደግሞ ከዕድሜዋ የሚልቅ፣ ምራቁን የዋጠ ሰው ነው:: ሰውዬው ከአበራሽ፣ እሷም ከእሱ እውቂያ የላቸውም:: የአከባሪ እናቷን እጅ አልገፋችም:: ባሏት ተስማምታ ቃላቸውን አከበረች:: ካጬላት ሰው ተዋውቃ ቤት ጎጆ መሠረተች::

አበራሽ የትዳር አጋሯን ካገኘች ወዲህ ብቸኝነቷ ቀርቷል:: ‹‹ከአንድ ብርቱ ሁለት›› ይሉት ብሂል እውነት መሆኑ ገብቷታል:: አንዳንዴ ባለቤቷ ሀገሩ መግባት እንደሚፈልግ ይነግራታል:: ይህ እውነታ ለእሷ ያስጨንቃታል :: በትዳር ሁለት ዓመታት አልፈዋል:: ከዚህ በኋላ ለብቻ መኖርን አትሻም:: ይህን ስታስብ ታዝናለች፣ ትተክዛለች::

### በድንገት

አንድ ማለዳ አበራሽ እግሯ ከሆስፒታል አደረሳት:: የመረመራት ሐኪም በእጁ የያዘውን ወረቀት እያስተዋለ ነፍሰጡር መሆኗን አበሰራት:: ደነገጠች፣ተደሰተች:: ይህ አጋጣሚ ለባለቤቷ እጥፍ የምሥራች ሆነ:: የእሷ ማርገዝ ሀሳቡን አስለወጠ:: መንገድ ያሰበው ልቡ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

ከወራት በኋላ አበራሽ የሴት ልጅ እናት ሆነች:: የጥንዶቹ ሕይወት በልጅ በረከት ታድሶ ቤታቸው ሞቀ:: ልጅቷ ማደግ፣መሮጥ ስትጀምር ተጨማሪ ገቢ አስፈለጋቸው:: የቤቱ አባወራ በጥበቃ ሥራ ጥቂት ገቢ ያመጣል:: መኖሪያቸው በኪራይ ነውና ተጨማሪ አቅም ያሻል::

አበራሽ ትንሽዋን ልጅ አዝላ ልብስ አጠባ ትውላለች:: በላብ በወዟ የምታገኘው ጥቂት ገንዘብ የልብ አያደርስም:: ከባለቤቷ ገቢ ተዳምሮ ለጎጂቿ ይውላል::



አበራሽ ደገፋ

### የቀን ጎዶሎ

አበራሽ ለኑሮ፣ትዳሯ መልፋቷን ይዛለች:: የትም ስትሄድ ልጇን አዝላ፣አስከትላ ነው:: በየሰው ቤት ልብስ ታጥባለች ፤ ሥራ አትንቅም:: ገንዘብ የሚያስገኘውን ሁሉ ትሠራለች:: አንዳንዴ የልብስ አጠባው ጊዜ አይሰጣትም:: ቀኑን ይይዝባታል:: ሁሌም በድካም ውላ ስትመለስ ቤቷን ታስባለች:: ጎጆዋ እንዳይጎድል፣ እጇ እንዳያጣ፣ልጇ እንዳትራብ የማትሠራው የለም ::

ወርሐ ጥቅምት ውርጩ አይሏል:: የጠዋት ማታ ቅዝቃዜው አልተቻለም:: አበራሽ ጊዜ አትመርጥም:: ልብስ አጠባ ባለበት ሁሉ ማልዳ መገኘት ግዴታዋ ነው:: ዕለቱን ከሥራዋ ውላለች:: ካጠበችው የልብስ ክምር የደረቀውን ለይታ አስገብታለች:: ጸሐይ የሚያሻውን አስጥታ ያጠበችበትን ዕቃ መላልሳለች:: ጣጣዋን እንደጨረሰች ልጇን አዝላ መንገድ ጀመረች:: ዛሬ ከወትሮው በተለየ አልቻለችም:: በጣም ርቧታል:: ቤት ገብታ እህል ካፏ እስኪደርስ እየናፈቀች ነው::

ብዙ እያሰበች ከግቢው ወጣች:: ልጇ ከጀርባዋ ተኝታለች:: የእናቲቱ ሆድ ይጮሀል:: አይምሮዋ እንደልማዱ ያስባል:: ቤት ገብታ ማድረግ ያለባትን ታቅዳለች:: ስለነገው ታልማለች:: በዚህ መሐል የረገጠችውን አታውቅም:: በድንገት እግሮቿ ፈጥነው ሸርተት አሉ:: በዋዛ መቆም አልቻለችም:: ከፊቷ ያደናቀፋት ድንጋይ ወደፊት አንሸራቶ በልቧ ድፍት አለች:: አንድ እግሯ ተገንጥሎ የወደቀ መሰላት:: በከባድ ስቃይ ውስጥ ሆና ያዘለቻትን ሕጻን አሰበች:: ከጀርባዋ እንዳለች ናት፣ አልወደቀችም::

የአበራሽን አወዳደቅ ያስተዋሉ መንገደኞች ፈጥነው ሊረዷት፣ ሊያነሷት ሞከሩ:: ቀኝ እግሯ ክፉኛ ተጎድቷል:: ሰውነቷ ይብረከረካል:: ትጮኃለች፣ ታቃስታለች:: ሰዎቹ ምኗን እንደሚይዙ ቸገራቸው:: ልጇን ከጀርባዋ አውርደው፣ እሷን እንደምንም ተሸክመው ከቤቷ አደረሷት::

ጠንካራዋ ሴት እንደዋዛ ከቤት ዋለች:: ስቃይዋ በረከተ፤መንቀሳቀስ መራመድ ተሳናት:: ውሎ አድሮ የወዳጅ ዘመድን ምክር ሰማች:: ከሕክምናው ወጌሻው እንደሚሻል አመነች:: ገጠር ከሚገኘው ወንድሟ ዘንድ መሄድ ግዴታዋ ሆነ::

### ‹‹እምቢኝ፣አሻፈረኝ››

ሁለት ወራትን ሀገር ቤት ያሳለፈችው አበራሽ ሁነኛ በተባለ ወጌሻ ስትታሽ ከረመች:: ተመልሳ አዲስ አበባ ስትመጣ እግሯ እንደታሰበው አልዳነም:: መሥራት መንቀሳቀስ ተሳናት:: መልሳ ከቤት ብትውል ሆስፒታል መሄድ ግድ አላት:: ሐኪሞች የእግሯን ስር የሰደደ ጉዳት አይተው መቆረጥ እንዳለበት አሳወቋት:: ምላሽዋ ‹‹እምቢኝ ፤ አሻፈረኝ ››ሆነ::

አበራሽ በወጌሻ መታሸቷ እያስቆጫት ነው:: ሕክምናው እግሯ አላግባብ በመታሸቱ እንደቀድሞው እንደማይሆን ጠቁሟታል:: አሁን ሮጣ አታድርም፣እርምጃ ጠፍቷታል፣ አቋሟ ተቀይሯል:: ሁለት ዓመት ያስቆጠረው የሕክምና ክትትል በእንጨት ክራንች ቆማ እንድሄድ አገዛት::

አበራሽ እንደቀድሞው በየሰዉ ቤት ልብስ ማጠብ፣እንጀራ መጋገር ፤መሮጥ መላላክ አልቻለችም:: ቤት ተቀምጦ መዋል ዕጣ ፈንታዋ ሆነ:: በየቀኑ ባለቤቷ ሀገሬ ካልገባሁ፣ ካልሄድኩ ይላታል:: ሁኔታው እያስጨነቃት ታስባለች:: መካሪዎቿ አሁንም ዝም አላሉም:: ‹‹ይበጃል›› ያሉትን ጠቆሟት:: ልጇን ይዛ ልመናውን እንድትሞክር ነገሯት:: አበራሽ ግን አሁንም ‹‹እምቢኝ አሻፈረኝ›› አለች ::

### ስመኖር

እሷ ለሕይወቷ ዝም አላለችም:: አልጋዋ ላይ ሆና የሽሮሜዳን ነጠላና ጋቢ መቋጨት ጀመረች:: ቁጭቱ ሲያልቅ ደንበኞቿ ለአንድ ነጠላ ሰባ አምስት ሳንቲም ይከፍሏታል፣ ሳታማርር በምስጋና ትቀበላለች:: ውሎ አድሮ ሥራውን ለመደችው :: ሳንቲሙ ጨምሮ አንድ ብር ከሀምሳ፣ ሁለት ብር፣ እያለ አምስት ብር ሆነላት:: የምታገኘውን ይዛ ለልጇ ዳቦ ደረሰች::

### ከዓመታት በኋላ

የትናንቷ ብርቱ ሴት ዛሬ አካል ጉዳተኛ ሆናለች:: በእጆቿ መሐል ክራንች ተደግፋ ኑሮን ለመግፋት ትጓዛለች:: ሩቅ ለመሄድ፣ ካሰበችው ለመድረስ ባትሮጥም ጉዳቷ ብቻውን ሰበብ አልሆናትም:: ዛሬም ጎጇዋን ለማቆም፣ ጓዳዋን ለመሙላት ትጥራለች:: በመልካም ሰዎች በጎነት ከጨረቃ ቤት ተላቃ የቀበሌ ቤት ገብታለች:: ምስጋናዋ ልቋል::

አበራሽ ከሌሎች አካል ጉዳተኛ ወገኖች ጋር ተደራጅታ ጫማዎችን ትሠራለች:: ሁሌም ከቤቷ ተነስታ ከሥራዋ ለመድረስ የትራንስፖርት ውጣ ወረድ እንደፈተናት ነው:: አንዳንዴ ክራንች አጥብቃ የምትይዘበት ብብቷ ይላጣል፣ አውቶቡስ ጥበቃ የምትቆምበት እግሯ ይዝላል:: እሷ ግን የዛሬን ብቻ አታይም:: ትናንት ሳንቲም ለማግኘት የለፋችበትን ጊዜ ታስታውሳለች ፤ የዛሬውን ጥቂት ብር አስባም በበዛ ምስጋና ትውላለች::

አበራሽ አንዳንዴ በሥራ ጉዳይ መርካቶ መሄድ ግድ ይላታል:: መንገዱ ፈተና አያጣውም:: መኖሯን የማያስቡ፣ ስለእሷ የማይጨነቁ እግረኞች ገፍተው ይጥሏታል:: በዚህ አጋጣሚ እጇ ተሰብሯል፣ እግሯ ጉዳት ገጥሞት ተሰፍታ ታክማለች::

አሁን ወይዘሮዋ አንድዬ ልጇ አድጋላታለች:: የዕድሜዋ መጨመር፣የወጣትነቷ ማበብ ያስደስታታል:: አንዳንዴ ደግሞ እንደ እናት ይህ ውበቷ ከሀሳብ ይጥላታል:: የአበራሽ መኖሪያ ቤት ከወንዝ ዳር ነው:: ጠዋት ወጥታ ማታ እክስትመለስ የልጇ ጉዳይ እንዳስጨነቃት ይውላል::

### አንገት ሰባሪ

አንድ ቀን አበራሽ ሥራ ውላ ቤት ደረሰች:: እግሯ ደጃፏን እንደረገጠ የሰማችው መርዶ ግን ልቧን ሰበረው:: ልጇ በጎረቤት ጎረምሳ ተደፍራለች:: አካባቢው ወንዝ ዳር በመሆኑ ጩኸቷን ሰምቶ ጎረቤት አልደረሰም:: ይህ የሆነው ‹‹የእኔን አካል ጉዳት በሚያውቁ ሰዎች ነው›› ስትል አመነች:: ይህ እውነት ይበልጥ አንገት አስደፋት:: ጉዳዩን ለሕግ ልታሳውቅ ጣረች:: ውጤቱ እንዳሰበችው አልሆነም:: ሁሉን ለፈጣሪዋ ትታ በነገ ላይ ተስፋ ጣለች::

### ከትናንት ዛሬ

አሁን አበራሽ በሥራ ተግታ ትውላለች:: ከትናንት ዛሬ ሕይወቷ መልካም ሆኗል:: የተጎዳው እግሯ በሚያመች ጫማ ታግዞ ይራመዳል:: እጆቿ ክራንች ጨብጠው አካሏን ይደግፋሉ:: ከምንም በላይ ግን በአንድ ልጇ ጉዳይ አዝና አልቀረችም:: ብዙ ያየችባት፣ፈተና የተሻገረችባት ፍሬዋ ዛሬ ኃዘኗ ቀርቶ፣ አንገቷ ቀንቷል:: በወግ ማዕረግ ለሌላ ሰው ተድራለች:: ይህ አይነቱ እውነት የእናት አበራሽን የልብ ቁስል አክሞ ፊቷን ለፈገግታ፣ አንደበቷን ለምስጋና አብቅቷል::

አበራሽ ሁሌም የእግሯን እንጂ የውስጧን ጉዳት አታስብም:: ያሳለፈችው ታሪክ የሕይወቷ አሻራ ነው:: በዛሬው ማንነቷ ጠባሳዋ ሽሯል:: ቁስሏ ጠጓል:: እሷ እግሯ እንጂ ልቧ እንዳልተሰበረ በጽኑ ታምናለች:: ጠንካራዋ ወይዘሮ አበራሽ ደገፋ ::

ዜና

# በማደያዎች የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ነዳጅ ኢትዮጵያ በርካታ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣበትና የሕዝቡን የኑሮ ጫና ለመቀነስ ትልቅ ድጎማ የሚደረግለት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህም ዋጋው ከጎረቤት አገራት ያነሰ በመሆኑ የሚስተዋለውን የነዳጅ ኮንትሮባንድ ለመከላከል ያስችላል ብለዋል።

በመሆኑም አገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመንና በዘርፉ ሚስተዋሉ ሕገወጥነትን በመከላከል ሕብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማቃለል እንደሚያግዝ ጠቁመው፤ በቀጣይነትም የትራንስፖርት ክፍያ ታሪፍን ዲጅታላይዝ በማድረግ የታለመለት የነዳጅ ድጎማን ለታለመለት ዓላማ እንዲውልም ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ገብረመስቀል ጫላ በበኩላቸው፤ የነዳጅ ግብይትን ዲጂታላይዝ ማድረግ በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር የሚገባውንና መንግሥትም ሚሊዮን ብሮችን ድጎማ የሚያደርግለትን ነዳጅ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ያግዛል።

የትኛው ተሽከርካሪ በቀን ምን ያህል ፍጆታ አለው የሚለውን ለመለየትና እንደ አገር ነዳጅ አጠቃቀማችን ላይ ያለውን ሥርዓት ለማስተካከል ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ጠቁመው፤ ለመንግሥት ተሽከርካሪዎችም ሆነ ለግሉ ዘርፍ የሀብት ብክነትን ለማስቀረትም ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ሲሉም ጠቁመዋል።

በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሥራውን በበላይነት የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣል ብለዋል።

የኢትዮ- ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ እንዳሉት ደግሞ፤ የነዳጅ ግብይትን በቴሌ ብር ማድረግ ዲጅታል ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚደረገው ሥራ አካል ነው።

በአሁኑ ሰዓት የቴሌብር ደንበኞች 30 ሚሊዮን መድረሳቸውን ጠቁመው፤ ላለፉት ስምንት ወራት ለድጎማ ተጠቃሚዎች 31 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የነዳጅ ግብይት በቴሌብር አማካኝት ተፈጽሟል። በቀጣይነትም በመላው አገሪቱ በሚገኙ ሁሉም ማደያዎች የነዳጅ ክፍያን በቴሌብር አማካኝት መፈጸም የሚቻልበት ሥርዓት መዘርጋቱን ተናግረዋል።

እስካሁን የተገኙ ውጤቶች ሕዝቡ አገልግሎቱን ለመጠቀም ባሳየው ፍላጎትና ተቋማትም አገልግሎታቸውን ለማዘመን ያግዛል። በቴሌ ብር የሚሰጡ አገልግሎቶችን በመጠቀም ለዲጅታል ኢትዮጵያ እውን መሆን የድርሻችንን እንወጣ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰሀረላ አብዱላሂ እንደገለጹት፤ የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ከተጀመረ ጀምሮ የድጎማ ሥርዓቱ ተመላሽ የሚደረግበት መንገድ አንዱ በቴሌ ብር አማካኝነት ነበር።

እንደ አገር በየዓመቱ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ሀብት ለነዳጅ ግዢ ወጪ ይደረጋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ይህ የኤሌክትሮኒክስ ግብይት ሥርዓት የነዳጅ ስርጭቱንና የት ማደያ ምን ያህል ግብይት ተፈጸመ የሚለውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ያስችላል።

ከመጋቢት 22 እስከ ሚያዝያ 15 የሙከራ ትግበራ ይከናወናል። ከሚያዚያ 30 ቀን 2015 በአዲስ አበባ የነዳጅ ግብይቱ ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ይሆናል ያሉት ወይዘሮ ሰሀረላ፤ ከግንቦት አንድ ቀን 2015 ጀምሮ አገልግሎቱ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል እንዲሰፋ ይደረጋል። ከሐምሌ አንድ ቀን 2015 ጀምሮ ደግሞ በመላ አገሪቱ ሁሉም ማደያዎችና ተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገው የነዳጅ ግብይት ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ የግብይት ዜዴ ይከናወናል ብለዋል።

እንደ አገር ካሉት አንድ ሺ 450 ማደያዎች አንድ ሺህ 250 ዎቹ በቴሌብር አማካኝነት ግብይት መጀመራቸውን አስታውሰው፤ ይህም ትግበራውን ሙሉ ለሙሉ ዲጅታላይዝ ለማድረግ ትልቅ አቅም መሆኑን ጠቁመዋል።

# “ሀገራዊ እሳቤዎቻችንን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ብልጽግና ዕውን ማድረግ የሚያስችሉ ግልጽና ጥራት ያላቸው እሳቤዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና ዕውን መሆን የሚያስችሉ ሀብቶች አሏት። አጠቃላይ የሰው ሀብታችን፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጣችንና የተፈጥሮ ሀብታችን ለብልጽግናችን ዕውን መሆን ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው ብለዋል።

እሳቤዎቻችንን እና ሀብቶቻችንን በአግባቡ ማየት ከቻልን ኢትዮጵያ ለመበልጸግ ትልቅ ዕድል ያላት ሀገር መሆኗን በአግባቡ እንረዳለን። እሳቤዎቻችንና ሀብታችንን ለመጠቀም ደግሞ በሶስተኛነት ጠንካራ አመራር ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት እሳቤዎቻችን የጠሩ፣ የኢትዮጵያን መሰረታዊ ሁኔታዎች ተጨባጭ ያደረጉና ኢትዮጵያን የሚያበለጽጉ እንዲሆኑ ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ሀብቶቻችንን በአግባቡ ለማወቅና ለመጠቀም የሚያስችሉ አቅጣጫዎችንም መከተል ጀምረናል ብለዋል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፣ በአረንጓዴ አሻራና በተለያዩ የልማት ሥራዎች የተፈጥሮ ሀብታችንን መጠቀም እንደምንችል አሳይተናል ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ አደም እንዳስታወቁት፤ ሶስተኛው ጉዳይ ልማቶቹን በውጤታማነት ለመፈጸም የሚያስችል አመራር ነው። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን የሚወድ ፣ ቁርጠኛና በፈተናዎች የማይሸነፍ አመራር አለ።

ፈተናን ወደ ዕድል የሚቀይር፣ በጊዜ የለንም መንፈስ የሚሰራ ውጤታማም አመራር አለን። ስለዚህ እሳቤውን፣ ሀብታችንን እና የአመራር ጥበብን በጥምረት ስናይ ኢትዮጵያ በትክክልም ተስፋ አላት ብለን መናገር እንችላለን ሲሉ አስረድተዋል።

ለ”ብልጽግና መሰረት የሚጥሉ ጉዳዮች እየተገነቡ ይገኛሉ። የዴሞክራሲና የነፃነት ልምምዱ እየተጠናከረ ሄዷል” ያሉት አቶ አደም፤ ባለፉት ሥርዓቶች በርካታ የሕዝብ ጥያቄዎች ነበሩ። በተለይ የኢኮኖሚ፣ የብሔሮች መብት እኩልነት እንዲሁም የዴሞክራሲ ጥያቄ መታየቱን አስታውሰዋል።

የዴሞክራሲ ባህሉ እና የትብብር እሴት ስላልተገነባ የኢኮኖሚውም ሆነ የብሔሮች ጥያቄ በአግባቡ ሳይመለስ መቆየቱን ጠቁመዋል።

ከለውጡ በኋላ ግን የዴሞክራሲ ባህልን የሚገነቡ ሰፋፊ ስራዎች ተከናውነዋል። የዴሞክራሲ ልምምዶቹም በርካታ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ መሰረት የጣሉ ናቸው ብለዋል።

የተቋማት ግንባታና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶበት ተሰርቷል። ተቋማትን በአመራር፣ በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በቴክኖሎጂ ብቁ እንዲሆኑና የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ጥረት መደረጉን ገልጸዋል።

ለሀገረ መንግሥት ግንባታና ብልጽግና የተቋማት ግንባታ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት የተሰጠው ስራ ነው። በተጨማሪ ብልጽግናን ዕውን የሚያደርጉና በአጭር ጊዜ ይገነባሉ ተብለው የማይታሰቡ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል ሲሉ ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች የቱሪስት መዳረሻዎችና የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች በፍጥነትና በጥራት ተሰርተዋል። በተመሳሳይ የዘገዩ ነባር ፕሮጀክቶችም በተሻለ ፍጥነትና ውጤታማነት እንዲገነቡ የተደረገበት አቅጣጫ የብልጽግና ጉዞውን አመላካች ናቸው ብለዋል።

ከለውጡ በኋላ በምንሰራቸው ስራዎች ሁሉ ስንከተላቸው የነበሩ የፍጥነት፣ የጥራትና የዘላቂነት መርሆዎች የብልጽግናን ጉዞ ውጤታማነት የሚያረጋግጡ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ አደም እንዳስታወቁት፤ በቀጣይ በዓለም ላይ አሉ ተብለው የሚጠቀሱ ስጋቶች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች፣ ከቴክኖሎጂ ጋር ያሉ አሉታዊ ጉዳዮችና የወረርሽኝ ስጋቶች ናቸው።

የብልጽግናን ጉዞ አፋጥኖ ዕውን ለማድረግ በነዚህ ስጋቶች ዙሪያ የሚደረገው ዝግጅት ወሳኝ ነው። ኢትዮጵያም በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለጎረቤት ሀገራት የሚተርፍ ስራ በመስራት የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን ለመቋቋም ዝግጅት እያደረገች ትገኛለች ብለዋል።

ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር ተያይዞ ጥቅሙን ከመውሰድ ባለፈ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ስራና በተቋም ግንባታ ሂደት የሚመለከታቸው ተቋማት ጠንካራ ዝግጅት እንዲያደርጉ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

አቶ አደም እንደገለጹት፤ አንድነታችንን አጠናክረን ለመሄድና የብልጽግና ጉዞውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ሀገራዊ ምክክርና መግባባት መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

በዚህ ሂደት የተጀመሩ ስራዎችን ውጤታማ በማድረግ የሀገረ መንግሥት ግንባታና የብልጽግናን ጉዞ ከፍ ባለ ውጤታማነት ማስቀጠል የሚቻልባቸው ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

## አማራ ክልል

የባለንብረቱ ስም ሰሚራ መሀመድ ሰሌዳ ቁጥር3 ኦሮ 25421 ሊብሬ የጠፋ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በቀን 15/07/2015ዓ.ም አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የመኪናው ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ሊብሬ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

ንብረትነቱ ጌታቸው በላይ ተገኘ የሆነ ተሽከርካሪ የፊት ሰሌዳ 01-10726 አማ መሆኑን ባለቤቱ በቀን 5/07/2015 ዓም. በተፃፈ ማመልከቻ አመልክተዋል።
በዚህ መሠረት የመኪናውን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**የሰሜን ወሎ ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**
**የአሽከርካሪና ትራንስፖርት የሥራ ሂደት**

## በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

ንብረትነቱ የአቶ ሰላሙ ተመስገን የሰሌዳ ቁጥሩ 02-01102 ደ/ህ ተሽከርካሪ የሞተር ሳይክል ሰሌዳ የጠፋባቸው ስለመሆኑ በቀን 07/06/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል።
በመሆኑም የመኪናውን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በሃዲያ ዞን የሌሞ ወረዳ ትራንስፖርትና**
**መንገድ ልማት ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ወ/ሮ ምሒራ ሀጋዚ እና በተከሳሽ አቶ ብርሀኑ ተስፋይ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ተከሳሽ ለክሱ ያሎትን መልስ ከነማስረጃው በፅሁፍ እና በሶፍት /ሲዲ/ ለ02/08/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ለሆን ቀጠሮ መልሶን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ሬጅስትራር ቢሮ ቁጥር B 01 በኩል እንድታያይዙ ታዟል እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በስምምነት ያላለቀ ከሆነ ለቃል ክርክር 03/08/2015 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 6ኛ ቤተሰብ ችሎት እንድትቀርቡ ታዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ዘውዱ ጃርሶ ሞጆ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02 01-B50533 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JAATVR54VR7109105 ሞዴል TFR59 የሞተር ቁጥር 904133 የሊብሬ ቁጥር 119332 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የኋላ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ23/02/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል።
በዚህ መሠረት የመኪናውን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብነት ከበደ ሺበሺ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-28480 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር L610-012185 ሞዴል 160B የሞተር ቁጥር L16-777665 የሊብሬ ቁጥር 391745 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 15/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፅዮን በዛብህ አየለ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C02781 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር MBHCZC63S00911995 ሞዴል CZC63S ሞተር ቁጥር K12MP 1387168 የሊብሬ ቁጥር 366981 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 15/7/2015 አመልክተዋል።
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ባለንብረት ስም ኦርቪንድ ላይፍ ስታይል/ኢፓ/ማ/ኃ/የ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A33194 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻሲ ቁጥር JTEBH3F605096931 ሞዴል KDJ150L-GKAEY የሞተር ቁጥር 1KD-2543551 የሊብሬ ቁጥር 426580 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ በው 14/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሁሴን አህመድ መሀመድ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A12155 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAALP34G467P01757 ሞዴል NPC65F የሞተር ቁጥር 4HF1-274827 የሊብሬ ቁጥር 349386 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 14/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ነብዩ አርጋው ሰማን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-84939 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JALK6A130D7100035 ሞዴል fsr33 የሞተር ቁጥር 6HH1-461204 የሊብሬ ቁጥር 190533/404851 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 15/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ያረጋል ደረጀ ዘሪሁን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-32999 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር EAFBDANMEH0000076 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0263313 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 5/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብደላና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግለ ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-30710 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር MROFR22G660501829 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KD7009133 የሊብሬ ቁጥር 352266 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 15/7/2015 አመልክተዋል።
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና**
**ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርት





## የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳው በድጋሚ ማስተካከያ እንዲደረግበት ተጠየቀ

**ብርሃን ፈይሳ**

የአዲስ አበባ ስታዲየም የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ በድጋሚ ማስተካከያ እንዲደረግበት ግብረመልስ ተሰጠ። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ባለሙያ በእድሳት ላይ የሚገኘውን የአዲስ አበባ ስታዲየም እንዲሁም የአቃቂ ስታዲየሞችን ጎብኝተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ እንዲሁም አስፈላጊውን መስፈርት የሚያሟሉ ስታዲየሞች አለመኖራቸውን ተከትሎ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን እንዳያከናውኑ ከታገዱ ስቴድየሞች አንዱ አንጋፋው የአዲስ አበባ ስቴድየም መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች ከምትገነባቸው ስቴድየሞች ባለፈ የአዲስ አበባ ስታዲየም እድሳት ተደርጎለት ወደ ውድድር እንዲመለስ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ እድሳቱ በተለያዩ ምክንያቶች በተያዘለት ጊዜ ባይጠናቀቅም የመጫወቻ ሜዳው ግን በአዲስ መልክ የሳር ተከላና እድሳት እንደተደረገለት ባለቤት የሆነው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ከወራት በፊት አስታውቆ ነበር፡፡ ይሁንና ከሰሞኑ በካፍ ባለሙያዎች በተካሄደው ጉብኝት ሜዳው በድጋሚ ማስተካከያ እንዲደረግለት መጠየቁ ተጠቁሟል፡፡

በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሜዳ ማዘጋጀት የሚችል ድርጅት ባለመኖሩ ባለሙያዎችን ከውጭ በመጋበዝ እንዲሠራ ከዚህ ቀደም የተጠቆመ ቢሆንም፤ የሜዳው ሥራም ሆነ የሳር ተከላው የተከናወነው እጅግ ኋላቀር በሆነ መንገድ በመሆኑ የተለያዩ ትችቶች ሲሰነዘሩ እንደነበር ይታወሳል። ሰሞኑን በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋባዥነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የካፍ ክለብ ላይሰንስ ዲፓርትመንት ኃላፊ መሀመድ ሲዳት በእድሳት ላይ የሚገኘውን የአዲስ አበባ ስታዲየም እንዲሁም የአቃቂ ስታዲየሞችን በጎበኙበት ወቅት፣ በቅድሚያ የተመለከቱት የአዲስ አበባ ስታዲየምን ሲሆን፤



**በእድሳት ላይ የሚገኘው የአዲስ አበባ ስታዲየም ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ፤**

እድሳቱ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን መግለጻቸውን የፌዴሬሽኑ መረጃ ያመላክታል፡፡ እድሳቱ በተለያዩ ምክንያቶች በተቆራረጠ ሁኔታ ሲካሄድ ቢቆይም የሁለተኛው ምዕራፍ ሥራ ከሞናኮ ትሬዲንግ ኮንተራክተር ጋር የኮንትራት ውል በመፈጸም ካለፉት ሁለት ወራት አንስቶ በከፍተኛ ርብርብ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር እና የፌዴሬሽኑ ኃላፊዎችም በተለያዩ ጊዜያት በአካል በመገኘት ክትትል ሲያደርጉበት ቆይተዋል፡፡

በውስት ሜዳዎች ላይ ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን ለመፈጸም የተገደደውን ብሔራዊ ቡድን ወደ አገሩ ለመመለስም ቀድሞ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ከሜዳው ውጪ ያለው እድሳት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ አሁን ባለበት ደረጃም መሻሻል ይገባቸዋል በሚል የተጫዋቾች መግቢያ፣ የመልበሻ ክፍል ወለሎች፣ የሚዲያ ትሪቡን፣ የቪአይፒ እና ቪቪአይፒ ትሪቡኖች፣ የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም የቦታ ሽግሽግ ሊደረግባቸው ይገባል በሚሏቸው ክፍሎች ላይ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ባለሙያው በአጠቃላይ በእድሳቱ የታዘቧቸው ጉዳዮች ላይም ግብረመልስ በማዘጋጀት በቀጣይ እንደሚልኩ አሳውቀዋል፡፡ በተለይ በፍጻሜ ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራና የተሰጡ የማስተካከያ ሀሳቦች ከተተገበሩ መስፈርቱን ማሟላት እንደሚቻልም ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

ሌላኛው ጉብኝት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተገነባ ባለው አቃቂ ስታዲየም ነው የተደረገው፡፡ አስቀድሞ የዞናል ስታዲየም ደረጃን እንዲያሟላ በማድረግ የተጀመረው የዚህ ስታዲየም ግንባታ፤ በድጋሚ የዲዛይን ማሻሻያ በማድረግ የካፍ መስፈርትን የሚያሟላ ዓለም አቀፍ ስታዲየም እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህንን ተከትሎም ባለሙያው ያለበትን ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ፤ የመልበሻና የሚዲያ ክፍሎች፣ የቪአይፒ እና ቪቪአይፒ ትሪቡኖች እና ሌሎች አስፈላጊ ክፍሎች ሊቀመጡባቸው የሚገባቸውን ስፍራ ከማቀያየር ውጪ በጥሩ ሁኔታ መገንባታቸውን ተናግረዋል።

ግንባታው ከ70 በመቶ በላይ የደረሰው የአቃቂ ስታዲየም በግንባታ ላይ ከመሆኑ አንጻር ለማስተካከያ ሥራ ምቹ ነው። በመጫወቻ ሜዳው ግንባታ ላይ ግን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የዘርፉ ፍቃድ ባላቸው ኩባንያዎች እንዲገነባ ባለሙያው መክረዋል። በአጠቃላይ የተሠሩት መሠረታዊ ሥራዎች በቂ ጊዜ እና ትኩረት በመስጠት እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ ጥሬ ዕቃ በመጠቀም የማጠቃለያ ሥራዎች ማከናወን ከተቻለ የካፍን መመዘኛዎች በቀላሉ ማሟላት እንደሚችልም ባለሙያው መጠቆማቸውንም በመረጃው ተመላክቷል። ከዚህን ስታዲየም ቀጣይ የሥራ ሂደት በሚመለከትም ባለሙያው በየ3 ወሩ በተንቀሳቃሽ ምስል በታገዘ ቴክኖሎጂ ውይይት በማድረግ ክትትላቸውን እንደሚቀጥሉም አሳውቀዋል።

በጉብኝት መርሃ ግብሩ ላይ የኢፌዴሪ ባህል እና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጂራ፣ በፌዴሬሽኑ የክለብ ላይሰንሲንግ መምሪያ ኃላፊ አቶ አምሀ ተስፋዬ፣ የግንባታ ኃላፊዎች እንዲሁም ሌሎች ባለሙያዎች ተገኝተዋል።


**የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሞኤንኮ/ አክሲዮን ማሕበር**

የኩባንያው የባለአክሲዮኖች 65ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 2441 በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ከጠዋቱ በ 500 ሰዓት ላይ ይካሄዳል፡፡

**አጀንዳ**

1. የዳይሬክተሮችን ሪፖርት ማጽደቅ፣
2. የኦዲተሮችን ሪፖርት ማጽደቅ፣
3. እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31 ቀን 2022 (ታሕሳስ 22/2015 ዓ.ም) ያለቀውን ዓመት የሂሳብ መግለጫ ማጽደቅ፣
4. ስለትርፍ ክፍያ የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ ማጽደቅ፣
5. የዓመቱን የዳይሬክተሮች ኃላፊነት ማውረድ፣
6. የዳይሬክተሮች እና/ወይም ኦዲተሮች ሹመትና ለውጥ፣

**በዳይሬክተሮች ቦርድ ትእዛዝ**
**የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ /ሞኤንኮ/ አ.ማ.**



**የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሞኤንኮ/አክሲዮን ማሕበር የስብሰባ ጥሪ**

የኩባንያውን የባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሚያዝያ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 2441 በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ከጠዋቱ በ5:30 ሰዓት ላይ ይካሄዳል፡፡

**አጀንዳ**

1. **የድርጅቱን መመስረቻ ጽሑፍ ስለማሻሻል፡፡**

በዳይሬክተሮች ቦርድ ትዕዛዝ
የኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ /ሞኤንኮ/አ.ማ

**THE MOTOR AND ENGINEERING COMPANY OF ETHIOPIA /MOENCO/ S.C.**
**NOTICE OF MEETING**

Notice is hereby given that an Extra-ordinary General Meeting of the Shareholders of the Company will be held at the Head Office of the Company, Bole Subcity, Kebele 03, House No. 2441 on April 28, 2023, at 11:30 a.m

**Agenda:**

1. **Amendment of the Company Memorandum of Association.**

**BY ORDER OF THE BOARD**
**THE MOTOR AND ENGINEERING COMPANY OF ETHIOPIA /MOENCO/ S.C.**